


# አስደናቂው ድነታችን

## Our Astonishing Salvation

"አስደናቂው ድነታችን እግዚአብሔር አባታችን በአስተማማኝ እጁ(ባህሪው)
እኛን እንደያዘን እንጂ እኛ በሚለዋወጠው ባህሪያችን
እርሱን እንደያዝነው አይደለም።"

ዮሐ 10፥28-29, 1 ዮሐ 4፥10

Scriptural Jesus ministry
በያዕቆብ አሸናፊ(James)

የማይሸጥ(በነፃ የሚሰጥ)

# ማውጫ

## ምዕራፍ አንድ


## የመዳን መንገድ ........................................................................

የመዳን መንገድ በብሉይ ኪዳን .....................................................
የመጀመሪያው አዳም መዳኛ መንገድ..............................................
የአቤል የመዳን መንገድ...............................................................
የኖህ የመዳን መንገድ...................................................................
የአብርሃም የመዳን መንገድ ........................................................
ታላቁ መስፍን ሙሴና ድንቋ በትር...................................................
የመዳን መንገድ በመገናኛው ድንኳን ...............................................
የሚቃጠል መስዋዕት .......................................................
የእህል ቁርባን ...............................................................
የሕብረት መስዋዕት .......................................................
የኃጢያት መስዋዕት .........................................................
የበደል መስዋዕት ...........................................................
የመዳን መንገድ በጥማትና በረሀብ...................................................
የመዳን መንገድ በእባብ ከመነደፍ በኃላ............................................
የአዛባዊቷ የረሀብ የመዳን መንገድ....................................................

## ምዕራፍ ሁለት የዘላለም ሕይወት ዋስትና

የሮሜና የያዕቆብ መልእክት ማብራሪያ...............................................
የእግዚአብሔር ምክንያት አልባ ፍቅር..................................................
የተገኘንበት አባት..........................................................................
የአዲስ ኪዳኑ መልካም እረኛ..........................................................
የአዲስ ኪዳን ዋስ.........................................................................


## ምዕራፍ ሦስት

## በዘላለም ሕይወት ዋስትና ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ የሚመስሉ ጥቅሶች እና ማብራሪያቸው


ማቴዎስ 7 ..........................................................................
ማቴዎስ 24 እና 25.......................................................................
ዮሐንስ 15 ና ማቴዎስ 13..............................................................
1ቆሮንጦስ 6,ገላትያ 5 እና ኤፌሶን 5..............................................
1 ቆሮንጦስ 9.............................................................................
ከዕብራውያን መልእክት የሚነሱ ጥቅሶች..........................................
ከራዕይ መጽሐፍ የሚነሱ ጥቅሶች..........................................................

## ከጸሐፊው

ይቺ ትንሽ መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስን ካገኘሁበት ጊዜ ጀምሮ ከቅዱሳት መጽሐፍትና ከመንፈስ ቅዱስ የተማርኩት ስትሆን ከተገለጠው ታላቅ ድነት አንጻር ያብራራሁበት መንገድ በቂ ነው ብዬ አላስብም። ነገር ግን የትኛውም ክርስቲያን አንብቦ ሊረዳው በሚችለው ቋንቋ ለመግለጽ ሞክሬአለው። በጌታችን የመጣው አስደናቂው እምነታችን መሰረቱ ይህ አስደናቂው ድነታችን ነው።ይህ ታላቅ አስተምሮ የሌለው ሰው እውነተኛ ክርስቲያን ነው ለማለት ያስቸግራል።ምክንያቱም ቅዱሳት መጽሐፍት ድነት የሚገኝባቸው መጽሐፍት ናቸውና (2 ጢሞ 3)።

## ለአንባቢያን ማሳሰቢያ

ይህ አስደናቂው ድነታችን የሚለው መጽሐፍ እስትንፋሰ እግዚአብሔር እና ስህተት አልባ አለመሆኑን እንድታውቁ እፈልጋለው። ጸሐፊው ከቅዱሳት መጽሐፍት ባገኘው መረዳትና የእግዚአብሔር ጸጋ በረዳው መሰረት የጻፈው ሲሆን እንደሰው ልጅ ጣልቃ ገብነት ስህተቶች ሊኖሩትና እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት ሊታረም የሚችል ነው። እስትንፋሰ መለኮት እና ስህተት አልባ የሆኑት ቅዱሳት መጽሐፍት በመጀመሪያዎቹ በብሉይ ነቢያትና በአዲስ ኪዳን ሐዋሪያት የተፃፉት 66 ቱ መጽሐፍት ብቻ ናቸው። በመጽሐፉ ከተባረካችሁበትና ከተጠቀማችሁበት ጌታን ለሚወዱ ሁሉ በማካፈል የእግዚአብሔርን መንግስት ልጆች በመረዳት ባለጠግነት ለማሳደግ ይተባበሩ፤ ደግሞም ጌታ ኢየሱስንና በእርሱ በኩል የፈሰሰውን የማዳን ጸጋ በተለያዩ ሐይማኖቶችና በጨለማው አለም ለታሰሩ ሰዎች በማካፈል የእግዚአብሔርን መንግስት እንዲያሰፉ በጌታ ፍቅር እጠይቃለው።በገዛ ደሙ የዋጃትን የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ሊያንጽና ወደ ፍጹም ሙላቱ ሊያሳድግ ለሚችል አገልግሎት ሁሉ ይህን መጽሐፍ በተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይቻላል። የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስና በቅዱሳን መካከል መለያየትን ለመፍጠር ይህን መጽሐፍ መጠቀም በፍጹም የተከለከለ ነው።

በመጽሐፉ ውስጥ ሆን ተብሎ(purposely) ብዙ ጥቅሶች እስከነመልእክታቸው ተጠቅሰዋል ምክንያቱም ጥቅስ ብቻ አስቀምጠን ብናልፍ ብዙ ሰው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልሶ የማንበብ ልማድ ስለሌለው ሳያነበው ያልፈዋል በሚል ነው።

## What a Wonderful Salvation!!!!!!

# ከቀደሙ አንባብያን

✍ 🗆 ሰላም የተወደዳችሁ የአባቴ ብሩካን በጌታችን እና በመድሀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ

ሰላምታዬን እያቀረብኩ፥ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ከሰጠን የእግዚአብሔርን ትልቁን ሀሳብ እና ሀይል የሆነውን የጸጋውን ወንጌል እግዚአብሔር በገለጠላቸው መጠን እና በመንፈስ ቅዱስ አማይነት ተረድተው ተንትነው ከአስተማሩን እና እያስተማሩንም ካሉት እና በኑሮአቸው ወይም በሕይወታቸው Model ከሆኑልን ከዚህ ዘመን ወጣቶች መካከል ወንድማችን ያዕቆብ አንዱ ነው። አሁንም ደግሞ እግዚአብሔር በረዳው እና በገለጠለት መሠረት "OUR ASTONISHING SALVATION" ወይም ደግሞ በ አማሪኛው ትርጉሙ "አስደናቂው ድነታችን" የሚለውን መጽሐፍ ይዞልን ብቅ ብሏል፥ እኔም ከዚህ መጽሐፍ ድንቅ ትምህርት ያገኘሁበት ሲሆን፥ ከዚህም መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ማንነት ትልቁ እና ዋነኛዉ ስለ "ድህነታችን ቀንድ ሰለ ሆነው ስለ ደሙ ማንነት፣ ሰለ አዲሱ ኪዳን (በክርስቶስ በኩል ስለተደረገው ስምምነት) ከዚህ መጽሐፍ ብዙ የተማርኩበት እና ከትናንትናው ይልቅ ዛሬ ክርስቶስን በውስጤ ሰለ ቀረጸና በጣም የተገረምኩበት መጽሐፍ በመሆኑ እናንተም ብታነቡት እና ብትጠቀሙበት ትልቁ ደስታዬ ነው።

ከእህታችሁ ፂሆን ኦብሳ

ꕯ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን፥ የአምላክ ጸጋ በረዳው መጠን ሁሉም ክርስቲያን ሊያውቀው የሚገባውን አስደናቂ መዳን ወንድማችን ያዕቆብ በቀላል ቃላት ጥልቁን መረዳት ጽፎልናል። እኔን ከጠቀመ የማይጠቀም ሰው የለምና ሁላችሁ ብታነቡት ትጠቀማላቸሁ።ለሌሎችም አካፍላችሁ ከአምላክ ራእይ ጎን በመቆም ምስክር ይሁኑ። ጸጋ አብሯችሁ ይሁን።

ከሾይስ ይልቃል

## በቀጣይ በጸሐፊው የሚወጡ ጽሑፎች

አስደናቂው እምነታችን

አስደናቂው አዳኛችን

አስደናቂው ቅዱስ መጽሐፍን መረዳት

አስደናቂው ሊቀ ካህናችን

አስደናቂው የዘመን ፍጻሜ

# ምዕራፍ አንድ

# የድነት መንገድ

- ድነት ማለት ሰዎች ሁሉ በመጀመሪያው አዳም አለመታዘዝ ምክንያት ከገቡበት ኃጢያት እና ኃጢያት ከሚያመጣቸው ውጤቶች ሁሉ በኋለኛው አዳም( በኢየሱስ ክርስቶስ) በኩል መትረፍ ፣ ማምለጥ ፣ መከለል ወይም መሰወር ማለት ነው። የመጀመሪያው አዳም ሰዎችን ሁሉ በመወከል ሀጢያትን ሲሰራ እኛም ሰዎች ሁሉ በእርሱ ወገብ ውስጥ በመሆን በኃጢያቱም በውጤቱም አብረናል። በዚያም ሀጢያት ምክንያት ሞትና መልካም ያልሆኑ ነገሮች ወደ ሰው ሁሉ ደረሰ። ሰዎች ሁሉ በኃጢያት በመውደቃቸውና ራሳቸውን መረዳት በማይችሉበት ዝቅታ ስለወደቁ እግዚአብሔር አምላክ የመዳንን መንገድ በፍቅሩና በምህረቱ በኩል አዘጋጀ። ይህም የመዳን መንገድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችን ነው።

ምንም እንኳን የአዳም በኃጢያት መውደቅና ጨለማን መምረጡ የፍቅሩን አምላክ ልብ ቢያሳዝንም፤ ይህ ክስተት ግን ለእግዚአብሔር አዲስ አልነበረም። ምክንያቱም እርሱ አምላክ በመሆኑም ገና በዘላለም ውስጥ ሊሆን ያለውን ሁሉ የሚያውቅ ስለነበረ ገና የቀድሞ አባታችን አዳም ሳይፈጠር የሚወድቀውን አዳም ማዳኛው መንገድ በስላሴ ምክር ተወሰነ።ይህ የፀናው የስላሴ የማዳን ምክር አዳም በወደቀበት ቀን መነገሩና አዳምን ራሱ ወደዚህ መዳኛ መንገድ እግዚአብሔር መምራቱ ደግሞ የአምላክን ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን ጥልቅ ፍቅር ይገልጻል።አዳም በኃጢያት በወደቀ ዕለት ነበር እግዚአብሔር ወደፊት ሊሰራ ያሰበውን የቤዛነቱን ስራ በምሳሌ ይገልጥ የጀመረው(ዘፍ 3፥21) ።

ገና በሰው ልጅ ውድቀት ማለዳ መነገር የተጀመረው የሰው ልጅ ወደ መዳን መምጣት በራሱ ስራና ጥረት ሳይሆን በእግዚአብሔር ስራ ብቻ እንደሆነ ነው።ይህንንም የምንረዳው እግዚአብሔር በኤደን ገነት ሳሉ አንድ በግ አርዶ ቁርበቱን እንዳለበሳቸው ከመጽሐፉ ስናስተውል ነው።

“እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።”
— ዘፍጥረት 3፥21

ከዚህ ቃል የምንረዳው እውነት አለ ይህም "አዳም ከወደቀ በኃላ አንዳች በጎ ስራ ለመስራት ሳይታትር ፣ ሳይጾምና ሳይጸልይ ፣ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሳይጥር እግዚአብሔር ለሴቲቱ የተናገራትን የተስፋ ቃል በማመንና በቃሉ በማረጋገጡ ብቻ እግዚአብሔር በግ አርዶ ቁርበቱን አለበሳቸው። ይህ ቁርበት የአዳም የላብ ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።" እንግዲህ ይህ ትምህርት ነው በአዲስ ኪዳን ጸጋ ተብሎ የቀረበው። ሰዎች የሚድኑት ከመጀመሪያውም እንደተነገረው በራሳቸው ስራና ድካም ሳይሆን እግዚአብሔር በሰራላቸው ስራ ብቻ ነው።ይህን የከበረ የእግዚአብሔር ሚስጢር ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል

ሮሜ 3
23 ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤
24 በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።
25 እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥

ሰዎች ሁሉ ኃጢያተኞች በመሆናቸው ምክንያት እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን የኃጢያት መስዋዕት አድርጎ እንዳቀረበው ሐዋሪያው ያስተምረናል።ቀጥሎም በዚህ የመስዋዕትነት ስራ የሰው ልጆች ድነት እንደተፈጸመ ሐዋሪያው በዕብራውያን መልእክቱ እንዲህ በማለት ያረጋግጥልናል

ዕብራውያን 10
-----------

10 በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።
11 ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤
12 እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥
...
14 አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።

የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስራ ብቻ ሰዎችን ለዘላለም አድኖ ያስቀራል የሚለው እውነት ምነኛ ደስ የሚያሰኝ በረከት ነው ? ይህንንስ መረዳት ምን ያህል የልብ ዕረፍትና መረጋጋት፤ በእግዚአብሔርም ብቻ ደስ የመሰኘት ምክንያት ነው?

ምንም እንኳን ቅዱሳት መጽሐፍት ሰዎች የሚድኑት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስራ ብቻ መሆኑን ሙሉ በሙሉ ቢያውጁም ለሆዳቸው ያደሩ ክፉ ሰዎች ግን በዚህ እውነት ላይ የራሳቸውን ሰው ሰራሽ ዕውቀት በመጨመር የእግዚአብሔርን ጸጋ አጣጥለውታል። ሰዎች ሕግን በመጠበቅ ወይም በመልካም ስራ የሚድኑ ከሆነ የክርስቶስን የመስቀል ስራ ምነኛ እያጣጣልን ነው።

“የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ።" ገላትያ 2፥21

እውነተኛ አማኞች ያገኙት የዘላለም ሕይወት በምንም ሊጠፋ የማይችል እንደሆነና እማኞች በእግዚአብሄር ፀጋ እና ኃይል በቅድስና በመኖር እስከ መጨረሻ እንደሚድኑና ድነታቸውን የማጣት ፍርሃት በልባቸው እንዳይኖር ቅዱሳን መጽሐፍት ያስተምሩናል፡(1 ጴጥ 1፥23, 2 ጢሞ 1፥7-9)።

# የድነት መንገድ በብሉይ ኪዳን

## 1. የመጀመሪያው አዳም የዳነበት መንገድ

በኤደን ገነት በኃጢያት የወደቀው አዳም የምስራቹን ወንጌል በቀጥታ ከምንጩ ከእግዚአብሔር የተሰበከለት፤ በውድቀቱ የተሳተፉ ሁሉ የስራቸውን ዋጋ ለመቀበል ተሰልፈው በቆሙበት ነው ያ የብርሃን ወገግታ ከአርያም የተሰማው። አዳም የምስራቹን ቃል ከአርያም በመስማት ተቀብሎ በማመንና እምነቱን በቃሉ በመግለጡ እግዚአብሔር የማዳንን ልብስ አልብሶ የጽድቅን መጎናጸፊያ ደረበለት። እንደ ቅዱሳት መጽሐፍት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለአዳኙ በግልጽ የተነገረበት ክፍልና አዳምም ያመነበት እውነት ይህ ነው
“በአንተና በሴቲቱ መካከል፥ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።”
— ዘፍጥረት 3፥15
ይህ ቃል ወደፊት ስለሚመጣው መሲህ የተነገረ የመዳን ተስፋ ቃል ሲሆን ይህን እውነት ከሰማይ ያደመጠው አዳም ሚስቱ ከተረገመችበት መረገም ሁሉ የሚመጣው ተስፋ ይበልጣል በማለት እምነቱን እንዲህ ገለጠ
“አዳምም ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም አወጣ፥ የሕያዋን ሁሉ እናት ናትና።”
— ዘፍጥረት 3፥20
ያ ሁሉ መርገም በዚያ ልክ ወረዶባት አዳም ግን ከተረገምሽበት መረገምና ካመጣብን ጣጣዎች ሁሉ ከአንቺ የሚወጣው እርሱ ሞታችንን ደምስሶ ሕያዋን ያደርገናል አላት። የአዳም እንዴት የሚደንቅ መረዳት ነው? በእርግጥም እንዳለው ከአለም ሁሉ ኃጢያት የሚበልጥ የአምላክ ቅድስናና ሕያውነት በሚመጣው በሴቲቱ ዘር በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ተገልጦአል(ሮሜ 5፥15)።ሐዋሪያት እንዳስተማሩን ከፍጥረት መጀመሪያ እስከ ፍጥረት ፍጻሜ ድረስ ከአርያም የሚሰበከው አንድ የምስራች ወንጌል አለ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው(ሮሜ 1፥1-4)። ይህን የመዳን ወንጌል የምንቀበልበት መንገድ ደግሞ
ሮሜ 10
----------

 ነገር ግን ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።
 ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤
1 ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።
11 መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና።

በአዳም ሕይወት የተከናወነውም ይሄው ነው " ሰማይ ሰበከለት እርሱም በልቡ አመነና በአፉ መሰከረ።" ደግሞም ይህ ከሆነ በኃላ እግዚአብሔር አዳምን እንዴት እንደተቀበለው ስንመለከት በጣም እንደነቃለን።
“እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።”

— ዘፍጥረት 3፥21

እንዲሁ መሲሁ ከመጣ በኋላ በወንጌል የሚያምኑትን ቅዱሳን እግዚአብሔር ያደረገው ገና በፍጥረት መጀመሪያ ያደረገውን ያንኑ ነው
ገላትያ 3
----------

2□ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤
2□ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።

ይህ ክርስቶስን የለበስንበት ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅንበት እንጂ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በኩል በውሃ የተጠመቅንበት አይደለም( 1 ቆሮ 12፥10-13) ። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቅንበት ጥምቀት የመዳንን ልብስ አልብሶ የጽድቅን መጎናጸፊያ ደርቦልናል

“አክሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ፥ በጌጥ ሽልማትዋም እንዳጌጠች ሙሽራ፥ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፥ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛልና በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፥ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች።”
— ኢሳይያስ 61፥10

በአዳም በኩል እግዚአብሔር ያከናወነው ድንቅ የወንጌል ምሳሌ በዚህ አላበቃም። አዳምና ሚስቱ ያን ቁርበት ከለበሱ በኋላ ምን ሆነ ?

ዘፍጥረት 3
----------

21 እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።
22 እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፥ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፥ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤

አዳም የለበሰው ቁርበት ወደ ፊት የሚመጣው የክርስቶስ ምሳሌ ስለሆነ፤ አዳም በኃጢያት ከወደቀ በኋላ ከስላሴ እንደ አንዱ(እንደ ወልድ) የሚሆንበት ሚስጢር ተገለጠ። እግዚአብሔር ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ ማለትም እኛን መሰለ አለ ምክንያቱም የለበሰው ቁርበት። ዛሬም ሰዎች በእግዚአብሔር ልጅ ሲያምኑ ወደ ልጁ መልክ እንደሚመጡ ማለት ነው(ሮሜ 8፥29,, 1 ዮሐ 3፥2,2 ቆሮ 3፥18)። ከዚያ ወዲያ የለበሰው ልብስ ዘላለማዊና የማይነጥፍ ፤ በዳነውም መዳን አርፎና ተዘልሎ እንዲቀመጥ ፤ እግዚአብሔር አምላክ በሰራለት ስራ እንዲደላደልና የሰው ልጅ ከዳነ በኋላ ሌላ ለመዳን የሚፈጽመው ነገር እንደሌለ ለማሳየት መንገዶቹን ሁሉ ይዘጋቸዋል።

እግዚአብሔር አምላክ ሰው በጸጋና በእምነቱ በኩል ከዳነና ክርስቶስን ከለበሰ ኋላ እንደገና ለመዳንና ሕያው ሆኖ ለመኖር እጁን መዘርጋት እንዳይጀምር

እግዚአብሔር የሀይማኖቶችን መንገድ ሁሉ ይዘጋል። ዛሬም ሰዎች በእግዚአብሔር ልጅ ካመኑና ከዳኑ በኃላ እንደገና ለመዳን የሚያደርጉት ተግባር እንደሌለ እግዚአብሔር ያስተምረናል።እግዚአብሔር ሰው እጁን ዘርግቶ( በራሱ ጥረት) የዘላለም ሕይወትንና ሕያወነትን ማግኘት እንደማይችል ቃሉ ያስተምረናል(ሮሜ 3፥19-30, 11፥4, ቲቶ 3, 2 ጢሞ 1፥7-9)።

የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ይድናል፣ ይጸድቃል፣ ይቀደሳል፣ ዳግም ልደትን ያገኛል፣ ክርስቶስን በመልበስ ከእግዚአብሔር እንደ አንዱ ይሆናል(የልጁን መልክ ይመስላል)፣ ከዚያ ወዲህ ዳግም ለመዳን የሚፈጽመው አንዳች ተግባር የለም።

## 2. የአቤል መንገድ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ ከእምነት አባቶች ዝርዝር ውስጥ በቀዳሚነት የተቀመጠው የአዳም ሁለተኛ ልጅ አቤል ነው(ዕብ 11)።አቤል የተመሰከረለትን ምክንያት ከቅዱሳት መጽሐፍት እንመልከት

“አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፥ በዚህም፥ እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር፥ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።”

— ዕብራውያን 11፥4

የአቤል መስዋህት ከቃየል የበለጠው የሚሰጥበት ልብ ታይቶ አይደለም።ምክንያቱም የትኛውም የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍል የልባቸውን አይነት አያስተምረንም። አጥርተው የማያዩና ለመንፈስ ቅዱስ ጊዜ የማይሰጡ ሰዎች ያንን ሲያወሩ ይሰማሉ። ከአዲሳት መጽሐፍት ዋቢ በመነሳት ግን እግዚአብሔር የተመለከተው የመጡበትን መንገድ እንደሆነ ያስረዳናል።

“ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።”

— ይሁዳ 1፥11

የጌታ ወንድም ይሁዳ እግዚአብሔር የተመለከተውና የናቀው የቃየንን ልብ ሳይሆን የቃየንን መንገድ እንደሆነ እየተናገረ በአዲሱም ኪዳን ያን መንገድ የሚከተሉትን የጥፋት ልጆች እያስጠነቀቀ ይጽፍልናል።የቃየን መንገድ ሲባል? ቅዱሳት መጽሐፍት ስለመንገድ ምን ያስተምሩናል?

“ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።”

— ዮሐንስ 14፥6

ማቴዎስ 7

----------

13 በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤
14 ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።

በአዲሳት መጽሐፍት ዋቢ ትርጉም ተነስተን መንገድ ጌታችን ራሱ እንደሆነ

ተረድተናል።አለምና ሀይማኖቶች በራሳቸው ብዙ ፍልስፍናና የሚዳንባቸውን መንገዶች ሰፋ አድርገው ያስቀምጣሉ።እውነተኛው መዳኛ መንገድ ግን አንድ ብቻ ነው።በመስቀል ላይ በድካም መሰቀሉን ተመልክተው ናቁት፤ ሌሎችን ሳይሆን ለራሱም ተስፋ ያለው አይደለም አሉ። በእርግጥም ክርስቶስና የመስቀሉ ስራ ጠባብና ለመግባትም(ለማመንም) የሚከብድ ነው። እውነተኛው የመዳን መንገድ ግን ያህ በመስቀል ላይ ዕርቃኑን የታየው በግ ነው። በእርሱ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል። አቤል የመጣበት የመስዋህት መንገድ እግዚአብሔር ለነአዳም የሰበከላቸውን ወንጌል በማመን በበግ መስዋህት ነው። ቃየል ግን ከተረገመችው መሬት የላቡ ውጤት የሆነውን መስዋህት ይዞ ቀረበ።እግዚአብሔር ግን ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ ማለትም "ወደ አቤል" ሲል የዕብራውያን መጽሐፍ እንደፈታልን "ወደ እምነቱ" ፣ "ወደ መስዋዕቱ" ሲል ደግሞ "እምነቱን ወደ ጣለበት በግ(የሚመጣው ክርስቶስ) ማለቱ ነው። ዛሬም ማንኛውም ሰው የሚድነውና በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኘው በክርስቶስ መስዋህትነትና ክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ብቻ ነው።

“በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ(በክርስቶስ) አለን።”

— ኤፌሶን 3፥12

ቃየን ግን እግዚአብሔር ከረገማት ምድር ፍሬ (በራሱ መልካም ስራ) ወደ እግዚአብሔር ለመግባት ፈለገ እግዚአብሔር ግን አልተቀበለውም። አባቱ አዳም በመጀመሪያ ያደረገው በኃጢያቱ ምክንያት የተገለጠውን ዕርቃኑን ለመሸፈን ከምድር ፍሬ በተገኘ ቅጠል ሸፈነ እግዚአብሔር ግን የለበሱት ቅጠል የማይቆይና ደርቆ የሚራገፍ በመሆኑ የበግ ቁርበት አበጅቶ አለበሳቸው። ያህ ማለት ዕድሜ በሌለውና በማይቀጥል መልካም ስራችሁ አትታመኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ በተገለጠው በበጉ የክብር ልብስ አሸብርቁ ይለናል ወንጌል።ያህ የአቤል መስዋዕት እስከዛሬ ድረስ እየተናገረ ነው የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ "ወደ እግዚአብሔር መግቢያ በሩ ለሰው ልጆች ኃጢያት በጎልጎታ ላይ የታረደው በግ ነው። ክብር ምስጋና ባለጠግነት መንግስትም ሁሉ የክብር ልብሳችን ለሆነው ለታረደው በግ ይሁን አሜን።

## 3. የኖህ መንገድ

በኖህ ዘመን የነበረችው አለም በኃጢያትን በአመጽ የተሞላች፤ እግዚአብሔር አምላክም በሰው ልጆች እጅግ ያዘነበትና ሰዎችን በመፍጠሩም በባህርዩ የተጸጸተበት (እንደሰው ያልሆነ መጸጸት) ጊዜ ነበር(1 ሳሙ 15፥29,ዘኊ 23፥19)። ኖህ ግን ከአባቶቹ የተነገረውን ተስፋ በመጠበቅ ከጠፊዋ አለም ጋር አልተባበረም።ብዙ ሰው ኖህ በራሱ ጽድቅ ከጥፋት ያመለጠ ይመስለዋል ነገር ግን ከጥፋቱ ያመለጠው ከአባቶቹ በመጣው በተስፋው ቃል ነበር።

ዘፍጥረት 5

-----------

[2]□ ላሜሕም መቶ ሰማንያ ሁለት ዓመት ኖረ፥ ልጅንም ወለደ።

[2]□ ስሙንም፡- እግዚአብሔር በረገማት ምድር ከተግባራችንና ከእጅ ሥራችን ይህ ያሳርፈናል ሲል ኖኅ ብሎ ጠራው።

ለሔዋን የተነገራትና አዳም ያመነውን የተስፋ ቃል ለልጆቻቸው ሲያስተላልፉ እንደነበር ከላይ ያለው ጥቅስ ያስረዳል። ላሜሕ የኖህ አባት ከአዳም ጀምሮ ዘጠነኛ ትውልድ ማለትም እስከ 2000 አመት ድረስ በመሐላቸው ርቀት አለው ግን ይህ ላሜሕ የተባለው ሰው እግዚአብሔር ምድርን እንደረገመና ከተረገመችው እርግማን ደግሞ የሴቲቱ ዘር ነጻ እንደሚያወጣ በእምነት ይናገራል። ማለትም ይህ የሴቲቱ ዘር በተስፋ በኩል በእምነት ይሰበክ ነበር ማለት ነው። አባታችን ኖህ በተሰበከው የሴቲቱ ዘር ላይ ባለው እምነት በኩል ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን ተቀበለ።ይህ ምገስ የተባለው ቃል ጸጋ( In english bible "Grace") ለሚለው ቃል ተለዋጭ ነው።

ኖህ ድነትን ያገኘው በዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ሁሉ በመልካም ስራው የተሻለ ሰው ስለነበር ሳይሆን በአባቶቹ የተነገረውን ከሴቲቱ የሚወለደውን ነጻ አውጪ መስፍን ተስፋ በእምነት አሜን ስላለ ነው።ይህ የተስፋ ቃል ዘር በመጣ ጊዜ ከተግባራችንና ከእጅ ስራችን ያሳርፈናል አለ ማለትም ሰዎች የሚድኑት በተግባራቸውና በእጅ ስራቸው(በመልካም ስራቸው) ሳይሆን በሚመጣው ዘር በኩል ብቻ እንደሆነ ማረጋገጫ ነው። የዚህም የተስፋ ቃል እምነት ከዘመኑ ከነበሩ ሰዎች ለይቶ በጽድቅ ሕይወት እንዲመላለስ አድርጎታል።የዚህ እምነት መገለጫ ደሞ ዝናብ አይተው በማያውቁ ሰዎችና ፍጥረት መሀል ከእግዚአብሔር ዘንድ የተነገረውን ቃል በማመን መርከብ ሰራ።

ይቺህ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተናገደችው ዝናብ የጥፋት ውሃን ነበር።የእምነት አባታችን ኖህ ከሴቲቱ የሚመጣውን ዘር በተስፋ አምኖ ከዚህ አለም ሰዎች ጋር በኃጢያታቸው እንዳላበረ ዛሬም ያለን ከአይሁዳዊቷ ድንግል የተወለደውን፤ ሙሴ በሕግ መጽሐፍ የተናገረውን ነቢያትም በትንቢታቸው ያወጁለትን የናዝሬቱ ኢየሱስን እንደአዳኝና እንደጌታ የተቀበልን እኛ አሁን ካለችው ኃጢያተኛና ጠፊ አለም ጋር እንዳናብር የዳንበት ሕይወት ያስገድደናል። ያኔ በእምነት የኖህ ልጆች መሆናችን ይገለጣል።
ኤፌሶን 2
----------

 ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
 ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
[1] እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

ነገር ግን ኖህ የዳነው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

## 4. የአብርሀም መንገድ

በአዲሳት መጽሐፍ እነደ ታላቅ የእምነት ሰው ከብሉያት መጽሐፍት በምሳሌነት የተወሰደ እንደ አብርሃም ያለ ሰው አናገኝም። አባታችን አብርሃም ጽድቅን በተቀበለበት በዛ መንገድ ዛሬ እኛም የምንጸድቅ መሆኑን ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ያውጃል። ክርስትና በኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ መሆን እንደ

አዲስ የጀመረ ብቻ ሳይሆን ቀድሞ በነበሩ አባቶች ዘመንም በተስፋ የተሰበከ እንሆነ ሐዋሪያት ያስተምሩናል(ሮሜ 1፥1-4,ገላ 3፥8)። አብርሃም የጸደቀበትን(የዳነበትን) መንገድ መጽሐፍ እምዲህ በማለት ይገልጸዋል

ሮሜ 4
----------

[2] አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።
[3] መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።
[4] ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤
□ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።

ይህ ክፍል የሚያስረዳው በወንጌል እየተነገረ ያለው "መጽደቅ በእምነት ነው እንጂ በመልካም ስራና በሕግ ስራ አይደለም" የሚለው አስተምሮ እንደ ኦሪት ሕግ መሰረት ስህተት ነው ብለው ለሚያስቡ አይሁዶች ስለዚህ የብርሃን እውነት ከኦሪት ሕግ የተሰጣቸው ማረጋገጫ ነው። አይሁዶች በስጋ የአብርሃም ልጆች ናቸውና እጅግ በጣም የሚመኩበትና የማይደራደሩበት አባታቸው ነው(ፊሊ 3፥1-12)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን ታላቅ የድነት መንገድ የዕብራውያን ምንጭ ከሆነው ከአብርሃም የመዳን መንገድ ዋቢ አድርጎ ያቀርብላቸዋል። አባታችኝ አብርሃም ነው ለምትሉ እስቲ አብርሃምን ተመልከቱ እንዴት እንደዳነ? ዛሬም ሰዎችን ሁሉ የምንጠራው አብርሃም ባመነበት እምነት እንዲያምኑ ነው። እስኪ ወደ አብርሃም እንመለስ

ዘፍጥረት 15
----------

[4] እነሆም፥ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል መጣለት፦ ይህ አይወርስህም፤ ነገር ግን ከጒልበትህ የሚወጣው ይወርስሃል።
□ ወደ ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት፥ ከዋክብትንም ልትቈጥራቸው ትችል እንደ ሆነ ቍጠር አለው። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው።
□ አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።
□ ይህችን ምድር ትወርሳት ዘንድ እንድሰጥህ ከከለዳውያን ዑር ያወጣሁህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ አለው።
□ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንድወርሳት በምን አውቃለሁ? አለ።
□ እርሱም፦ የሦስት ዓመት ጊደር፥ የሦስት ዓመት ፍየልም፥ የሦስት ዓመት በግም፥ ዋኖስም፥ ርግብም ያዝልኝ አለው።
[1□] እነዚህንም ሁሉ ወሰደለት፥ በየሁለትም ከፈላቸው፥ የተከፈሉትንም በየወገኑ ትይዩ አደረጋቸው፤ ወፎችን ግን አልከፈለም።
[11] አሞራዎችም በሥጋው ላይ ወረዱ፥ አብራምም አበረራቸው።
[12] ፀሐይም በገባች ጊዜ በአብራም ከባድ እንቅልፍ መጣበት፤ እነሆም፥ ድንጋጤና ታላቅ ጨለማ ወደቀበት፤
...

[1] ፀሐይም በገባች ጊዜ ታላቅ ጨለማ ሆነ፤ የምድጃ ጢስና የእሳት ነበልባል በዚያ በተከፈለው መካከል አለፈ።
[1] በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳን አደረገ፦ ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ፤

እግዚአብሔር ለአብርሃም ታላቁን ወንጌል በሰበከለት ጊዜ አብርሃም ካመነ በኃላ ግን እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ጥያቄ ፈጠረበት። ዛሬም መዳን በክርስቶስ ላይ ባለ እምነት ብቻ ነው ብለን ስናውጅ እንዴት? የሚል ጥያቄ ይፈጠርባቸዋል። እንደምወርስ እንዴት አውቃለው ሲል እግዚአብሔር ለአብርሃም ያስተማረው ትምህርት ነው "የጸጋ አስተምሮ" የሚባለው።በመጀመሪያ ግን አብርሃም ይመጣል ብሎ ያመነው ዘር ማነው? የሚለው ጥያቄ ይመለስ

ገላትያ 3
-----------

 መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፦ በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ።
...
[1] ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፦ ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፦ ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ።

ሁሉም ቅዱሳት መጽሐፍ በመስማማት ስለክርስቶስ ብቻ ሲናገሩ ስናይ ልባችን እርፍ ይላል። ይህን ያበራልን አምላክ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን አሜን። አብርሃም ገና በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ከጌታችን በስጋ መምጣት 2000 አመት በፊት ላይ እግዚአብሔር ከአንተ ውስጥ የሚያወርስ ዘር አመጣለው ሲለው አብርሃም ክርስቶስን ከሩቅ እንደሚመጣ በእምነት አይቶ አሜን ሲል ያህ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት። ዛሬም አብርሃም 2000 አመት ወደፊት አይቶ በእምነት በጸደቀበት መንገድ እኛም 2000 አመት ወደ ኃላ በማየት ክርስቶስ በሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ላይ ባለ እምነት እንጸድቃለን። ግን እንዴት በእምነት ብቻ? ምንም ሳንሰራ እንዴት ልንድንና ልንወርስ እንችላለን? የሚለው ጥያቄ የአብርሃምም ጥያቄ ነበር

“አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንድወርሳት በምን አውቃለሁ? አለ።”
— ዘፍጥረት 15፥8

ለዚህ ጥያቄ እግዚአብሔር ለአብርሃም የመስዋዕት እንስሳት አዘጋጅና እኔ እንዴት እንምትወርሳት አሳይሀለው አለው። አብርሃምም አዘጋጀና እንስሳቶቹን ሁለት ቦታ ከፍሏቸው ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ሊያደርግ ይጠብቀው ጀመር። እግዚአብሔር ግን ከአብርሃም ጋር በአንድነት አይደለም ይህንን ኪዳን የሚያጸናው ብቻውን ይህንን ኪዳን ይፈጽመውና አብርሃምን ይባርከዋል።እግዚአብሔርም በአብርሃም ላይ ከባድ እንቅልፍ ይጥልበትና በሚያስፈራ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጥሎት ኪዳንኑ ብቻው ገባ። ማለትም እኛ በበደላችንና በኃጢያታችን ሙታንና በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በነበርን

ሰአት እግዚአብሔር ራሱ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ሰውቶ እንደታረቀን ማለት ነው(ኤፌ 2፥1-5,ኤፌ 5፥8,ሮሜ 5፥6-11)።

ኤፌሶን 2
-----------

4 ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥
 ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥

ቲቶ 3
-----------

4 ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥
 እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤
- ያን መንፈስም፥ በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን፥ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው።

## 5. የእስራኤላውያን የድነት መንገድ

ለዕብራዊው አብርሃም እግዚአብሔር አምላክ በሕልም በተናገረው መሰረት (ዘፍ 15፥13-16) የእስራኤል ልጆች በዮሴፍ አማካይነት ወደ ግብጽ ወረዱ።የእስራኤል ልጆች በግብጽ ለ 430 አመታት ከቆዩ በኃላ የግብጽ ንጉስ ፈረኦን ከጊዜ ወደ ጊዜ መከራውንና ጭቆናውን እየጨመረ ይሄድ ነበር። የእስራኤል ልጆች ጭሁትም ወደ አባቶቻቸው አምላክ ደረሰ(ዘጸ 2፥23-24)።በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር በዘመን መጨረሻ የሚደረገውን የማዳን ስራ በምሳሌ ይገልጥ የጀመረው።

- **ታላቁ መስፍን ሙሴና ድንቋ በትር**

እግዚአብሔር አምላክ ለ 430 አመታት በግዞትና በጭቆና የተያዘውን የእስራኤል ሕዝብ ከጭቆና ለማውጣት አንድ መስፍን እንዲወለድ አደረገ። ይህም መስፍን ሙሴ ይባላል። በዕብራይስጥ ሙሴ የሚለው ቃል ማውጣት የሚል ትርጉምን የያዘ ነው።ሙሴ በተወለደ ወራት የግብፅ ንጉስ ፈረኦን ከእስራኤል የሚወለዱ ወንዶች ልጆች ሁሉ ይሙቱ የሚል ትእዛዝ አውጥቶ ነበር። እግዚአብሔር በድንቅ መንገድ ያንን ታላቅ መስፍን ከፈረኦን እጅ በማዳን በተአምራት አሳደገው።ከዚያም በቅዱሱ ተራራ በግዞት የተጨቆነውን ሕዝብ ነፃ እንደሚያወጣ በመናገር ያበረታው ጀመር።

ይህን ታሪክ ስናጠና የእግዚአብሔርን ልብ ካገኘነው እያወራን ያለው ወደ ፊት የሰውን ልጆች ከኃጢያትና ከጨለማው አለም አለቆች ነጻ ስለሚያወጣው እውነተኛ መስፍን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ከብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነብይ ከሚልኪያስ በኃላ እግዚአብሔር አምላክ ለ 430 አመታት ገደማ በምንም

አይነት መገለጥ ሳይታይና ነብያትንም ለሕዝቡ ሳይልክ ዝም ያለበት ወቅት ነበር። ይህም በሁለቱ ኪዳናት መካከል ያለ ዘመን (Inter testamental period) በመባል ይታወቃል።በዚህ ወቅት የሰማይ መስኮቶች የተዘጉበትና እግዚአብሔርም ዝም ያለበት ወቅት ነበር።ለምን? ቢባል የእስራኤል ሕዝብ ግብጽ ከገባ ከ 430 አመት በኃላ እግዚአብሔር ታላቁን መስፍን ሙሴን ነፃ እንዲያወጣቸው እንደላከው እንዲሁ እግዚአብሔር ለአይሁድ የመጨረሻውን ነብይ ከላከበት 430 አመታት በኃላ እውነተኛውን ነጻ አውጪ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚልክበት ጊዜ ስለደረሰ ነው።

"ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛው(አማናዊው) እና የአዲስ ኪዳኑ ሙሴ ነው።"

“ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ እኔ ጽፎአልና።”
— ዮሐንስ 5፥46

ወደ አዲሱ ኪዳን ስንመለስ ከ 430 አመታት የዝምታ ጊዜ በኃላ በይሁዳ ቤተልሄም ታላቅ መስፍን መወለዱን መላእክታት(ለቃ 2፥9፥14) እና የሰማይ ኮከቦች (ማቴ 2፥1-2) ይመሰክሩ ጀመረ። ስሙ ደግሞ ኢየሱስ ይባላል። ኢየሱስ የሚለው ቃል በግሪኩ ሲሆን አዳኝ ወይም መድኃኒት የሚለውን ቃል ይተካል። ይህ ሕጻን በተወለደ ጊዜ የይሁዳ ገዢ ሄሮድስ ወንድ ሕጻናት ሁሉ እንዲገደሉ አዘዘ። እግዚአብሔር ግን ኢየሱስን በተአምራት አስመልጦት በድንቅ አሳደገው። ኢየሱስንም በቅዱሱ ተራራ ላይ እግዚአብሔር በታላላቆቹ ነቢያት በኩል ስለኃጢያተኞች እንደሚሞትና በትንሳኤው ሀይልም ሰዎችን ከኃጢያትንና ከዚህ አለም አለቆች እጅ ነጻ እንደሚያወጣቸው ተነገረው(ሉቃ 9፥30-31, ሜቴ 17፥1-9)።ይህ ሁሉ ታሪክ የተመዘገው በማቴዎስ ወንጌል ሲሆን ሙሴ ከተራራው በወረደ ጊዜ እስራኤልን ከግብጽ ለማውጣት 10 የሚደርሱ ተአምራትን አደረገ(ዘፀ 7-11)፤ አማናዊው ሙሴ ኢየሱስ እንዲሁ ከተራራ በወረደ ጊዜ 10 ተአምራትን አደረገ( ማቴ 8-9)።

የብሉይ ኪዳኑ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች በሕግ መንገድ መጣ፤ የአዲስ ኪዳን አዳኝ ጸጋን ተሞልቶ መጣ(ዮሐ 1፥17)። በዚህም ምክንያት የብሉይ ኪዳኑ ሙሴ አልወረሰም አላስወረሳቸውም፤ የአዲሱ ኪዳን አዳኝ ግን በሁሉ ተፈትኖ አልፎ ወርሶአልና በርግጥም ያስወርሰናል(ዕብ 1፥2-3,ዕብ 6፥20,ሮሜ 8፥17)።ምንም እንኳን ሙሴ የኢየሱስ ምሳሌ ቢሆንም በፍፁምነት ግን አይተካውም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ የሚበልጥና የሚያስወርስ መስፍን ነው። ዕብ 3፥1-12

የእስራኤል ሕዝብ የዳነበትና ከፈረኦን እጅ ነጻ የወጣበት መንገድ ሙሴ ይባላል እንዲሁ ሰዎች ከኃጢያትና ከጨለማው አለም አለቆች የምንድነውና ነጻ የምንወጣው በአንዲ መንገድ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው(ሐዋ 4፥12, ዮሐ 14፥6, ቆላ 1፥13)።በእርግጥም በኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የሚመጣ አያፍርም(ሮሜ 10፥11, 1 ጴጥ 2፥6)።

ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ለማዳን አንዲት በትር ብቻ ይዞ እንደመጣ ኢየሱስም

እንዲሁ ሰዎችን ለማዳን አንዲትን ስራ ብቻ ይዞ መጣ። ኢየሱስ ይዞ የመጣውን ስራ እስኪ ከዛች ብትር ምሳሌነት እንመልከት
ዘጸአት 4
----------

2 እግዚአብሔርም፦ ይህች በእጅህ ያለችው ምንድር ናት? አለው። እርሱም፦ በትር ናት አለ።
3 ወደ መሬት ጣላት አለው፤ እርሱም በመሬት ጣላት፥ እባብም ሆነች፤ ሙሴም ከእርሷ ሸሸ።
4-5 እግዚአብሔርም ሙሴን፦ የአባቶቻቸው አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ፥ እግዚአብሔር እንደ ተገለጠልህ እንዲያምኑ እጅህን ዘርግተህ ጅራትዋን ያዝ አለው። እጁንም ዘርግቶ ያዛት በእጁም ውስጥ በትር ሆነች።

ሙሴን ያምኑበት ዘንድ የተሰጠው ምልክት ይህ ነው። ያቺ በትር ወደ መሬት ትወድቃለች እባብም ትሆናለች እንዲሁ ክርስቶስ ስለኃጢያታችን በውርደት ይያዛል ይናቃል እንደ እባብም ይሰቀላል(ዮሐ 3፥15) በምድር ሆድ ውስጥ ለ 3 ቀናት ይቆያል ሙሴ ብትሩአን እንዳነሳት እግዚአብሔርም የሞትን ጣር አጥፍቶ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሳዋል(ሐዋ 3፥15,ሮሜ 8፥11,ገላ 1፥1)። ክርስቶስ እናምንበት ዘንድ ይዞ የመጣው የከበረ ስራ ይህ ነው(1 ቆሮ 15, ዮሐ 12፥27)።

የእስራኤል ሕዝብ የዳነው በሙሴና በያዛት በትር እንደሆነ የሰው ልጅም ድነትንና ዋስትናን የሚያገኘው በእግዚአብሔር ልጅና በመስቀል ላይ በሰራለት ክቡር ስራ ብቻ ነው።

- **ፋሲካ የመዳን ምክንያት**

እግዚአብሔር አምላክ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ለማውጣት በሙሴ እጅ ወደ 9 የሚደርሱ ተአምራትን አድርጎ ፈረኦን ግን ፈጽሞ ሊለቃቸው አልቻለም።ይህ እውነት ትልቅ መገለጥን የተሸከመ ነው። እግዚአብሔር እንዲሁ በክርስቶስ ኢየሱስ እጅ በስጋው ወራት ብዙ ተአምራትን አድርጎአል። ነገር ግን በእውነተኛው ፋሲካ እንጂ መሲሁ በፋሲካ ወራት ባደረገው ድንቅና ተአምር ማመን ከኃጢያትና ከሞት ሊያድነን አይችልም(ዮሐ 223-24)።

እግዚአብሔር አምላክ ለእስራኤል ልጆችና ዛሬ ላለን ሰዎች የትኛውም ከተፈጥሮ አቅም በላይ የሆነ ድንቅና ተአምር ለሰው ልጆች ድነትን ሊሰጥ እንደማይችል በግልጽ ካወጀ በኃላ ታላቁን የመዳን መንገድ ማሳየት ይጀምራል።
ዘጸአት 12
----------

1 እግዚአብሔርም በግብፅ አገር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦
2 ይህ ወር የወሮች መጀመሪያ፤ የዓመቱም መጀመሪያ ወር ይሁናችሁ።
3 ለእስራኤል ልጆች ሁሉ ተናገሩ፥ በሉአቸውም፦ በዚህ ወር በአሥረኛው ቀን ሰው ሁሉ ለአባቱ ቤት አንድ ጠቦት፥ ለአንድ ቤትም አንድ ጠቦት ይውሰድ።

…
 የእናንተ ጠቦት ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ተባት ይሁን፤ ከበጎች ወይም ከፍየሎች ውሰድ።
 በዚህም ወር እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ጠብቁት፤ የእስራኤልም ማኅበር ጉባኤ ሁሉ ሲመሽ ይረዱት።
 ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበኑን ይቅቡት።
…
 ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ፥ ነገር ግን ከራሱ ከጭኑ ከሆድ ዕቃው ጋር በእሳት የተጠበሰውን ብሉት።
…
13 ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ፤ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።

ይህ የእግዚአብሔር ፋሲካ የተባለው ለእስራኤል ልጆች ከግብፅ መውጣትና ለነጻነታቸው መጀመሪያ ነው፤ ማለትም ከዚህ በፊት በግብጽ ውስጥ የኖሩበት ወራትና አመታት ለዚህ አለም ገዢ የኖሩበትና የሰሩበት ነውና አንዳችም ከእርሱ ጋር ሕብረት እንዳይኖራቸው ወራት ሲቆጥሩ ከፋሲካ ጀምረው፤ የአመታቸውም ጅማሬ የታረደው በግ እንዲሆን ከሰማይ ይታዘዛሉ። ሰማይ ከግብጽ ለመውጣት የሚሻ ሁሉ አንድ በግ ማረድና ደሙን በመቃኑና በጉበኑ ላይ መቀባት እንዳለበት ያዛል። ከዛ ደም የተነሳ ፍርድ ወደ እነርሱ ቤት እንደማይገባ ተናገራቸው። የሚያርዱት በግ ንጹህና ነውር የሌለበት እንዲሆንም ታክሎ ታዘዙ።ይሄ በግ የሚታረድበት ጊዜ ምሽት ይሁን ደሞ ፈጽመው ጥሬውንና የተቀቀለውን እንዳትበሉ የተጠበሰውን እንጂ። ከዚያ ደም የተነሳ ጥፋት ወደ እናንተ አይመጣም አላቸው።

የእስራኤል ልጆች እንደተነገራቸው አድርገው ደሙን በጉበናቸውና በመቃናቸው ቀብተው፣ ከመጣው ፍርድ ድነው፣ ከግብጽና ከገዢው ከፈረኦን መንግስት አምልጠው ወደ ተዘጋጀላቸው መንግስት አመሩ።ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ወደ ፊት ሰዎች በእንዴት አይነት መንገድ እንደሚድኑ እየተናገረ ነበር።

በአዲሱ ኪዳን ፋሲካ የሆነ ቀን ሳይሆን ማንነት ሆኖ ተገለጠ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው(1 ቆሮ 5፥7, ቆላ 2 ፥16-17)። እርሱ እንከንና ነውር አልባ ተባእት የሆነ የእግዚአብሔር በግ ነው( ዮሐ 1፥29, ዕብ 7፥26, ኢሳ 9፥7)። በእውነትም እንከንና ነውር አልባው የእግዚአብሔር በግ በመስቀል ላይ ታረደልን በፈሰሰውም ደሙ ከእግዚአብሔር ቁጣ አዳነን ከጨለማውም መንግስት ነፃ አውጥቶን በፍቅር ወደ ተሞላው መንግስት አፈለሰን(ሮሜ 5,ቆላ 1፥13)። ማንም መዳን የሚፈልግ ቢኖር እንደቆመ ተአምራት የሚያደርገውን ኢየሱስን ሳይሆን ስለኃጢያታችን በመስቀል ላይ በእግዚአብሔር የፍርድ የቁጣ እሳት የተጠበሰውን በግ ስጋና ደም መብላት(ማመን) አለበት(ዮሐ 6፥35-51)። ያህ በግ በውርደት ሲታረድ ጸሐይ ጠልቆ በምሽት ነበር(ማቴ 27፥15)። ያህ ደም ለቀቡት(ላመኑበት) ሁሉ ዋስትናቸው ይሆናል። የአማኞችም ታሪክ ጅማሬ ይህ የቀራንዮ በግ ፋሲካችን ይሆናል(2 ቆሮ 5፥13-17)።

የእስራኤል ልጆች ከመጣው ፍርድ ያመለጡት ራሳቸውን ከሌላው እስራኤላዊ አውዳድረው የተሻሉ በመሆናቸው ሳይሆን በጉበንና በመቃናቸው ላይ የተቀባው ክቡር ደም ነው። ዛሬም ከታላቁ የኃጢአት ፍርድ አምልጠን የምንድንበት መንገድ ከእኛ ውስጥ በሚወጣ መልካምነት ሳይሆን በመስቀል ላይ በድካም በተዘረረው በቅዱሱ በእግዚአብሔር ልጅ ደም ነው።እስራኤልን ከንቱና ትርፍ ከሌለው ከግብጽ ኑሮ የዋጃቸው ደሙ ነው።

“ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ።”
— 1ኛ ጴጥሮስ 1፥18-19

ይህ የፋሲካ ክብረ በአል ለእስራኤል ልጆች የዘላለም ማስታወሻ ይሆንላቸው ዘንድ በየአመቱ እንዲያከብሩት ታዘዙ።ለእኛ ግን ፋሲካችን የሆነውን ክርስቶስን ሁልጊዜ እንድንመለከተው እግዚአብሔር ከፊት ለፊታችን እንደታረደ አድርጎ አኖረው።ዛሬ ግን በተለያዩ ሰው ሰራሽ አስተምሮዎችና በሰው ስርዓት አይናችን ደብዝዞ ማየት አቃተን።(ገላ 3፥1-2)።ያንን በድካም በፊት ለፊታችን የተሰቀለውን የእግዚአብሔር በግ ማየት ለሁለንተናችን ፈውስ ነው።

"ቅዱስ አባት ሆይ አይኖቻችንን የአይንህ ማርፊያ ወደ ሆነው ወደ ታረደው በግ መልስልን።"

## ➢ የድነት መንገድ በመገናኛው ድንኳን(በአምስቱ መስዋዕቶች)

እግዚአብሔር አምላክ ታላቁን የመዳን መንገድ ማወጅ በዚህም አላበቃም።የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ ከወጣ በኃላ በምድረበዳም ሳለ ከግብፅ የወጡበትን መንገድ እንዳይረሱና ለዘላለም ወደ እርሱ የሚቀርቡበትን መንገድ በተለያዩ የመስዋህት አይነቶች ያስተምራቸዋል። ያዕቆብ የሚወደውን ልጁን ዮሴፍን በቀለማት ያሸበረቀ ልብስ እጀ ጠባብ አለበሰው(ዘፍ 37)፤ ወንድሞቹ ዮሴፍን በተለያየ አቅጣጫ ሲመለከቱት የተለያየ ቀለምን ይመለከቱ ነበር።በእግዚአብሔር አብ የተወደደው ከሰማይ ማረጋገጫና ማዕተም የተደረገበት አማናዊው ዮሴፍ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።(ማቴ 3,ሉቃ 3)።ምንም እንኳን ወንድሞቹ ባይቀበሉትም የኃላ ኃላ ግን ተስፋ በቆረጡ ጊዜ መሸሸጊያቸው ሆኖአል እንዲሁ ባለማወቅ እየጠላነው ሸጥነውና እንዲሰቀል አሳልፈን ሰጠነው የኃላ ኃላ ግን ራሱን ገልጦልን መሸሸጊያችን ሆኖአል። እንግዲህ አንዱን ኢየሱስን እግዚአብሔር በቃለማት ያሸበረቀ ልብስ አልብሶታል(ዕብ 2፥7)። ማለትም አንዱ ኢየሱስ ብዙ ነገራችን ሆኖአል።

"ከሚወደው አባቱ ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችን፣ ቅድስናችን፣ ቤዛችን፣ ንጉሳችን፣ የመስዋህት በጋችን፣አምላካችን፣ስብከታችን፣ ጌታችን፣ ተስፋችን፣በረከታችን፣ የሚመጣው ፍጻሜአችን .... በእነዚህ ሁሉ ቀለማቶች ያሸበረቀው አማናዊው ዮሴፋችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"

የእስራኤል ልጆች በምድረበዳ ሳሉ እግዚአብሔር ወደ እርሱ የሚቀርቡበትን መንገድ በአምስት መስዋዕቶች ደንግጎላቸዋል(ዘሌ 1-7)።እነዚህ የመስዋዕት አይነቶች አንዱ ክርስቶስን በተለያየ አቅጣጫ የሚያሳዩን ናቸው።

**+ ክርስቶስ የሚቃጠል መስዋዕታችን (ዘሌ 1፥3-17 ,ዕብ 13፥11-12)**
ይህ የመስዋዕት አይነት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ማምጣት ያለባቸው መስዋዕት ነው።ማቅረብ ያለባቸውን የእንስሳት አይነት ይነግራቸውና የሚያመጣው ሰውዬ እጁን በእንስሳው ላይ ይጫን፤ በሰውዬውም ኃጢያት ምክንያት የእግዚአብሔር ቁጣ በበጉ ላይ ይሆናል።በጉ አንዳች ሳያጠፋ እስራኤላዊው ላጠፋው በምትክነት ይቃጠላል። እሳት በቅዱሳት መጽሐፍት መሰረት የእግዚአብሔር ፍርድ ምሳሌ ነው(ዘሌ 10፥1-2, ማቴ 3፥12,ማቴ 13፥30)።የሰው ልጆች ሁሉ በኃጢያታቸው ምክንያት መሞት ሲገባቸው(ሮሜ 6፥23) ግን እግዚአብሔር ልጁን ልኮ በምትክነት(በቤዛነት) ፍርዱን እንዲቀበል አድርጎ መዳኛ መንገድ አዘጋጀ(ሮሜ 3፥24,ኤፌ 1፥7,1 ጢሞ 2፥6)። በእርግጥም ኢየሱስ ክርስቶስ የሚቃጠል መስዋህታችን ነው(ዕብ 13፥11-12)።

ዕብራውያን 13
----------

11 ሊቀ ካህናት ስለ ኃጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም ያቀርባልና፤ ሥጋቸው ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል።
12 ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።

በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በፍጹም አይፈረድበትም ምክንያቱም ክርስቶስ እርሱ ስለእኛ ተፈርዶበታልና(የሚቃጠል መስዋዕት ሆኖአልና) (ዮሐ 3፥17-18,32 , ዮሐ 5፥24)።

**+ክርስቶስ የእህል ቁርባን መስዋዕታችን(ዘሌ 2፥1-16 , 1 ቆሮ 5፥8)**
ይህ የመስዋዕት አይነት ከዱቄት የሚዘጋጅ፣ ያለእርሾና ያለማር ተጋግሮ በዘይት የሚለወስና በጨው የተቀመመ ፣ ለእግዚአብሔር አምላክም ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት ነው። ዱቄቱ የሚገኘው ከስንዴ ነው ያ ስንዴ ደግሞ ክርስቶስ ነው(ዮሐ 12፥24)።ስንዴው ተፈጭቶ ዱቄት እንደሚሆን እንዲሁ ክርስቶስ ስለበደላችን ደቀቀ(ኢሳ 53፥5)።ዱቄቱ በዘይት ተለውሶ ያለእርሾ በእሳት ይቃጠላል እንዲሁ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስና በሀይል ተቀብቶ(ሐዋ 10) ያለኃጢያት የሆነ ንጹህ(ያለእርሾ 1 ቆሮ 5፥8) በእግዚአብሔር ፍርድ ተጠበሰ። ይህንንም ቁርባን ካህኑ ወደ እግዚአብሔር ፊት ይዞ ይገባል።በክርስቶስ ንጹህ የመስዋህትነት ስራ ደካሞችና አቅመቢሶች ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረብ ድፍረት ያገኛሉ( ኤፌ 2፥18,3፥12,ዕብ 9፥24,10፥19-20)።

ነገር ግን ማንም በዚህ መስዋህት ላይ እርሾ ወይም ማር እንዳይጨምር ማለትም በክርስቶስ ኢየሱስ ንጹህ መስዋህት ላይ ድካሙንም(እርሾ) ይሁን (1 ዮሐ 2፥1-2)፤መልካም ስራውን(ማር ኢሳ 64፥6 ) እንዳይጨምር። የትኛውም ሰው በዚህ መስዋዕት ላይ ድካሙንም(እርሾ) ጨምሮ እጠፋለው ብሎ እንዳያስብ ደግሞም መልካም ስራውንም(ማሩንም) ጨምሮ እድናለው ብሎ

እንዳያስብ የቀረበው መስዋህት በጨው ብቻ(በጸጋ ቆላ 4፥6) የተቀመመ ይሁን ይላቸዋል።ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛውና ንጹህ ወደ እግዚአብሔር አብ መግቢያው መንገዳችን ነው።

**+ክርስቶስ የሕብረት መስዋዕታችን (ዘሌ 3፥1-17 , ሮሜ 5፥10-11,ቆላ 1፥20)**
ይህ የመስዋዕት አይነት ደግሞ ሌላኛው ስሙ የሰላም መስዋዕት(peace offering) የሚባለው ነው።ሰው በኃጢያቱ ምክንያት የእግዚአብሔር ጠላት በመሆኑ ምክንያት እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር እንደገና ሕብረት ማደሻን(ሰላም መፍጠሪያን) መስዋዕት ለእስራኤላውያን ያስተዋውቃቸዋል። ይህ መስዋዕት ከእንስሳት ወገን እንከን የሌለበት ተመርጦ ኃጢያተኛው እስራኤላዊ እጆቹን በበጉ ላይ በመጫን ፍርዱን ሁሉ ወደ ንጽሑ በግ ይተላለፍና በንጽሑ በግ ሞት ኃጢያተኛው ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ ሰላሙ ይመለሳል።

እንዲሁ ንጹህ በግ ክርስቶስ በኃጢያተኛው ፈንታ በመሞት ኃጢያተኛውን ከአምላኩ ጋር ያስታረቀ የዕብረት መስዋዕታችን ነው።

“ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤”
— ሮሜ 5፥10

ከእግዚአብሔር አብ ጋር የዘላለም ሕብረት ውስጥ መግባት የሚቻለው እርቅን ባገኘንበት በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።በልጁ ደም በኩል ከአብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሕብረት አለን(1 ዮሐ 1፥3-4, 2 ቆሮ 13፥14)።

**+ክርስቶስ የኃጢአት መስዋዕታችን(ዘሌ 4፥1-5፥13 , ሮሜ 8፥3,ኢሳ 53፥10)**
ይህ የመስዋዕት አይነት አንድ እስራኤላዊ አምላኩ እግዚአብሔር አታድርጉ ብሎ ካዘዛቸው ትእዛዛት ባለማወቅ ተላልፎ ቢገኝ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው የመስዋዕት አይነት ነው። ቅዱሳት መጽሐፍት በቀጥታ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት መስዋዕታችን እንደሆነ ያስተምራሉ(ሮሜ 8፥።3)። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢያት የሰራው እስራኤላዊ አንድ ንጽህ በግ ያመጣና እጆቹን ጭኖ በምትክነት እንዲሞት አሳልፎ ይሰጠዋል። እንዲሁ ክርስቶስ ከሰማይ የአለምን ሁሉ ኃጢያት ሊሸከም የኃጢያት መስዋዕት ሆኖ ተገለጠ።እርሱ እንከን የለሹና ፃድቁ ሰው በኃጢያተኛው ምትክ ኃጢያት ሆነ። እርሱ ኃጢያተኛ ሳይሆን እራሱ ኃጢያት ሆነ(2 ቆሮ 5፥21)። ምክንያቱም የኃጢያተኛ ሳይሆን የኃጢያት ደሞዝ ሞት ነውና(ሮሜ 6፥23)።

እርሱ ንጹህ ሆኖ ሳለ የአለምን ኃጢያት በመሸከሙ ከበር ውጭ መከራን ይቀበል ዘንድ ተገደደ። ነቀፎታችን ቆሻሻችንን ሁሉ በመስቀሉ ሞት አስወገደ። የዲያቢሎስን ስራ እሱም ኃጢያትን ያፈርስ ዘንድ ወደ መስቀል ወጣ። "ክርስቶስ የኃጢያት መስዋህታችን ሆኖአል" ስንል በእርሱ ደም በኩል ዘላለማዊ የኃጢአት ይቅርታን አግኝተናል እያልን ነው(ኤፌ 1፥7)። ከእንግዲህ ወዲህ የትኛውም ኃይል ስለ ኃጢያት ሊከሰን አይችልም ምክንያቱም ክርስቶስ የኃጢያት መስዋዕታችን ሆኖአልና(ሮሜ 8፥1-4, 1 ዮሐ 2፥1-2)።

መዳን የሚገኘው በኃጢያት ስርየት በኩል ነው። የኃጢያት ስርየት ደግሞ በኃጢያት መስዋዕት በኩል ነው። የኃጢያት መስዋዕታችን ደግሞ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።ስለዚህ መዳን የሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

“መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።”
— ሐዋርያት 4፥12

**+ክርስቶስ የበደል መስዋዕታችን(ዘሌ 5፥14-6፥7,ኢሳ 53፥5)**
ይህ የመስዋዕት አይነት ደግሞ እስራኤላዊ ባለእንጀራውን በበደለ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚሰዋው ነው። ኃጢያት በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ሲሆን በደል ደግሞ በሰው ላይ የሚፈጸም ነው(ማቴ 6፥12)። በተዘዋዋሪ የበደልም ጠያቂ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር አምላክ ጻድቅ ፈራጅ በመሆኑ ማንም ቢሆን በባለንጀራው ላይ በደል ቢፈጽም የእግዚአብሔር ቁጣ ትነዳለች(ዘፍ 4፥11-12)። ክርስቶስ ከሰማይ የመጣው ለኃጢያታችን ብቻ ሳይሆን በደላችንንም ከእኛ ሊያርቅ ነው።ክርስቶስ የሰጠን ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ጠላትነት የሚያስወግድ ብቻ ሳይሆን ሰዎችንም በእግዚአብሔር ፍቅር እንድንወድ የሚያደርገን ነው(1 ዮሐ 3፥14-15)።

ይህን እውነት ከክርስቶስ ሐዋሪያት እንማራለን።ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋው ወራት ከጠራቸው ሐዋሪያት አንዱ ቀራጩ ማቴዎስ ነው(ማቴ 9፥9)። ይህ ሰው አይሁዳዊ ቢሆንም ግን በዘመኑ አይሁዶችን ሲገዙ ከነበሩ ሮማውያን ጋር በማበር እስራኤላውያንን በቀረጥ ያሰቃይ ነበር። ቀረጥ ሰብሳቢዎች ከተባሉት በላይ ሕዝቡን ገንዘብ እየጠየቁ ስለሚያሰቃዩ "የኃጢያተኞች" ምሳሌ ነበሩ። በተቀራኒው ደሞ ቀናተኛው ስምኦን የሚባለው ሌላ ሐዋሪያ ደግሞ ከቀናተኞች መካከል የተጠራ ነው። እነዚህ ቀናተኞች የአይሁድ መብት ተካራካሪዎች ሲሆኑ አብዝተው ሮማውያንን የሚጠሉ ነበሩ።ከዚያ አልፈው በጫካ ሸምቀው ሮማውያንን እና ከሮም መንግስት ጋር የሚያብርን ሁሉ የሚገድሉ ነበሩ። ከእነዚህ መሀል የኢየሱስ ሐዋሪያ ቀናተኛው ስምኦን አንዱ ነው(ማቴ 10፥4)። ቀራጩ ማቴዎስ ከሮም መንግስት ጋር በማበር ስለሚሰራ የቀናተኛው ስምኦን ጠላት ነበር። ነገር ግን እነዚህ ለመገዳደል የሚፈላለጉ ሰዎች በአንድ ማዕድ ዙሪያ ተቀመጡ(ሉቃ 22፥14)። የዚህ ምክንያት ደሞ የበደል መስዋዕታችን የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እርሱ በደሙ በኩል ከአብ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ጋር አስታርቆናል። መጽሐፍ እግሮቻችን ደም ለማፍሰስ የፈጠኑ እንደነበሩ(ሮሜ 3፥15 ሰዎችን ለማጥፋት የሚሮጡ) እና አሁን ግን የምስራቹን ወንጌል ይዘው የሚሮጡ እንደሆነ ያስተምሩናል(ሮሜ 10፥15 ሰዎችን ለማዳን የሚሮጡ)። ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንኖር ዘንድ አንዱ ስለሁሉ ሞተ።ክርስቲያን የመብቱ ተከራካሪ አይደለም ራሱ እየተጎዳ ሌሎችን የሚጠቅም እንጂ። የዚህ ምክንያት ክርስቶስ የበደል መስዋዕታችን ስለሆነ ነው(ፊሊ 2፥4-5)። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ሰዎች ከብዙ አይነት ባህልና አስተሳሰብ የመጣን ስንሆን በክርስቶስ ደም በኩል እንደ አንድ አካል ተዋቅረናል።
“እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም

ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።”
— ኢሳይያስ 53፥5

- **ድነት በእባቡ ከመነደፍ በኃላ**

የእስራኤል ሕዝብ ከግብጽ በበጉ ደም በኩል ካመለጠ በኃላም እግዚአብሔር ስለድነታቸው መንገድ መመስከሩን አላቋረጠም። የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ በፉሲካው በግ ደም መንገድ ቢወጣም ዳግም ውልደትን ግን አላገኘም ነበር ማለትም አዲስ ፍጥረት አልሆነም ነበር። የዳግም ወልደት ሕይወት የተገለጠው አካል በሆነው በአዲስ ኪዳን ነውና(ዮሐ 3፥1፥10)። ያህ በትልቁ ምልክት ከግብጽ የወጣው ሕዝብ በኃጢያቱና በበደሉ የሞተ ስለሆነ ወይም ያመለጠው በውጫዊ ማንነቱ ስለሆነ ውስጣዊ ማንነቱ ግን በእግዚአብሔር ላይ ያምጽ ነበር። እግዚአብሔርም ጻድቅ ፈራጅ ነውና የከለላ እጁን በማንሳት የበረሃ እባቦች እንዲነድፋቸው አደረገ።

ዘኍልቁ 21
----------

 ሕዝቡም በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ፡- በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፥ ውኃ የለም፤ ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ ተጸየፈ ብለው ተናገሩ።
 እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፥ ሕዝቡንም ነደፉ፤ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ።

በእነዚህ ክፉ እባቦች ከተነደፉት ብዙዎቹ ሲሞቱ የቀሩት ደሞ ይሰቃዩ ነበር።በቅዱሳት መጽሐፍት ላይ እባብ የኃጢያት ምሳሌ ነው(ዘፍ 3)።አለም ሁሉ በኃጢያቷና በበደሏ የሞተችና የምትሰቃይ ነበረች(ኤፌ 2፥1)። እግዚአብሔር በኃጢያት እየሞተና እየተሰቃየ ያለውን ሕዝብ ለማዳን የተጠቀመበትን መንገድ እንመልከት

ዘኍልቁ 21
----------

 ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ። እግዚአብሔርም ሙሴን፡- እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል አለው።
 ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ፤ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየ ጊዜ ዳነ።

እግዚአብሔር በእባብ የተነደፈውን የእስራኤል ሕዝብ የናስ እባብ ሰርተህ በእንጨት ላይ ስቀል እባቡን የተመለከተው ሁሉ ይድናል የሚል መንገድን ሰጠው እንዳለውም ሆነ።ይህን ታሪክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንዲህ ይተረጉመዋል

“ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።”

— ዮሐንስ 3፥14-15
የእስራኤል ሕዝብ በእባብ ተነደፉና ሞቱ እንዲሁ የሰው ልጆች በኃጢያት ተነደፉና ሞቱ(ሮሜ 5፥12-13)። የእስራኤል የድነት መንገድ የነደፈውን የእባብ አይነት እራሱ መስቀል ነበር ወደእርሱም የሚመለከት ይድን ነበር።እንዲሁ ክርስቶስ ስለአለም ሁሉ ኃጢያት ሆኖ በመስቀል ላይ ዋለ ምክንያቱም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንደኖረው እንጂ እንዳይጠፋ።ሰዎች ከገቡበት የኃጢያት ጨለማ የሚድኑበት መንገድ ኃጢያት ሆኖ በመስቀል ላይ የተሰጣው የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው(2 ቆሮ 5፥21)።

- **ድነት በጽኑ ረሀብና ጥማት ውስጥ**

የእስራኤል ልጆች በጽኑ ምድረበዳ የተራቡና የተጠሙ የሆኑበት የሕይወት ስርዓት ሰዎች ያለክርስቶስ ኢየሱስ የሚኖሩበት ኑሮ ምሳሌ እንደሆነ ኢየሱስ ራሱ በዮሐንስ ወንጌል 6 ላይ ተናግሯል። ከዚህ ርሀብና ጥማት ያርፉ ዘንድ እግዚአብሔር የሄደበት መንገድ እጅግ ትልቅ ትምህርት ነው።እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለገቡበት ረሀብ ከሰማይ እንጀራን አውርዶ ጊዜአዊ ረሀባቸውን ገታ። እንዲሁ በዚህ ዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ለገቡበት የሕይወት ረሀብ አንድና ብቸኛ የሚወደውን ልጁን የሕይወት እንጀራ አድርጎ ላከ።እነዚህ ሰዎች ይህን እንጀራ ለማውረድ ያደረጉት አንዳች በጎ ነገር ሳይኖራቸው የእግዚአብሔር ና የሙሴ ጠላት ሆነው ሳሉ የመላእክት እንጀራ የሆነው መና ከሰማይ ተሰጣቸው።እንዲሁ አለም ሁሉ የእግዚአብሔር ና የልጁ ጠላቶች ሆነው ሳሉ እግዚአብሔር የዘላለምን ሕይወት እንጀራ ከሰማይ አወረደ። ይህ የአዲስ ኪዳኑ(አማናዊው) የሕይወት እንጀራ እንደብሉይ ኪዳኑ እንጀራ ተብልቶ የሚሞት አይደለም።ከዚህ እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል(ዮሐ 6)።

በጽኑ ጥማት ውስጥ ለገቡት የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲ አለው
“እነሆ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ፤ ዓለቱንም ትመታለህ፥ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው። ሙሴም በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት እንዲሁ አደረገ።”
— ዘጸአት 17፥6
ይህ አለት በተመታ ጊዜ ውሃ ፈሰሰ ሕዝቡም ጠጥቶ ረካ።በዚህ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን ትምህርት ከሐዋሪያው ጳውሎስ ስንቀዳ

1ኛ ቆሮንቶስ 10
----------

3 ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፥ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤
4 ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፥ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።

ሊታመን በማይችል መንገድ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ጥማት የሚያረካበትን መንገድ ሲናገር ከፊታቸው የቆመው ዓለት በተመታ ጊዜ ምንጭ ይፈልቃል ጠጥታችሁም ትረካላችሁ አላቸው ነገር ግን ከዚያ በኋላ እንደማይጠሙ ተስፋ አልተሰጣቸው።አሁን ግን አማናዊው አለት ተገልጦአል

እርሱም በመስቀል ላይ ተመቶአል በዛም ምክንያት ከእርሱ ጠጥተን ለዘላለም የማንጠማበት የሕይወት መንፈስ ተሰቶናል ከዚህ አለት ውሃ የሚጠጣ ግን ለዘላለም አይጠማም(ዮሐ 6)። በክርስቶስ መመታት ምክንያት ያገኘው እርካታ ዘላለማዊ ከመሆኑ የተነሳ ከእንግዲ ወዲህ መዳንን ጽድቅን የዘላለም ሕይወትን ፍለጋ አይታትርም አይደክምም። እርካታው በዚያ አለት ላይ የጸና ይሆናል።መዳን የሚገኘው በተሰቀለው ጌታ ብቻ ነው።

## 6. የአዛባዊቷ ረሀብ መንገድ

አህዛባዊቷ ረሀብ በእነርሱ ከተማ ላይ ከሚመጣው ጭፍጨፋና ከማይታዘዙት ጋር ያልጠፋችበትን  እና ያመለጠችበትን መንገድ እንመልከት እስቲ

“እነሆ፥ እኛ ወደ አገሩ በገባን ጊዜ ይህን ቀይ ፈትል እኛን ባወረድሽበት መስኮት በኩል እሰሪው፤ አባትሽንም እናትሽንም ወንድሞችሽንም የአባትሽንም ቤተ ሰብ ሁሉ ወደ አንቺ ወደ ቤትሽ ሰብስቢ።”
— ኢያሱ 2፥18

ረሀብ እንድታደረገው የነገሯት ነገር ቀይ ፈትል ወስደሽ በቤትሽ መስኮት ላይ አድርጊ ለጥፋት በመጣን ጊዜ የምትድኚው ያንን ቀይ ፈትል ካሰርሽ ብቻ ነው ያለዚያ ትጠፊያለሽ አሏት። እርሷም ያን ቀይ ፈትል በመስኮቷ ላይ በማድረግ ከጥፋት አመለጠች።ከሚመጣው ቁጣ የሚያድነን ያህ ቀይ ፈትል የክርስቶስ ሐምሳሌ ነው። በቅዱሳት መጽሐፍት ቀይ የደም ምሳሌ ነውና።የክርስቶስ ደም ከጥፋትና ከሞት ያመለጥንበት መንገዳችን ነው። እንግዲህ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ረሀብ በእምነት እንደዳነች ይናገራል(ዕብ 11፥31)። ዛሬም የሚዳነው ደሙ ላይ ባለ እምነት ብቻ ነው (ሮሜ 5፥9)።

አስደናቂው የመዳናችንን መንገድ ከብሉይ ቅዱሳት መጽሐፍት አንስተን ሁሉን ብንናገራቸው ጊዜም አይበቃንም።የሩትን ፣ የጌዲዮንን ፣የሳምሶንን ፣የዮፍታዬን ፣የግራኙ ናኦድን ፣የሳሙኤልን ፣ የዳዊትን፣ የእስራኤል ታላላቅ ነገስታትን ፣የካህናትንና የታላላቅ ነቢያትን የእያንዳንዱን የመዳን መንገድ

### ❖ የድነት መንገድ በአዲስ ኪዳን

የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፍት የሚያውጁት የድነት መንገት ከብሉያት የተለየ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ብሉያት ወደ ፊት የሚመጣውን መዳኛ መንገድ ሲያውጁ አዲሳት ደሞ ወደ ኃላ በማየት በክርስቶስ ኢየሱስ መምጣት የተፈጸመውን መዳን ያውጃሉ። ብሉይ እንደ ጥላነት ሲያገለግል አካሉ ግን ክርስቶስ ነው(ቆላ2፥16-17, ዕብ 8፥5)። በአዲስ ኪዳን የተከናወኑ ነገሮች ሁሉ ፈጽመው ያልታሰቡ ሳይሆኑ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተሰውሮ የነበሩ ናቸው። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው በብሉይ ኪዳን የነበረው የድነት መንገድ እራሱ ነው በአካል የተገለጠው። በየትኛውም ዘመን ሰው በሕግ ስራ በእግዚአብሔር ፊት ጸድቆ አያውቅም። ሕግን የሰጠው ሙሴ ራሱ በሕግ የጸደቀ አልነበረም(ዕብ 11፥24-29)። ቀድሞም ሕግ ሰዎችን ለማጽደቅ የተሰጠ አይደለም(ገላ 3፥19-26)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመዳን መንገድ ሆኖ በመጣ ጊዜ በአለም ላይ

ሁለት አይነት ሰዎች ነበሩ። አይሁድና አህዛብ። አይሁድ በስጋ መገረዝ የተገረዙና የዕብራዊው አብርሃም ዘሮች የሆኑ ሲሆኑ አህዛብ ደግሞ ከያዕቆብ 12 ልጆች ውጭ ያሉ ሕዝቦች በሙሉ ናቸው።የኢየሱስን መምጣት ከእነዚህ ሕዝቦች አንጻር መረዳት ጥሩ ነው።

አይሁድ የሚባለው ሕዝብ በአባቶቹ ስራ በጣም የሚመካ ፣በስጋው መገረዝ ራሱን እንደተለየ ማህበረሰብ የሚያይና አይሁድ ያልሆኑ ሰዎችን በጣቱ እንኳን መንካት ማይፈልግ በፈጣሪ የተመረጠ የአለም ማዕከላዊ ሕዝብ የነበረ ነው። ይህ ሕዝብ እንደሚለው የተለየ እንደሆነ ቅዱሳት መጽሐፍት ያውጃሉ
“እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር ኪዳንም የሕግም መሰጠት የመቅደስም ሥርዓት የተስፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤”
— ሮሜ 9፥4

ይህ ታላቅ ሕዝብ የብሉይ ኪዳናት በረከቶች ሁሉ የርሱ የሆነለት ነጉስና ካህናት የሆኑለት ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጠ ከሌላው በአለም ካለው ሕዝብ ሁሉ የተለየ ነበር። ከዚህም ሕዝብ እግዚአብሔር ለአለም መድኃኒት የሚሆንን ዘር እንደሚያመጣ ቃል የተገባለት ነበር። ይህ ታላቅ ሕዝብ ከንጉስ ሰለሞን ዘመን በኃላ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ጣኦት አምላኪነት ገባ። እግዚአብሔር ብዙ ነቢያትን በመላክ ቢያስጠነቅቃቸውም እነርሱ ግን ሊሰሟቸው አልቻሉም።ስለዚህም እግዚአብሔር በነብዩ ኤርሚያስ በኩል የአህዛብን መንግስት ወደ አንቺ አመጣለው በባርነትም ለሰባ አመት ወደ ባቢሎን ትወርጂያለሽ ለአህዛብም ባሪያ ትሆኛለሽ ብሎ ለኢየሩሳሌም ተናገራት(ኤር 25፥11-12)። የተባለው ተፈጽሞ የባቢሎን መንግስት ኢየሩሳሌምን ከቦ ሕዝቦቻን ወደ ባቢሎን አጋዘ፤ ኢየሩሳሌም ባሪያ ሆነች(2 ዜና 36)።በባርነት ወደ ባቢሎን ከተወሰዱ አይሁዳውያን መካከል ዳንኤል አንዱ ነበር። ይህ ዳንኤል በአንድ ወቅት የነብዩን ኤርሚያስን ትንቢት እያነበበ ኢየሩሳሌም ለ70 አመት በባቢሎን በግዞት እንደምትገዛ የተነበየውን ካነበበ በኃላ ያህ የተነገረው ሰባ አመት እየተፈጸመ እንደሆነ ሲያስተውል ዳንኤል "ኢየሩሳሌም የምርኮዋ ጊዜ ተፈጽሞአልና ወደራሷ መንግስት መልሳት" እያለ ሲማጸን እግዚአብሔር በመልአኩ በኩል ፀሎቱን በራዕይ ይገልጥለታል(ዳን 9)።

ነብዩ ዳንኤል የኢየሩሳሌም መልሶ መገንባትንና እንደመንግስት መቆምን በአምላኩ በእግዚአብሔር ፊት በንስሀ ያቀርባል።እግዚአብሔርም የኢየሩሳሌምን መልሶ መገንባትና እንደመንግስት ለማቆም 70 ሱባኤ(ማለትም 490 አመታት) ታውጀዋል።ይህ 490 አመት ሲፈጸም የዳዊት ልጅ ይመጣና ኢየራሳሌምን እንደገና ይገነባታል።ነገር ግን ከዚህ 490 አመት አስቀድሞ በ 69 ኛው ሱባኤ ( ማለትም 490 አመቱ ሊፈጸም 7 አመት ሲቀረው) መሲሁ ይገደላል። ከ 7 አመትም በኃላ የመሲሁ መንግስት በኢየሩሳሌም እንደሚመሰረት መልአኩ ለዳንኤል በራዕይ ገለጠለት።እነደተባለውም መሲሁ በ 69ኛው ሱባኤ ላይ ተገደለ ማለትም ዳንኤል ባየው መሰረት የኢየሩሳሌም ቅጥር መገንባት ከጀመረበት ጀምሮ 483 አመት በኃላ ማለት ነው። ከመሲሁ መሞት 7 አመት በኃላ ቅድስቲቱ ከተማ እንደ ሀገር እንደምትቆም ቢተነበይም አይሁዶች መሲሀቸውን ባለመቀበላቸው ምክንያት ያቺ ሰባት አመት ሳትጀምር በ69 ኛው ሱባኤና በቀረችው አንድ ሱባኤ(7 አመት) መካከል በብሉይ ነቢያት ያልታየች

ግን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የነበረ ሚስጥር የጸጋ ዘመን በመካከል ገባ(ኤፌ 3)።

ይህም ብቻ ሳይሆን በዳንኤል 2 እና 7 ላይ በንጉስ ናቡከደነፆርና በራሱ በዳንኤል የታዩ ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸው ሁለት ሕልሞች ታይተዋል።የሁለቱም ምንጭ እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር ወደፊት የሚመጣውን ጉዳይ ቁልጭ አድርጎ እስከነፍቺው ይነግራቸዋል።

ሕልሞቹን ትቼ ወደ ፍቺው ስገባ በአለም ላይ በተከታታይ የሚነሱ አራት መንግስታት እንዳሉ በራእዩ ተናገና እነዚህ አራት መንግስታት እስራኤልን በግዞት የሚይዙ ናቸው። የመጨረሻውና አራተኛው መንግስት በተነሳ ጊዜ በጣም ኃይለኛ የብረት መንግስት እንደሚሆንና እስራኤልን በሀይለኛው እንደሚያስጨንቅ ተናግሯል። በዚያህ ጊዜ ያንን መንግስት የሚያፈርስና የሚያጠፋ የሰማይ መንግስት(መንግስተ ሰማይ) እንደሚወርድና እስራኤልን በተከታታይ በአራት መንግስታት ከተገዛችበት ግዞት ነጻ እንደሚያወጣ፤ በአለምም ላይ ገናና መንግስት እንደሚመሰርት መልአኩ ለዳንኤል ይገልጥለታል። ይህም መንግስት የዳዊት ልጅ መንግስት ወይም የመሲሁ መንግስት ይባላል።

እንግዲህ የእስራኤል ልጆች ከሰለሞን መንግስት በኃላ ከ 722 ቅ.ዓ.ክ ጀምሮ በተለያዩ አራት መንግስታት በግዞት የነበሩ ሲሆን እግዚአብሔር በዳንኤል አማካይነት ከአራተኛው መንግስት በኃላ የዳዊት ልጅ እንደሚወለድና ያቺን የጸናች የመሲሁን የሰማይ መንግስት(መንግስተ ሰማይ) እንደሚመሰርት ተናግሯቸዋል። እነዚህ መንግስታት የባቢሎን መንግስት(ቅ.ዓ.ክ- ) ፣ የፋርስና የሜዶን መንግስት ፣ የግሪክ መንግስት ና የሮም መንግስት ናቸው።የሮም መንግስት አራተኛውና እንደዳንኤል ትንቢት የመጨረሻው መንግስት ሲሆን በዚህ መንግስት ዘመን የእስራኤል ሕዝብ የዳዊት ልጅ የሚመጣበት ጊዜ እንደደረሰና የሮምን መንግሥት ደምስሶ በእስራኤል ላይ የሰማይን መንግስት(መንግስተ ሰማያት) መስርቶ የተደላደለችውን የዳዊትን ዙፋን ሚመሰርትበት ጊዜ እንደደረሰ አውቀዋል።በዚህ ጊዜ ነበር የናዝሬቱ ኢየሱስ የተወለደው። የናዝሬቱም ኢየሱስ የተወለደው በነብዩ ዳንኤልና በሌሎች ነቢያት የተነገረውን የሰማይ መንግስት (መንግስት ሰማያት) ማለትም የዳዊትን ዙፋን ለመሰረት ነበር(ሉቃ 1፥31-33)።

ይህ መሰረታዊ እውነት ከገባን አዲስ ኪዳንን ስናጠና መዳን እና መንግስት ሰማይ የሚሉ ሀሳቦችንም ትርጉም እናገኛቸዋለን። በኢየሱስ ትምህርት ውስጥ መንግስት ሰማይ የሚለውን ሀሳብ በቀጥታ ከቤተ ክርስቲያን የመዳን መንገድ ጋር ለማገናኘት ከተሞከረ የተወሳሰበ ጉዳይ ውስጥ ልንገባ እንችላለን። በአዲስ ኪዳን መዳንን ለአይሁድና ለአህዛብ ብለን ከፍን እንመልከት

1. መዳን ለአይሁድ

ኢየሱስ በስጋ በተገለጠበት ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ እንደዳምኤል ትንቢት መሰረት አራተኛው መንግስት ሲሆን ያንን ታላቅ መንግስት የሚያደቅ የሰማይ መንግስት ለእስራኤል እንደምትመጣ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ። እነርሱም በቅርቡ

መሲያችን የዳዊት ልጅ ይመጣና ይህንን የሮምን መንግስት ደምስሶ የእስራኤልን መንግስት ይመልሳል ይሉ ነበር። ኢየሱስም በመጣ ሰዎን የሰበከው የእስራኤል ልጆች የሚጠብቁትን የሰማይ መንግስት(መንግስተ ሰማይ በግእዙ) ነበር። የእስራኤል ልጆችም ኢየሱስን የዳዊት ልጅ ይሉት ነበር። በትክክል ኢየሱስ የመጣውም ለእስራኤል ልጆችን ነፃ ሊያወጣ ነበር(ማቴ 10፥5-7, 15፥24)።ኢየሱስ ባስተማረውና በሰበከው መንግስት ውስጥ ከእስራኤል ልጆች ውጭ ያሉት ተካፋይ አልነበሩም ይልቅስ ድንጋዮችና ውሾች እየተባሉ ሲገፉ ነበር(ማቴ 3፥9,15፥26)። የእስራኤል ልጆች መዳንና መንግስት ሰማይ ሲባሉ ከሮም መንግስት ነፃ መውጣትንና በራስ ሀገር በነፃነት መኖርን ነው የሚጠብቁት። ታላቁና የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ነብይ መጥምቁ ዮሐንስም በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ ነበር(ማቴ 11)።

ኢየሱስ እንደዳዊት ልጅ የተገለጠበት ከሌሎቹ መጽሐፍት በተለየ በማቴዎስ ወንጌል ነው። በዚህ ወንጌል ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የዳዊት ልጅና የእስራኤል ተስፋ እንደመጣ የሚያውጅ መጽሐፍ ነው። በተለየም በዚህ ወንጌል ነው የዳዊት ልጅ , መንግስተ ሰማይ የሚሉ ቃላት በብዛት የሚገኙት።በዚህ ወንጌል ኢየሱስ የዳዊትን ልጅ መንግስትና ለዚህ መንግስት በሚገባ በንስሀ እንዲዘጋጁ እየሰበከ የመጣበት መጽሐፍ ነው።የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ነፃ ያወጣው ሙሴ በተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ሕግ በተራራ ላይ እንዳወረደ እንዲሁ የአዲሱ ኪዳን ነፃ አውጪ ኢየሱስ በተራራ ላይ የእግዚአብሔርን ሕግ ሰጣቸው(ማቴ 5-7) ።ሙሴ አስር ተአምራትን አደረገ እንዲሁ ኢየሱስ ከተራራ ከወረደ በኃላ አስር ተአምራትን አደረገ። ነገር ግን የእስራኤል ልጆች መሲሀቸውን መቀበል አልቻሉም ፤ ነፃ አውጪያቸውን አንተ የቤኤል ዜቡል መንፈስ አለብህ አሉት(ማቴ 11-12)።

በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ከቤት (ከእስራኤል ልጆች) በመውጣት የመንግስተ ሰማያትን ሚስጥር(ቤተ ክርስቲያንን) ማስተማር ጀመረ(ማቴ 13)። መንግስተ ሰማይ ከአይሁድ የመዳን ጉዳይ ጋር የሚያያዝ ሲሆን የመንግስተ ሰማያት ሚስጥር ደግሞ የአህዛብን የመዳን መንገድ የሚናገር ነው።የእስራኤል ልጆች መሲሀቸውን ባለመቀበላቸው የተዘጋጀላቸው መዳን ወዳልተወሰ ጊዜ ተላለፈና ከእንግዲህ በዳዊት ልጅ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ስትዪኝ መጥቼ አድንሻለው(ሉቃ 13፥35) ብሎአት ፊቱን ወደ አህዛብ አዞረ:::: ከዚያም ከሮም ግዛት የመዳን ትምህርት ተቀይሮ ከኃጢያት የመዳን ትምህርት ተጀመረ። ኢየሱስ ክርስቶስ የዳዊት ልጅና የአብርሃም ልጅ በመባል ተገልጦአል(ማቴ 1፥1)።የዳዊት ልጅ መሆኑ ለእስራኤል ከሮም ግዛት መዳንና የዳዊትን መንግስት ለእስራኤል መመለስ ሲሆን(2 ሳሙ 8) የአብርሃም ልጅ መሆኑ ደግሞ ለአለም ሁሉ በረከት ወይም መዳን የሚለውን ትምህርት ይይዛል(ዘፍ 15)።

ይህ ሁሉ ነገር ግን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ የነበረ ትምህርት ነበር።ነብዩ ዳንኤል መሲሁ እንደሚሞት ካየ በኃላ በቀጥታ መንግስቱን እንደሚመሰርት ተነበየ (ዳን 9)። የኢየሱስ ሐዋሪያትም ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኃላ መጀመሪያ ያቀረቡለት ጥያቄ እንዲህ የሚል ነው

ሐዋርያት 1

----------

 እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት።
 እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ኢየሱስ ለእስራኤል መንግስትን የሚመልስበት ጊዜ እንዳለ ነው ያህ ግን ጊዜው በአብ ዘንድ ተሰውሮአልና እናንተ ግን መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችሁ የጸጋውን ወንጌል ተሰብካላችሁ አላቸው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ያልተናገሩት ይህ የጸጋ ወንጌል ከየት መጣ? ሲባል ሐዋሪያው ጳውሎስ ይመልስልናል። ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን 3 ላይ እግዚአብሔር በእንዴት አይነት መንገድ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ አካል እንዳለበሰው ይተርክልናል።ይህ እውነት ከቀደሙት ነቢያት የተሰወረ ነው የተገለጠውም በአዲሳት ነቢያትና ሐዋሪያት ነው በማለት ይህንን ክፍለ ዘመን(Dispensation) ያስተዋውቀናል።ይህ ክፍለ ዘመን አህዛብን ሁሉ የጨመረና ለአለም ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ደጆች የከፈተ የጸጋ ዘመን ይባላል።

የአይሁዶች የመዳን መንገድ በዚች መጽሐፍ ምዕራፍ ሦስት ላይ በማቴዎስ 24 እና 25 ላይ መልሶችን ስዘነዝር በተወሰነ መልክ አንስቻለው።በተጨማሪ ስለዘመን ፍፃሜ የተጻፉ መጽሐፎችን እንድታነቡ በጌታ ፍቅር አሳስባለው።

## 2. የአህዛብ የመዳን መንገድ

ለአይሁድ ሕዝብ አህዛብ በክርስቶስ መንገድ ገብቶ የኪዳን ተካፋይ ይሆናል የሚለው ትምህርት እጅግ በጣም ያስቸግራቸዋል። ከክርስቶስ ኢየሱስ ትንሳኤ በኃላ ኢየሱስ ራሱ ወንጌልን እስከ አለም ዳርቻ ስበኩ ብሎ ነግሯቸው፤ ሐዋሪያት ሲያስቡት የነበሩት በአለም ሁሉ ላይ ተበትነው ለሚገኙ አይሁዶች ብቻ አድርሱ ያላቸው መስሏቸው ነበር። ምክንያቱም ራሱ መሲሁ ከትንሳኤው በፊት ወደ አህዛብና ሳምራውያን እንዳትገቡ ብሎ አዟቸው ስለነበር ነው።እግዚአብሔር ራሱ ለሐዋሪያው ጴጥሮስ በሕልም ተገልጦ አህዛብን በወንጌል እንዲደርሳቸው ሲነግረው ከጌታ ጋር ግብ ግብ ውስጥ ገብቶ ነበር ።እነዚህ አረማውያን እንዴት የኪዳኑ ተካፋዮች ይሆናሉ? በሚል(ሐዋ 10)። ምንም እንኳን ጴጥሮስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለአህዛብ ወንጌልን ሰብኮ የቤተ ክርስቲያን አካል ቢሆኑም ለእርሱ ግን አልተዋጠለትም ነበር።

በኃላ ጌታ ደግሞ ይህንን እውነት በስፋት መስበክና ማስተማር የሚችል አንድ ከኃጢያተኞች ዋና ባለአእምሮ ጠራ። ስሙም ሳውል የተባለ ጳውሎስ ይባላል።ይህ ሰው ፈሪሳዊ የነበረ ሲሆን በሙሴ ሕግም ከዘመኑ ከነበሩት አይሁዳዊ ወጣቶች ሁሉ የበለጠ ምሁር ነው(ፊሊ 3፥4-6,ገላ 1፥13-14 )።እግዚአብሔር በዚህ ሰው በኩል አህዛብ በእንዴት አይነት መንገድ ከአይሁድ ጋር አብረው ወራሾች እንደሆኑ በመገለጥ ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተምሮ ብቅ አለ።(ገላ 1፥11-12,ኤፌ 3)። ይህ ክርስቶስ በጳውሎስ በኩል የላከው ወንጌል ከቀደሙት ሐዋሪያት ትምህርት ጋር የሚስማማ ግን ከእነርሱ ይልቅ የጠለቀና የሰፋ ይዘት ያለው ነበር። ይህም ታላቅ ወንጌል በኢየሱስ ክርስቶስ

ስቅለት፣ ሞት መቀበርና መነሳት ላይ ያነጣጠረ ነበር(1 ቆሮ 15፥1-7)። ይህ ሰው አህዛብ ከአይሁድ ጋር የኪዳን ተካፋይ የሆኑበት መንገድ የክርስቶስ ደም እንደሆነ አስተማረ(ኤፌ 2)። አህዛብ ወደ አይሁድ ግንድ የገቡት በኢየሱስ መወለድ ሳይሆን ከኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኃላ ነው። ይህም የጸጋው ወንጌል ዘመን ይባላል። ከኢየሱስ መወለድ እስከ ሞቱ ድረስ ሲሰበክ የነበረው የመንግስት ሰማያት ወንጌል(የመንግስቱ ወንጌል) በመባል ይታወቃል(ማቴ 24፥12)። በዚህ ወንጌል ውስጥ ዋናው ትኩረት የዳዊት ልጅ ለእስራኤል የሚመልሰው ምድራዊ መንግስት ነበር። ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በኃላ ግን እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ የመስቀል ስራ በኩል ከአህዛብና ከአይሁድ አንድን አዲስ አካል ፈጠረ(ኤፌ 2)። ይቺም አዲስ አካል ቤተ ክርስቲያን ትባላለች።ይቺ አካል አይሁድም አህዛብም አይደለችም(ገላ3፥27-30,ቆላ 2)።

ይህቺ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በፊት በአካል ያልነበረችና አልፎ አልፎ ግን ክርስቶስ ወደ ፊት ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመሰርት ይናገር ነበር(ማቴ 8፥11,16፥18-19)።ይችህ ቤተ ክርስቲያን መነሻዋ የክርስቶስ የመስቀል ስራና ያፈሰሰው ደሙ ነው(ኤፌ 2,ዘጸ 12፥1)።ወደ ኪዳኑም መግቢያ መንገዱ መንግስቱን እያሰቡ ንስሀ መግባት ሳይሆን ሀጢያተኛ መሆኑን አውቀው መድኃኒት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝና እንደ ጌታ መቀበል ነው። "መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ" የሚለው ስብከት ምድራዊ መንግስት ለሚጠብቁ የእስራኤል ልጆች የሚሰበክ ነው እንጂ ፈጽሞ ለአህዛብ አለም የሚሰበክ አይደለም።ለአህዛብ ሁሉ "መንግስተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሀ ግቡ" ብንላቸው የምን መንግስት? ነው የሚሉን።ግን በአሁኑ ጊዜ በየአደባባዩ መንግስተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሀ ግቡ ሲባል ይሰማል በእኛም በኢትዮጵያ ምድር፤እና የትኛው መንግስት የሚል ጥያቄ ያስነሳል።ምክንያቱም ሰዎች ከዚህ በፊት የሚመጣ መንግስት እንዳለ አልሰሙምና። አህዛብ መጀመሪያ የሚመጣ መንግስት እንዳለ መስማት አለበት። ግን እኛ ስለሚመጣው መንግስት ሳይሆን ስበኩ የተባልነው "ኢየሱስ ክርስቶስ ሀጢያተኞችን ሊያድን መቶአል" የሚለውን ቃል ነው(1 ጢሞ 1፥15)።

ድነት የሚለው ቃል ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በፊት ከሮማውያን ግዛት ተላቆ የዳዊትን ልጅ መንግስት ለእስራኤል መመለስና ለአይሁዶች አካላዊ ነጻነትን መስጠት ሲሆን ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በኃላ ግን ከኃጢያት ና ከሞት አምልጦ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆንን ስልጣን ማግኘት ነው። ይህም ድነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ማለትም ከሞት መነሳቱን በልባችን ስናምንና ጌታ መሆኑን በአፋችን ስንመሰክር ነው(ሮሜ 10)። የእስራኤልን መንግስት ለመውረስ ግን በእስራኤል ልጆች የሰባቱ አመት መከራ ስለመሲሁ ሲባል የሚሰደዱትን አይሁዶች(የኢየሱስን ወንድሞች) ለእነርሱ የምትመጣ መንግስት እንዳለች በማመን ሲራቡ ማብላት የታረዙትን ማልበስ የታሰሩትን መጠየቅ ያስፈልጋል(ማቴ 25፥32፥46)።

እኛስ ከሞቱና ከትንሳኤው በኃላ የመጣን በልጁ ደም አምነን ከእግዚአብሔር ቁጣ ያመለጥም፣ ያለምንም መልካም ስራ የዳንንና ከሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች የሆንን አዲስ ፍጥረቶች ነን። ለመዳን የተራበ ካበላን የታረዘ ካለበስን የታሰረ ከጠየቅን እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ ማለት ነው! (ገላ 2፥21)። ያዳነንም

ክርስቶስ ሳይሆን መልካም ስራችን ነው ማለት ነዋ? ግን ፈጽሞ አይደለም።
2ኛ ጢሞቴዎስ 1
-----------

 ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥
1-11 አሁን ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቶአል። እርሱ ሞትን ሽሮአልና እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን በተሾምሁበት በወንጌል ሕይወትንና አለመጥፋትን ወደ ብርሃን አውጥቶአል።

# ምዕራፍ ሁለት

## የዘላለም ሕይወት ዋስትና

በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ አንድ እውነተኛ ክርስትያን በተለያዩ ድካሞች ድነቱን ሊያጣ ይችላልን? የሚለው ጥያቄ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ ወደፊት እንዳይራመዱ አንቆ የያዛቸው ጉዳይ እንደሆነ ግልጽ ነው። የዚህ ምክንያት ቅዱሳት መጽሐፍት በግልጽ ስለዚህ ጉዳይ የሚሉት ነገር ስለሌለ ነውን? ብለን ስንጠይቅ ቤተ ክርስቲያንን ለ 2000 አመታት ከውስጥም ከውጭም የሚነሱትን የስህተት ትምህርት ወጀቦች ተቋቁማ ዛሬን እንድትደርስ ደጀን የሆኗትን ቅዱሳት መጽሐፍት ለዚህ ትምህርት ማረጋገጫ የለውም ማለት የቅዱሳት መጽሐፍትን ሀይል ያለመረዳት ድንዛዜ ነው፤ እንጂ የቅዱሳት መጽሐፍት ትልቁና መሀከላዊ ትምህርት መዳንና አለመጥፋት ነው። በአጭሩ ቅዱሳት መጽሐፍት የድነት መጽሐፍት ናቸው ማለት እንችላለን።

“ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።”
— 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥15

"መዳንና አለመጥፋት ከእግዚአብሔር ዘንድ በነጻ የተሰጡን ነፃ ስጦታዎች ናቸው።" (ዮሐ 3፥15-16, ሮሜ 6፥23)

ድነት የእግዚአብሄር ስጦታ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ይናገራል። ሰዎችም በክርስቶስ ከማመን በስተቀር ለመዳን የሚከፍሉት ወይም የሚሰሩት ምንም አይነት ስራ የለም። የተቀበልነው ድነት ዳግም ልደትን ፣ መፅደቅንና ልጅነትን ያስገኛል። ይህም በእምነት የተገኘው አዲሱ ህይወት አዲስ የህይወት ዜዬን ፈጥሮልናል(ቲቶ 1:11 ሮሜ 6:23፤2ጢሞ 1:9)። ይሁንና በዚህ አዲስ ህይወት የተጀመረው ድነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊታጣ ይችላል የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት ለዚህ መፅሀፍ ቅዱሳዊ መልስ ለመስጠት ከሁለት አቅጣጫ ማየት ግድ ነው።

- ከእግዚአብሄር አቅጣጫ ፡- የሰዎችን መልካምነት ግምት ውስጥ ሳያስገባ በቸርነቱ ድነትን የሰጠ እግዚአብሄር በጊዜ ሂደት የሰዎችን ባህርይ ተንተርሶ ሃሳብ በመለወጥ በነፃ የተሰጠውን ድነት መልሶ አይወሰደውም(ፊሊ 1፡6)። በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛነት በኩል ወደ አማኞች የመጣው በረከት ሁሉ ሰማያዊና መንፈሳዊ እንደሆነ መረሳት የለበትም(ኤፌ 1፥3)።ሰማያዊና መንፈሳዊ ማለትም በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ የተደረጉ ናቸው።

ኤፌሶን 1
-----------

3 በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።
4 ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።

ከላይ ባለው ክፍል ውስጥ "በፊቱ" (በእግዚአብሔር ፊት) የሚለው ሀይለ ቃል ነው። ይህ ቃል በትርጉም ውስጥ ከተዘነጋ ብዙ ትምህርቶችን ያዛባብናል።የእኛን ስራና ስሜት ባላገናዘበ ሁኔታ ድነት በክርስቶስ ኢየሱስ በሰማያዊ ስፍራና በመንፈሳዊ እይታ በአብ ፊት ተጠናቀዋል።

“አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት አይደለም።”
— ሮሜ 4፥2
በዚህም ክፍል " የእግዚአብሔር ፊት" የሚለው ሀይለ ቃል ነው። ካልሆነ ደሞ ከያዕቆብ መልእክት ጋር እየተጋጨ እየመለሰን እንቸገራለን።

- ከሰዎች አቅጣጫ፡- በዳግም ልደት ህይወት የተለወጠ፤ በቅድስና እንዲያድግና ወደ ኋላ የመመለስ ፈተናዎችን እንዲያሸንፍ የሚያስችለውን የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ በየእለቱ የሚያገኝ ፣ደግሞም ክርስቶስ በአብ ቀኝ ሆኖ የሚማለድለት ሰው ይህን ሁሉ ድጋፍ ከእግዚአብሄር እያገኘ ጌታን ሊክድ ወይም በአመፅ ሊኖር አይችልም (ኤፌ 6፥1-23 ,ሮሜ 8፡31-39)። በእግዚአብሔር ፊት በጸጋ በኩል የተሰጡንን በረከቶች ሁሉ የምንቀበለው በእውነተኛ እምነት በኩል ብቻ ነው።ሁሉም ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ የተደረገለትን የተቀበለበትን እምነት ፈጽሞ አጥብቆ ሊይዝ ይገባል(ዕብ 10፥35፥39)።

  ብዙ ክርስቲያኖች የእነዚህን ሁለት አድማሶች ልዩነት ባለማወቃቸው የተወዛገበና መሰረት የሌለው አቋም ላይ ናቸው። ለምሳሌ በሮሜ መልእክት 4 እና በያዕቆብ መልእክት 2 መካከል ያለውን ልዩነት በትክክል ካወቅን የድነት ትምህርት በአንድ አቅጣጫ መሰረቱ ይስተካከላል

የያዕቆብ መልእክትና የሮሜ መልእክት ንጽጽር

# ያዕቆብ መልእክት መግቢያ

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለመፍታት ጥንቃቄ ከሚፈልጉ መጽሐፍት መካከል የያዕቆብ መልእክት ዋነኛው ነው። ምክንያቱም ከሰላምታው ጀምሮ " ለተበተኑት ለዐስራ ሁለቱ ነገዶች " ብሎ ይጀምራል። ምንም ለክርስቲያኖች የተጻፈም የሚመስል አይደለም። በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ቦታ ብቻ ነው "ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚል ስም የተጠቀሰው ። ምናልባትም እነዚህን ጥቅሶች ብናወጣቸው መጽሐፉ ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍነት ይወጣና የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ይሆን ነበር። እና ከሰላምታው ጀምሮ ከብኪ ጋር የሚመሳሰል መጽሐፍ ነው።

የአዲስ ኪዳን መሰረት የሆኑት የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ መሆን( Incarnation ) እና ትንሳኤ (Resurrection) በመጽሐፉ ውስጥ አልተጠቀሱም።በመጽሐፉ ውስጥ በአንድም ስፍራ " ወንጌል " የሚለው ቃል ፈጽሞ አልተጠቀሰም።እንዲሁም መሲሁ እንደመጣና መቤዠትም ደሞ በእርሱ በኩል እንደሆነ የሚናገር ክፍል የለውም።

የመተርጎም መንገዳችንን ትንሽ የሚያከብድብን ደግሞ በመልእክቱ ውስጥ ከሐዋሪያው ጳውሎስ ጋር ተመሳሳይ ጥቅስ ተጠቅመው ግን የተለያየ ፍቺ መስጠታቸው ነው። "አብርሃም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት" ለሚለው ዓረግ ሁለቱ የሰጡት ፍቺ የተለያየ ስለሆነ ስነ አፈታቱ ላይ ጥንቃቄ ይፈልጋል።

በአጠቃላይ ግን

"Paul looks closely at the root of Gosple tree and James focuses primarly on the fruit of Gospel tree.

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ማስረገጫዎች ላይ ተመስርተን የያዕቆብ መልእክት የድነት መጽሐፍ አለመሆኑን እናውቃለን

- የክርስቶስ ስጋ መሆን አለመጠቀስ
- የክርስቶስ ትንሳኤ አለመጠቀሱ
- ወንጌል የሚለው ቃል በመጽሐፉ ውስጥ አለመኖሩ
- ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም ከሁለቴ በላይ አለመጠቀሱ
- የኢየሱስ የቤዛነት ስራ ከነጭራሹ አለመነሳቱ

በእነዚህና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ ተመስርተን ያዕቆብ ይሄንን መልእክት የጻፈው የድነትን መንገድ ለመናገር እንዳልሆነ እናረጋግጣለን። ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ የምናገኛቸውን መልእክቶች ለድነት እንደሚሆነ አድርጎ መጠቀም ሊያሳስተን ይችላል።ታዲያ ያዕቆብ የጻፈበትን ምክንያት ከመጽሐፉ ራሱ ማግኘት ስላለብን የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት

“በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።”
— ያዕቆብ 1፥12

"ስለዚህ ርኵሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፥ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።"
— ያዕቆብ 1፥21

* ከመጀመሪያው ጥቅስ "የሕይወት አክሊል" ከሁለተኛው ደግሞ " ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን" የሚሉትን ዓረጎች ስንመለከት በትክክል ያዕቆብ የሚናገረው ነገር ይገባናል። ሁለቱንም እንያቸው እስቲ

1. በያዕ 1፥12 ላይ "የሕይወት አክሊል"
* የዘላለም ሕይወትና መጽደቅ ከእግዚአብሔር ዘንድ በነጻ የተሰጡን ስጦታዎች ናቸው( ሮሜ 6፥23, ሮሜ 3፥24)። በዚህ ክፍል ላይ የተነሳው ሀሳብ ግን "የዘላለም ሕይወት" ሳይሆን "የሕይወት ሽልማት" ነው። ማለትም አክሊል ማለት አንድ ሰው የሆነ ስራ ሰርቶ(most of the time በሩጫ ውድድር አሸንፎ 1 ቆሮ 9፥24-27) የሚቀበለው ሽልማት ነው። ይህ ስጦታ አይደለም የራስ ጥረት ውጤት ስለሆነ አክሊል ወይም ሽልማት ነው።

"ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።"
— ራእይ 2፥10
* ከዚህ መጽሐፍ የምንረዳው የሕይወት አክሊል ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንዲሁ የሚቀበሉት ስጦታ ሳይሆን ለክርስትናቸው እስከሞት ድረስ የታመኑ ሲሆኑ የሚቀበሉት ሽልማት ነው።መዳን ግን በጸጋ ብቻ ነው።ያዕቆብ ሲጀምር ክርስቲያኖችን ስለ አክሊል(ሽልማት) ከመናገር ይጀምራል ማለትም መጽሐፉ የሚናገረው ስለክርስቲያኖች የመዳን መንገድ ሳይሆን ስለ ክርስቲያኖች የስራ ውጤት ነው። መዳን የእምነት ውጤት ነው , አክሊል ከእምነት የመነጨ የስራ ውጤት ነው።

2. ያዕ 1፥21 "ነፍሳችሁን ማዳነ የሚችለውን በውስጣችሁ የተተከለውን ቃል "

* በዚህ ዐረግ ውስጥ ደግሞ እየተወራ ያለው መዳን የመንፈስ ሳይሆን የነፍስ ነው። ዳግም ውልደት, መጽደቅ,የዘላለም ሕይወት, አዲስ ፍጥረት መሆን በቀጥታ የሚያያዘው ከመንፈሳችን ጋር እንጂ ከነፍሳችን ጋር አይደለም(ዮሀ 3፥5-10)። በእምነት በኩል የዳነው መንፈሳችን ነው እንጂ ነፍሳችን በእምነት ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ነው እየዳነች የምትሔደው። የመንፈስ መዳን ቅጽፈታዊ ነው የነፍስ መዳን ግን ሂደታዊ ነው(ፊሊ 2፥12)።

መንፈሳችን ባመነ ቅጽፈት መዳኑን አግኝቶአል(ኤፌ 2፥8-9, ሮሜ 4፥24-25, 1ቆሮ 6፥ 11...) ነፍሳችን ግን በጊዜ ሂደት ውስጥ ድነቷን እየተቀበለች ትሄዳለች(1ጴጥ 1፥8-9, ፊሊ 2፥12, ያዕ 1፥21..)። ስጋችን ደሞ በንጥቀት ጊዜ ደነቱን ይቀበላል( 1ቆሮ 15፥51-58, ፊሊ 3፥20-21, ሮሜ 13፥11)።መንፈስ ድነትን የሚቀበለው በጸጋ ላይ ባለ እምነት ብቻ ነው ነፍስ ግን ድነትን የምትቀበለው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።የትኛውም ሰው የያዕቆብን መልእክት አንስቶ ስራ ያድናል ያጸድቃልም የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ የቅዱሳት መጽሐፍትን ትምህርት ባለማወቅ ጠንቅ ተይዞአል ማለት ነው። ኢየሱስ በአንድ ስፍራ እንዲህ አለ

"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።"
— ማቴዎስ 22፥29

ጌታ የተናገረውን ቃል በትክክል ካየነው ስለቅዳሳት መጽሐፍ አጠናን የሚጠቁመን ነገር አለ። ያለው "መጽሐፍንና" ሳይሆን " መጽሐፍትንና" in english no " Scripture", He said " Scriptures" . ጌታ እንዲህ ያለው የተወሰነ መጽሐፍ ብቻ ይዘው doctrine ለመስራት የሚፈልጉትን ሰዱቃውያንን ነው። የያዕቆብን መጽሐፍ ብቻ ይዞ አስተምሮ (doctrine ) መመስረት ለስህተት ይዳርጋል።ስለዚህ ሙሉ ቅዱሳት መጽሐፍት መሀከል ያደረገ አስተምሮ (doctrine) እናቁም

የሮሜ መጽሐፍ 4 ና የያዕቆብ 2 የሚጋጩ ሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ ግን ልክ አይደሉም። በመጀመሪያ የያዕቆብን መልእክት የጻፈው የጌታ ወንድም ያዕቆብ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ብቻ እንደሚዳን በታላቁ የኢየሩሳሌም ጉባኤ የመጨረሻውን ውሳኔ ያስተላለፈ አባት ነው(ሐዋ 15)። ያዕቆብ ራሱ እምነት + ስራ = መዳን የሚለውን የማይቀበል መሆኑን አረጋግጠን ወደ መጽሐፎቹ እንግባ።

ሐዋሪያው ጳውሎስ መዳን በእምነት እንደሆነ ያስተማረበትንና አብርሃምን ምሳሌ አድርጎ ያቀረበበትን ክፍል እንመልከተው ሮሜ 4

¹ እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን?
² አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።
³ መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።

ይህ ክፍል ሰዎች ሊጸድቁ የሚችሉት እንደ አብርሃም በእምነት ብቻ እንጂ በስራ እንዳልሆነ ይገልጻል።ከዚያ አብርሃም በእምነት ብቻ ስለጸደቀ የሚመካበት የለውም ተባለ። የሚመካበት የሌለው ግን በጸደቀበት በዚያ ስፍራ ነው። ስፍራው የት ነው ሲባል "በእግዚአብሔር ፊት" ወይም "Before God" (ቁ 2)። አብርሃም ግን የሚመካበት የለው ወይ?? ብለን ስንጠይቅ የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለው አብርሃም አይደለም ከእርሱ 2000 ምናምን አመት በኃላ የመጣው ጳውሎስ እንኳን የአብርሃም ልጅ በመሆኑ በስጋ የሚመካበት ነበረው

ፊልጵስዩስ 3
----------

⁴ እኔ ግን በሥጋ ደግሞ የምታመንበት አለኝ። ሌላ ሰው ማንም ቢሆን በሥጋ የሚታመንበት እንዳለው ቢመስለው፥ እኔ እበልጠዋለሁ።
በስምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፥ ከእስራኤል ትውልድ፥ ከብንያም ወገን፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ ነኝ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤
ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ ነበርሁ፤ በሕግ ስለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ ነበርሁ።

ጳውሎስ ራሱ የአብርሃም ዘር በመሆን ይህን ያህል እየተመካ አብርሃምን እንዴት መመካት አይችልም አለው ሲባል ሊታሰብ የሚችለው "ስፍራው" ብቻ ነው። አብርሃም ባመነ ጊዜ የጸደቀው በሰዎች ፊት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ነው። ጳውሎስ ያስተማረው Positional righteuosness እንጂ Ethical righteousness አይደለም። ሰዎች ደግሞ ይህን ጽድቅ በስራም ሆነ በመገረዝ ሊያመጡት አይችሉም። ከዛ በኃላ ሐዋሪያ ጳውሎስ

የያዕቆብን መጽሐፍ መፍቻ ቁልፍ ይሰጠናል እንዲህ በማለት

“እንዴት ተቆጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም፥ ሳይገረዝ ነበር እንጂ።”
— ሮሜ 4፥10

አብርሃም በእግዚአብሔር አምኖ የጸደቀው በዘፍጥረት 15፥6 ላይ ነው የተገረዘው ደግሞ በምዕራፍ 17 ላይ ነው። ስለዚህ አብርሃም ፈጽሞ የጸደቀው በእምነቱ ነው እንጂ በመገረዙ አይደለም። ምክንያቱም ሳይገረዝ በፊት የነበረው እምነት ነው ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት የሚል ነው። እስኪ አሁን ደሞ ይህንኑ አተረጓገም ይዘን የያዕቆብ መልእክት ጋ እንሂድ እስቲ። By the way መጽሐፍ ቅዱስ የተሰወረ መጽሐፍ አይደለም የተሰወረም እንኳን ቢሆን ለሚጠፉት ነው(2 ቆሮ 4፥3)። አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ማንኛውም ክርስቲያን ሊረዳው አይችልም ብለው ሲናገሩ ይሰማል ይሄ የሀይማኖተኞች propaganda ነው። ጳውሎስ እንዲህ ያለው ስለ መልእክቶቹ ሲናገር

“ከምታነቡትና ከምታስተውሉት በቀር ሌላ አንጽፍላችሁምና፤ በጌታችን በኢየሱስ ቀን እናንተ ደግሞ ትምክህታችን እንደምትሆኑ እንዲሁ ትምክህታችሁ እንድንሆን፥ በከፊል ስለ እኛ እንዳስተዋላችሁ ፈጽማችሁ ታስተውሉት ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ።”
— 2ኛ ቆሮ 1፥13-14

ጳውሎስ ልትረዱትና ልታስተውሉት ምትችሉትን እንጂ አክብደን አንጽፍላችሁም እያለ እኛ ሕዝቡን አትረዳውም የምንለው ከሆነ መጽሐፉን ከሕዝቡ ደብቀን የራሳችንን ትምህርት ለማስተማር መንገድ እያመቻቸን ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ አደገኛና ፍርድ ያለው ነው(ገላ 1፥6-10)። የጳውሎስን በፈታንበት በዚያው መንገድ የያዕቆብንም እንፈተዋለን። ቅድም ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚያነሳው " በእግዚአብሔር ፊት" ስለመጽደቅ ነው። ከያዕቆብ መልእክት 2 ውስጥ ግን " በእግዚአብሔር ፊት " የሚል ነገር የለም። ስለዚህ በማን ፊት ነው ብለን ያቆብን ስንጠይቅ እንዲህ ብሎ ይመልሳል

“ነገር ግን አንድ ሰው፦ አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፥ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል።”
— ያዕቆብ 2፥18

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ነገርዬው በእግዚአብሔር ፊት ስለተደረገው ጽድቅ ሳይሆን እኛ ስለምናየው ጽድቅ ነው። ማለትም " ለእግዚአብሔር አሳየው" አላለም " ለእኔ አሳየኝ" ነው እንጂ። ይህ ያዕቆብ ያለው በእግዚአብሔር ፊት ስለምናስቆጥረው ጽድቅ ሳይሆን ሰዎች እኛ ላይ ማየት ያለባቸውን ጽድቅ ነው። ያዕቆብ በጻፈላት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ " አምኛለው አምኛለው " የሚሉ ሐሰተኛ ወንድሞች ነበሩ። ምክንያተቱም ቁ 19 ላይ

“እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።”
— ያዕቆብ 2፥19

መዳን አንድ ፈጣሪ እንዳለ በማመን አይደለም። በእግዚአብሔር ልጅ ማንነትና በሰራልን ስራ በማመን እንጂ( ዮሀ 1፥12, 3፥15-18, 32 , ሮሜ 10፥6-10, ቲቶ 3፥4-8 ...) እና ያዕቆብ ልክ

ያለሆነና ሊያድናቸው የማይችል እምነት ብቻ ይዘው "እናምናለን" እንደሚሉ ይወቅሳቸዋል እንዲህ በማለት

“ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?”
— ያዕቆብ 2፥14

እና ያዕቆብ እውነተኛ ያልሆነውና ሊያድናቸው የማይችል እምነት ብቻ ይዘው "እናምናለን" እንደሚሉ ይወቅሳቸዋል እንዲህ በማለት

“ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?”
— ያዕቆብ 2፥14

ከዛ ደሞ ሐዋሪያው ጳውሎስ እንዳደረገው ማስረጃ ፍለጋ ወደ ብሉይ ኪዳን ገብቶ አብርሃም ያነሳና እንዲህ ይላቸዋል

ያዕቆብ 2
----------

²¹ አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን?
²² እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?

# አብርሃም በእምነት ብቻ ሳይሆን በስራ ጸድቆ እነንደሆነ በምን እነንወቅ ስንለው " የሞሪያን ተራራ " ታሪክ ያመጣልናል (ዘፍ 22) ። ጳውሎስ ቅድም መገረዝ አያጸድቅም ብሎ ምክንያቱም ከጸደቀ በኃላ ነው የተገረዘው ብሎ ነው በም 17 ላይ ያለው ታሪክ የነገረን ታዲያ ዘፍጥረት 17 ላይ የተፈጠረ ታሪክ ከጸደቀ በኃላ ነው ብሎ ጳውሎስ ፈቶልን እንዴት በዘፍ 22 ላይ ያለ ታሪክ ለመጽደቅ Criteria ተደርጎ ይቀመጣል ተብሎ ይታሰባል። በፍጹም አይደለም አይልምም።

አብርሃም የጸደቀው በ 75 አመቱ ገደማ በምዕ 15
አብርሃም የተገረዘው በ 90 አመቱ ገደማ በምዕ 17
አብርሃም ይስሀቅን ለመሰዋት የወሰደው በ 125 አመት ገደማ በምዕ 22

- አብርሃምን ለማጽደቅ ከይስሀቅ መስዋህት ይልቅ ግርዘቱ ይቀርባል። በጳውሎስ ሮሜ 4 አፈታት መሰረት መገረዝ ፍጽሞ በእግዚአብሔር ፊት የመጽደቅ መንገድ ካልሆን በዘፍ 22 ላይ ያለውም ታሪክ የመጽደቂያ መንገድ እንዳልሆነ እንረዳለን።

* ታዲያ የጌታ ወንድም ያዕቆብ መልእክቱ በቀጥታ እውነተኛ የአብርሃም እምነት የሌላቸውን ሐሰተኛ ወንድሞች መሀከል አድርጎ " የእምነታቹ ልክ አለመሆን ያለፍሬ አስቀርቶአችኃል" በማለት ይሟገታቸዋል። የዛፉ ስር ልክ ስላልሆነ ዛፉ ደርቋል ይላቸዋል።

# ስለዚህ ያዕቆብ ሚላቸውን ነገሮች ተመልከቱ ከዛ

“እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?”
— ያዕቆብ 2፥22

እምነቱ በስራ እንደተፈጸመ ተመልከት የሚለው "በእግዚአብሔር ፊት" አይደለም ምክንየያቱም ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ እምነቱን በስራ ፍጹም ለማድረግ የሚጥር ሰው በጳውሎስ ተወግዟል

“እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጸማላችሁን?”
— ገላትያ 3፥3

*ያዕቆብ እግዚአብሔር ያመነውን እምነት በስራችን ያረጋግጥልናል እያለ አደለም ያን ትምህርትማ ጳውሎስ አውግዞታል(ገላ3፥3) እግዚአብሔር እምታችንን በስራ አያረጋግጥም እርሱ ሁሉን በሚያውቀው እውቀቱ እምነታችንን ባመንበት ቅጽፈት ያረጋግጣል ለዛ ነው ባመንበት ቅጽፈት የዘላለምን ሕይወት የሰጠን። (1 ዮሀ 5፥11-12)::

# በቤተ ክርስቲያነን ውስጥ ያሉ ሰዎች ግን እምነትን የማየት አቅም ስለሌላቸው በስራችን እምነታችንን እንገልጥላቸዋለን ወይም እናሳያቸዋለን። (ያዕ 2፥18)።

# ሲቀጥል

“ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።”
— ያዕቆብ 2፥24

-ይሄም ጥቅስ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት መውሰድ ያዕቆብም መንፈስ ቅዱስም ያላስተማሩትን እንግዳ ትምህርት ማስገባት ይሆናል። እኛ ክርስቲያን ወንድሞች አምኛለው ስላልክ ብቻ መጽደቅህን አናረጋግጥልህም። ይልቅስ እምነቱ የአብርሃም አይነት ከሆነ የአብርሃምን አይነት ስራ ሲሰራ መጽደቁን ታያላችሁ እንጂ እግዚአብሔር ያየዋል አላለም። ከተጻፈው አለማለፍ የሐዋሪያቱን መንገድ መከተልና መሰረቱን በእነርሱ ትምህርት ላይ ብቻ መገንባት ነው።

“ወንድሞች ሆይ፥ ስለ አንዱ በአንዱ ላይ አንዳችሁም እንዳይታበዩ፡- ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክንያት ስለ ራሴና ስለ አጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ።”
— 1ኛ ቆሮንቶስ 4፥6

# የያዕቆብና የሮሜ መልእክታት የሚለው ትምዕርት እዚህ ጋ ያበቃል።

“የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።”
— ሮሜ 16፥24

በእግዚአብሔር ልጅ ያገኘነው ሕይወት ዘላለማዊና የማይቋረጥ ስለመሆኑ የቅዱሳት መጽሐፍት መሀከላዊ አስተምሮ ነው። የትኛውም ክርስቲያን ግለሰብ ስለመዳንና አለመጥፋት ለማወቅና ለሌሎች ለማሳወቅ ሲነሳ የሚቀጥሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት

## 1. የእግዚአብሔር ምክንያት አልባ ፍቅር (ዮሐ 3፥14-16)

ዮሐንስ 3

---

14-1 ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።
1 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

የሰው ዘር ሁሉ ከገባበት የኃጢአት ቅጣትና ውጤቶቹ ሁሉ ነጻ ወጥቶ መዳንን የሚቀበለው በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ማንነትና ስራ ብቻ እንደሆነ ቅዳሳን መጽሐፍት ያለማንገራገር ያስረዳሉ(ሮሜ 10,ሐሥ 4፥12,ዮሐ 14፥6)። የአባቶች ተስፋ የሆነው መሲሕ ከሰማይ ወርዶ በሚከፍለው ዋጋ በኩል የሰዎች ድነት እንደሚፈጸመ ከአዲሳት በተጨማሪ የብሉይ መጽሐፍት በግልጽ ያውጃሉ( ኢሳ 53, መዝ 22)።እነዚህ መጽሐፍት መሲሑ በውርደት እንደሚመጣና በክብር እንደሚያርግ ጨምረው ሲያውጁ በሰውነቱ በኩል የሚሰሩ ስራዎቹ ሁሉ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ ኃጢያታችንን ከእኛ ለማራቅና ምስራቅ ከምህራብ እንደሚርቅ በደላችንን ከእኛ ለማስወገድ ከሕያዋን መንደር በግፍ እንደሚወገድ ተተንብዮአል(መዝ 103፥11-13)።ስለ ሰው ልጆች የተከፈለውን ዋጋ ስናስብና የአምላክን በዛ ልክ ተዋርዶ እንደ ትቢያ የሆነውንና ለተደረገለት መልካምነት እንኳን መመለስ የማይችለውን ጨለማ ፍጥረት ለማዳን የተኬደበት መንገድ እጅግ ጥልቅና በፍጥረታዊ አምእሮ ለማብራራት የማይቻል ነው።የዚህ ሁሉ ስር ምክንያት አልባው ፍቅር(አጋፔ) ነበር።

ይህ ታላቅ ፍቅር ከተቀባዮቹ አዎንታዊ ምላሽ ባይሰጠው እንኳን እየወደደ የሚሚወድ መሆኑ በመስቀል ላይ ያህ የእግዚአብሔር በግ ለፈወሳቸውና ላበላቸው ኃላ በምላሹ ግን ለሚገድሉት ለክፉ ሰዎች እንደ ንጉስ ዳዊት የተበቀላቸው ጩኸት ሳይሆን በፈሰሰው ደም በኩል ይቅር በላቸው የሚል የምልጃ ጩኸት ሲያስተጋባ፤ ያኔ ነው በርግጥ በኢየሱስ በኩል ዋስትና እንዳለ ያረጋገጥነው። ምክንያቱም የወደደን ስለወደድነው ሳይሆን እርሱ ፍቅር ስለሆነ ነው። ገና ኃጢያተኞች ሳለን እንዲሁ ወደደን(ሮሜ 5፥1፥11)።

**"እርሱ እኛን ያለምንም ምክንያት ወደደን፤ እኛ ግን እርሱን በበቂ ምክንያት እንወደዋለን"**

**(1 ዮሐ 4 ፥19)**

"የፈሰሰውን ፍቅር እንደ ባህር ነው ብለን አንገልጸውም
ምክንያቱም የባህር ስፋቱና ከፍታው ይታወቃልና
ደግሞም እንደወንዝ ነው ብለን አናሳንሰውም
የወንዝም ከፍታውና ጥልቀቱ ይለካልና።
የእርሱ ፍቅር ከፍታው ልኬት የለውም
ትልቁ እግዚአብሔርን ወደምድር አውርዶታልና
ደሞም ጥልቀቱ መለኪያ የለውም
ኃጢያተኛውን ከጥልቁ አውጥቶ ሰማይ ከቶአልና።
የስፋቱም ርዝማኔ ከመታወቅ ይልቃል
አምላክየለሹን ባለአባት ተስፋ የለሹን ባለሕያው ተስፋ አድርጓልና።
( ኤፌ 3, ሮሜ 10 ,1 ጴጥ 1፥3)

የክብር ሁሉ ምንጭ የሆነውን እርሱን ክብር አሳጥተውት እየሰደቡትና እያሾፉበት ስጋው ከአጥንቱ ተለያይቶ እየረገፈ በመጽሐፍ "አጥንቴ ተቆጠሩ" እንደሚል ደሙም በምድር ላይ ያለማቋረጥ እየፈሰሰ ተሰብስበን ላጠፋነው ጥፋት ብቻውን እየከፈለ ስለሁላችን በደል ቅዱሱ በሰማይ ቁጣ እየተጠበሰ ግን ለጠላቶቹ ያለማቋረጥ የልቡ ፍቅር ይፈስ ነበር።እንደወንዝ ብላችሁ አታሳንሱት ተቀባይ ባይኖረው እንኳን ያለማቋረጥ ወደሸለቆ ወርዶ ወደ ተራራ ይወጣል። በእግዚአብሔር ፍቅር ጥርጣሬ ውስጥ ገብተህ ለዲያቢሎስ እድል ፈንታ አትስጠው "የወደደህ እስከመጨረሻ ወዶሀልና(ዮሐ13፥1)" ።

“የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።”
— 1ኛ ዮሐንስ 3፥1

በዮሐ 3፥14-16 ባለው ክፍል መሰረት ድነት ወይም የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በመስቀሉ ስራ እንደሆነ ኢየሱስ በዘኁልቁ መጽሐፍ የተጻፈን የእስራኤልን ታሪክ አንስቶ ያብራራላቸዋል።የእስራኤል ሕዝብ በምድረበዳ በእግዚአብሔር ላይ ሲያምጽ በክፉ እባብ ተነድፈው በመሞት ላይ ሳሉ እግዜሩ ለሙሴ የናስ እባብ ሰርተህ ስቅል የተነደፈው ሁሉ የተሰቀለውን ባየ ጊዜ ይድናል የሚል ምሳሌያዊ ወንጌል ሰበከ (ዘኁ 13) እንዲሁ ደግሞ በመጀመሪያው በአዳም እንጨት ፍሬ ምክንያት የሚጠፋው የሰው ዘር በኃለኛው አዳም መሰቀል ፍሬ በኩል ወደ ድነት እንደሚመጣ መሲሁ ራሱ ያውጃል።በእርግጥ የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች መዳን በእግዚአብሔር ልጅ ማንነትና ስራ እንደሆነ አይጠራጠሩም ግን አለመጥፋት ጋ ሲመጡ ራሳቸውን ያስገቡና እንዲህና እንዲያህ ካላደረኩ ግን እጠፋለው ወይም ላልድን እችላለው ብለው ይመልሳሉ።በዚህ ክፍል ላይ ግን ኢየሱስ ለሕግ መምህሩ ኒቆዲሞስ ሲያስተመረው መዳንን ብቻ ሳይሆን አለመጥፋትንም ጨምሮ የሚገኘው በመስቀል ላይ በተሰራው ስራ ብቻ እንደሆነ ያስረግጥለታል።

" መዳናችን ብቻ ሳይሆን የአለመጥፋታችንም ዋስትና የተንጠለጠለው

በክርስቶስ የመስቀል ስራ ላይ ብቻ ነው።"
" የዳንበት ፍቅር የሁለትዮሽ ፍቅር አይደለም ያለምንም ምክንያት ከአንድ አቅጣጫ ወደ ሁሉ የሚፈስ እንጂ። እንደባለትዳሮች ሰውና እግዚአብሔር ተስማምቶ አልተዋደደም።" መጽሐፍ ፍቅርን ሲያብራራው እንዲህ በማለት ነውና "ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።"
— 1ኛ ዮሐንስ 4፥10

ብዙ ሰው ግን እንዲህ አያስብም ከእንግዲህ ግን እስቲ እንደ ቃሉ እናስብ። ይህ ፍቅር የሁለትዮሽ ባለመሆኑ ኃይሉም የሚመሰረተው ፍቅሩን በሚሰጠው ላይ ብቻ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ የዚህን ፍቅር ኃይል ሲያስረዳ እንዲህ በማለት ነበር

ሮሜ 8
----------

3□ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?
3□ ስለ አንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።
3□ በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።
3□ ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥ የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥
3□ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።

ክፍሉ በትክክል ከተነበበ የሚለው ኃያልና ብሩቱ ፍቅሩንም ከሰጠን ከአሸናፊው አምላክ ከእርሱ በሰውነታችን ላይ የሚመጣ ማንኛውም ለውጥ ፣ በስፍራችን ላይ የሚከሰት ማንኛውም ነውጥ እኛ ደካሞችን የሚነጥል ኃይል የለም ይለናል ሐዋሪያው ምክንያቱም በቁ 26 ላይ ደካሞች እንደሆንን ጽፎልናል። በሌላ ቋንቋ ስንገልጸው ከእግዚአብሔር ጋር አለተያያዝንም እርሱ እኛን ያዘን እንጂ።

ዮሐንስ 10
----------

2□ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።
2□ የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።

የትኛውም ሰማያዊው ቢሆን ምድራዊ ኃይል እግዚአብሔር በክርስቶስ ለኛ ካለው ፍቅር እኔን ደካማውን መለየት አይችልም። ምክንያቱም የፈሰሰው ፍቅር ከፍጥረት ኃይል በላይ የሆነው የፈጣሪ ባህሪ ነውና።

ይህ ታላቅ ፍቅር ከአንተ ብቻ ዘንድ ለፈሰሰ እግዚአብሔር አብ ፤ በአንተ ብቻ በኩል ደግሞ ለተሰጠ እግዚአብሔር ወልድ ፤ ለአንተ ብቻ ሆኖ በእኛ ውስጥ ላፈሰስክ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ኃይልም ባለጠግነትም ተጠቅልሎ ኃያል ለሆነው ስም ይሁን። አሜን።

" አስቀድመ ስለወደድከን እንወድሀለን "

## 2. የተገኘንበት አባት

አባት የሚለው ቃል av ከሚለው የሂብሩ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙ ምንጭ ወይም መገኛ እንደማለት ነው። እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በመልኩና እንደ ምሳሌው አድርጎ ወደ ሕልውና አምጥጦት(መንፈሱን) የሕያውነተ እስትንፋስን እፍ አለበት(ነፍስን) በመጨረሻ ከምድር አፈር አበጀው(ስጋውን)። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በመገኘቱ የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ። ነገር ግን ይሄንን የከበረ የአባቱን መልክና አምሳል ይዞ ለዘላለም መኖርን ባለመምረጡ በሀጢያት ጨለማ ውስጥ ወደቀ ባለመታዘዝ መንገድ። ይሄን ተከትሎ የተገኘበት ስር ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ ከሕይወት ወደ ሞት፣ ከበረከት ወደ መርገም ገዢ ሆኖ የተፈጠረበትን አለም ሁሉ ይዞ ወረደ። ያንን የከበረ የብርሃናት አባትን መልክ ትቶ በራሱ መልክ ልጆችን መውለድ ጀመረ(ዘፍ 5፥3) ።

የሰው ልጆች ሁሉ አባት የሆነው የመጀመሪያው አዳም ኃጢያትንና መዘዙን ጎትቶ በዘሩ ውስጥ ከተተው። ከዚህም የተነሳ ገና ከፍጥረታችን(ማለትም ከአባታችን) የቁጣ ልጆች ተባልን(ኤፌ 2፥1-3)። ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲያብራራው በአንዱ አለመታዘዝ ምክንያት የሰው ልጆች ሁሉ በኃጢያትና በሞት ስር ተገዢ እንደሆኑ በሮሜ መልእክቱ ያብራራልናል።

ሮሜ 5
----------

12 ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤
13 ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤
14 ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።
1□ ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።
1□ አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ።

[1]□ በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።
[1]□ እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።
[1]□ በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።
[2]□-[21] በደልም እንዲበዛ ሕግ ጭምር ገባ፤ ዳሩ ግን ኃጢአት በበዛበት፥ ኃጢአት በሞት እንደ ነገሠ፥ እንዲሁ ደግሞ ጸጋ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተነሣ በጽድቅ ምክንያት ለዘላለም ሕይወት ይነግሥ ዘንድ፥ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በለጠ።

የሰው ልጆች ሁሉ ከአዳም በመገኘታቸው ብቻ ሀጢያተኞችና የሞት ምግቦች እንደሆኑ ሐዋሪያው ይነግረናል። እጅግ በጣም ጥሩ ሰዎች ሆንም ደግ ሰዎች በአዳም ምክንያት ኃጢያትና ሞት እጣ ፈንታችን ሆኖአል "በአንድ ሰው በደል ብዙዎች ሞተዋልና" ቁ 15 ተብሎአል። ምክንያቱም አዳም የሁሉ አባት(ምንጭ) ነውና። ወንዙ ከምንጩ መርዛማ በመሆኑ ወራጅ ወንዙ ሁሉ በመርዝ ተሞልቶአል። ለዚህ ችግር መፍትሔ የእግዚአብሔር እርምጃ ሌላ አዳም መላክና ሌላ ምንጭ መክፈት ነበር።ስለዚህ አባት(ምንጭ) ለመቀየር እግዚአብሔር የራሱ ዘር ያለበትን ልጁን ላከ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከብርሃን የተገኘ እውነተኛ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነውና እርሱ ለዘላለም የማይጠፋ ዘር ነው። የመጀመሪያው አዳማ ከመሬት መሬታዊ ነውና ጠፊ ነው። የኃለኛው አዳም ግን ከሰማይ ሰማያዊ ነውና ለዘላለም ሕያው ሆኖ ይኖራል።የሰው ልጅ ክርስቶስ ኢየሱስን በተቀበለ ጊዜ የሚቀይረው ጸባይ ሳይሆን ዘር ነው። እውነተኛ አማኝም በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ዘር ተካፋይ ሆኖአል
“ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።”
— 1ኛ ዮሐንስ 3፥9

የእግዚአብሔር ልጅ ዘር በእውነተኛ አማኝ ውስጥ መኖሩ በረከቶቹ ብዙ ሲሆኑ አንዱ ግን አለመጥፋት ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዘር አይጠፋምና። አማኞች በክርስቶስ ናቸውና ለዘላለም ከማይጠፋ ዘር ተወልደዋል።

“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።”
— 1ኛ ጴጥሮስ 1፥23
መጽሐፉ በግልጽ የተገኛቹበት ዘር(አባት) የሚጠፋ አይደለም ለዘላለም ሕያው ሆኖ የሚኖር የማይጠፋ ዘር ነው። የማይጠፋ ዘር ማለት ምን ማለት ነው? የማይጠፋ ዘር ማለት ነዋ!!! ስለዚህ ለዘላለም ከማይጠፋ ዘር ተወልደናልና ለዘላለም አንጠፋም።

## 3. የአዲስ ኪዳኑ መልካም እረኛ

የእረኝነት ትምህርት ሲነሳ ሁሌም የሚነሳው ንጉስ ዳዊት ነው።ንጉስ ዳዊት የበጎች እረኛ ነበር።
1ኛ ሳሙኤል 17
----------

34 ዳዊትም ሳኦልን አለው፦ እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፥ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር።
3□ በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፥ ከአፉም አስጥለው ነበር፤ በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር።

ትንሹ ዳዊት በጎችን በሚጠብቅበት ጊዜ አንበሳና ድብ ማለትም የጨለማ ሀይላት(1 ጴጥ 5) ከጠቦቶቹ መካከል በመንጠቅ ይወስድ ነበር። እኔ ግን ተከትዬው አስጥለው ነበር አለ። ትንሹ ዳዊት እንኳን በጎቹን አሳልፎ ለአውሬ አይሰጥም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ደሞ የዳዊት ልጅ ነው።እርሱን የዳዊት ልጅ ስንል ከዳዊት ያንሳል እያልን አይደለም ስለዙፋን እየተናገርን እንጂማ እርሱ ኮ የዳዊት ጌታና አምላክ ነው።
ማቴዎስ 22
----------

41-42 ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ፥ ኢየሱስ፦ ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው። የዳዊት ልጅ ነው አሉት።
43-44 እርሱም፦ እንኪያስ ዳዊት፦ ጌታ ጌታዬን፦ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል?
4□ ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው፥ እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው።

“እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።”
— ራእይ 22፥16

እንግዲህ ከትንሹ ዳዊት እጅ እንኳን አንድም በግ በአውሬ ካልተበላና ዳዊት ካስጣላ የእውነተኛው ዳዊታችን እረኛ ከሆነን ከክርስቶስ እጅ ሊነጥቀን የሚችል ማነው? የትኛውስ ሀይል? ምንም በጎቹ ደካማና አቅመ ቢስ ቢሆኑ እረኛቸው ግን ታላቅ ነው።እርሱም ቅጥረኛ እረኛ አይደለምና በጎቹን ለአውሬ አይሰጥም።ክርስቶስ መልካም እረኛ ነው። እንጠፋለን ብላችሁ የምታስቡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ያንሳል እያላችሁ ነው እርሱ ግን ከዳዊት ይበልጣል።ከእርሱ ዘንድ በጎችን ነጥሎ የሚወስድ ሀይል የለም።

ዮሐንስ 10
----------

2□ እናንተ ግን እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም።
2□ በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤
2□ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም

ማንም አይነጥቃቸውም።
[2]□ የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።

ኢየሱስ ለዘላለም አይጠፉም ያለው እኛን ታምኖ ይመስላችኋልን? ወይስ የዘላለም ክክንዶቹን? አባት ሆይ በክርስቲያኖች መካከል ታላቁ እረኛችንን ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን አክብረው!!!

“እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።”
— 1ኛ ጴጥሮስ 2፥25
ወደዚህ ታላቅ የነፍስ እረኛ መመለሳችሁን እርግጠኛ ሁኑ እንጂ እርሱ ፈጽሞ የሚያጠፉ አይደለም።

## 4. የሚሻለው ኪዳን ዋስ

እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው በምድረበዳ ሳሉ እግዚአብሔር አንድ ድንቅ ትምህርት አስተማራቸው። ከየነገዱ ለሌዋውያን የሚሆኑ 6 ከተሞች አዘጋጁና ስጡአቸው።እነዚያም ከተሞች የመማጸኛ ከተሞች ይሁኗችሁ። እነዚህ 6 ከተሞች አንድ እስራኤላዊ ሳያውቅ ኃጢያት በሰራ ጊዜ ሸሽቶ የሚያመልጥባቸው ከተሞች ነው ይህ የመማጸኛ ከተማ አንድ ሳያውቅ ሰው የገደለ እስራኤላዊ ከተበቃዩ የሚያመልጡባቸው ከተሞች ናቸው።እግዚአብሔር እስራኤላዊው ሸሽቶ ወደ መማጸኛ ከተማ በገባ ጊዜ ነፍሱ ከጥፋት ትድናለች።የመዳኛ መንገዱ ሸሽቶ ወደ ከተማው መግባት ነው። በአዲሱም ኪዳን መዳኛ መንገዱ ሸሽቶ ወደ አማናዊው የመማጸኛ ከተማ መምጣት ነው።እርሱ የነፍሳችን መልዕቅ ነውና። ስዎች ሁሉ ከአጥፊው ሸሽተው ወደ ቅዱሱ ከተማ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አለባቸው።
ዕብራውያን 6
----------

[1]□-[1]□ ስለዚህም እግዚአብሔር፥ የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደ ማይለወጥ አብልጦ ሊያሳያቸው ስለ ፈቀደ፥ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር፥ በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ፥ በመሓላ በመካከል ገባ፤
[1]□ ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው፤

ያንን ታላቅ የመዳን ተስፋ ለመያዝ ወደ አዲሱ ኪዳን የመማጸኛ ከተማ እንደሸሸን ሐዋሪያው ጳውሎስ ያስተምረናል።ይህ ማለት የአዲስ ኪዳም የመማጸኛ ከተማችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው።ወደ መማጸኛ ከተማ የሸሸው ኃጢያተኛው እስራኤላዊ በዛች ከተማ ውስጥ በኖረ ዘመን ሁሉ ነፍሱ ከጥፋትና ከሞት የተጠበቀች ትሆናለች። ይህ ኃጢያተኛ እስራኤላዊ እስከመቼ ድረስ በመማጸኛ ከተማ ውስጥ መቆየት ይችላል?
“በማኅበሩ ፊት ለፍርድ እስኪቆም ድረስ፥ በዚያም ወራት ያለው ታላቁ ካህን እስኪሞት ድረስ በዚያች ከተማ ይቀመጥ፤ ከዚያም ወዲያ ነፍሰ ገዳዩ

ይመለሳል፥ ወደ ከተማውም ወደ ቤቱም ሸሽቶ ወደ ወጣባትም ከተማ ይገባል።”

— ኢያሱ 20፥6

መጽሐፉ እንደሚነግረን የኃጢኡ እስራኤላዊ በከተማ ውስጥ የመቆየቱ ተስፋ በከተማ ውስጥ የሚያሳየው ጥሩ ጸባይና መልካም ምግባር ሳይሆን የዚያት ከተማ ታላቁ ካህን(ሊቀ ካህናት) በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው።በዚያህ ወራት ያለው ሊቀ ካህናት ከሞተ ያህ ኃጢኡ እስራኤላዊ ከከተማው እንዲወጣ ይደረጋል ከከተማው ከወጣ በኃሏ ግን ነፍሱ ዋስትናዋን ታጣለች። በከተማ ውስጥ የመቆየት ተስፋው በዘመኑ ያለው ሊቀ ካህናት ነው።ያህ ሊቀ ካህናት የኃጢኡ እስራኤላዊ የነፍስ ዋስትና ነው።

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ደካሞችና ሟቾች ስለነበሩ ወደ ከተማዋ የሚገባ እስራኤላዊ ዋስትናው ለጥቂት ጊዜ ብቻ ነው። የአዲስ ኪዳኑን ሊቀ ካህናት እንመልከት እስቲ

ዕብራውያን 7
-----------

22 እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።
23 እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤
24 እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤
2 ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።

የአዲሱ ኪዳን ሊቀ ካህናት የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው።እርሱ የኪዳኑ ዋስ(ዋስትና) ነው።ሐዋሪያው ጳውሎስ እርሱ እንደ ብሉይ ኪዳኖቹ ሊቃነ ካህናት የሚሞትና ወደ እርሱ ለገቡ የሚሰጣቸው ዋስትና ጊዜአዊ አይደለም። እርሱ ለዘላለም በሕይወት ስለሚኖር የትኛው ኃጢያተኛ ወደዚህ ከተማ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ነፍሱ የዘላለም ዋስትንና አግኝታለች። እውነተኛ አማኝ የማይጠፋበት ምክንያት የአዲስ ኪዳኑ ሊቀ ካህናት የናዝሬቱ ኢየሱስ ለዘላለም የማይሞት ስለሆነ ነው።

፡በመጨረሻም የዘላለም ህይወት የሚጠፋ ሕይወት አይደለም የዘላለም ህይወት ያገኘ ሰው የዘላለምን ሞት አይሞትም (ዮሐ 3፡15፣ ዮሐ 16፡34፣ ዮሐ 5፡24)። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገር እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። (አንድ ጊዜ የተሸገረ ሰው ተመለሶ ወደ ፍርድ አይመጣም (1የሐ 5፡10-13 , 1ጳጥ 1፡3-5)።

በጌታ በኢየሱስ በማመን የተወለደ ሰው ከተወለደ በኋላ አለመውለድ ወይም መሞት አይችልም። ዳግመኛ በመወለድ አዲስ ፍጥረት የሆነው ሰው ተመልሶ አሮጌ ፍጥረት ሊሆን አይችልም (1ጴጥ 1፡23,ያዕ 1፡18,ዮሐ 1፡3,2ቆሮ 5፡17)።

ያዳነን የዘላለም ህይወት በጸጋው የሰጠን እግዚአብሄር እስከ መጨረሻ ሊጠብቀንና መንግስቱን ሊያወርሰን የታመነ ነው (ሮሜ 8፡29-30) ፣1ቆሮ 1፡8-9

፣ፊል 1፡6)። እግዚአብሔር ከእርሱ የሚለየን እንደማይኖር በቃሉ አስረግጦልናል (የሐ 10፤1-7 ፤10፡28-29 1ጴጥ 1፡5 ፤ ዕብ 13፡20-21 ፤ሮሜ 8፡37-39 ።ድነትን ያገኘ ሰው ኃጢያት እየሰራ አይኖርም (ዮሐ 3፡4፣2ቆሮ5፡18፣ ኤፌ 2፡10)። ድነትን ያገኘ ሰው በተሰጠው በእግዚአብሄር ፀጋ ይኖራል (ሮሜ 12፤1-2፣ ርሜ 10፡1-3)። ደህንነታችን ዘላለማዊ ነው።

▸ በዘላለም ዋስትና ብዙውን ጊዜ የሚነሳው ተቃውሞ ይህ አስተምህሮ ሰዎች

ድነታቸውን ስለማያጡ እንደፈለጉ እንዲኖሩ ፈቃድ ይሰጣል ወይንም በሀጥያት መኖር ይችላሉ የሚል ነው። ይህ ደግሞ ስናየው እውነት ቢመስልም መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም። አንድ ሰው በእውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ከተዋጀ ሀጥያትን ልምምድ ያደረገ ህይወት አይኖረውም።መፅሀፍ ቅዱስ ደህንነት በፀጋ ብቻ፥ በእምነት ብቻ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ይነግረናል።
( ኤፌ ምዕ. 2)
8፤ ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤9፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
➡ ሰው በእውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ባመነበት ቅፅበት ድኗል እንደገናም ደህንነቱም ዋስትና አግኝቷል። ነገር ግን አንድ ሰው ድነት በእምነት ነው የምቀበለው ካለ በኋላ ፀንቶ ለመኖር መስራት አለብን ቢል ይህ መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

à ጳውሎስ በገላቲያ መልዕክቱ

" እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጸማላችሁን? "(ገላትያ 3:3)

በእምነት ከዳንን ድነታችን ፀንቶ የሚኖረው እና ዋስትና የሚያገኘው #በእምነት ብቻ ነው። ድነታችንን በራሳችን ጥረት ማግኘት አንችልም። ስለዚህ ድነታችንን በራሳችን ጥረት ማፅናት አንችልም።
✝ እግዚአብሔር ብቻ ነው ድነታችንን ማፅናት የሚችለው። ( ይሁዳ 24)
✝ የእግዚአብሔር እጅ ነው ማንም እንዳይወስደን አጥብቆ የያዘን።( ዮሀንስ 10:28~29)
✝ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው ማንም ከእርሱ ሊለየን እንዳይችል ያደረገው ( ሮሜ 8:38~39)
➡ በዘላለም ዋስትና(ያለመጥፋት) ላይ የሚነሳ ማንኛውም ተቃውሞ ድነትን በሰው ጥረት እና አቅም የሚፀና እንደሆነ ማመን ነው።ይህ ደግሞ በፀጋ መዳን ከሚለው ጋር የሚጋጭ ነው። ምክንያቱም የዳንነው በኢየሱስ መልካምነት እንጂ በእኛ መልካምነት አይደለም።(ሮሜ 4:3~8)... ድነታችንን ለማፅናት/ላለመጥፋት የሙሴ ሕግ መጠበቅ ወይንም መስራት አለብን ማለት የኢየሱስ ሞት ለእኛ ሀጥያት በቂ ክፍያ አይደለም ማለት ነው።
#የኢየሱስ ሞት ግን ላለፈው ፥ላሁኑ እና ለወደፊቱ ሀጥያታችን የተከፈለ ከ በቂ በላይ የሆነ ዋጋ ነው። (ሮሜ 5:8 ;1ቆሮ 15:3 ; 2 ቆሮ 5:21)
⁀ ታዲያ ይህ ማለት አንድ ክርስቲያን እንደፈለገው መኖር ይችላል ማለት ነውን?
à መፅሀፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ መልሱ ክርስቲያኖች እነሱ እንደፈለጉ ሊኖሩ አይችሉም የሚል ነው።

˚ ክርስቲያኖች አዲስ ፍጥረት ናቸው።( 2 ቆሮ 5:17)
˚ ክርስቲያኖች የመንፈስ ፍሬዎች የሚገለጥባቸው ናቸው።( ገላ 5: 19~21)
˚ ክርስቲያኖች ሀጥያትን እንደልምድ አርገው ሊኖሩ አይችሉም።( 1 ዮሀ 3:6~9)
►ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለዚህ ነገር ሲናገር ፥ ( ሮሜ ምዕ. 6)
1፤ እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ #በኃጢአት_ጸንተን እንኑርን? #አይደለም።2፤ ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?
►ስለዚህ የዘላለም ዋስትና የሀጥያት ፈቃድ ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ ለሚያምኑ ለዘላለም እንደሚኖሩ የሚያረጋግጥ ዋስትና ነው።የእግዚአብሔርን ውድ የድነት ስጦታ ማወቅ እና መረዳት ለሀጥያት ፈቃድ ከመስጠት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።
( ሮሜ ምዕ. 6)14፤ ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።

# ምዕራፍ ሦስት

# በዘላለም ሕይወት ዋስትና ላይ ጥያቄ የሚያስነሱ የሚመስሉ ጥቅሶች ከነማብራሪያቸው

በዚህ ምዕራፍ ላይ ደግሞ የዘለለም ሕይወት የማይጠፋና ማንነት የሆነ አካል እንደሆነና እውነተኛ አማኞች እስከመጨረሻ የዳኑ እንደሆነ የሚያስረግጠውን ታላቁን ወንጌል ከመሰረተ ሃሳባቸው በወጡ ጥቅሶች ዋጋ ሊያሳጡ የሚፈልጉ ሰዎችን ወደ ቅዱሳት መጽሐፍት አስተምሮ እንመለስ።

1. ማቴዎስ 7

21 በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።
22 በዚያ ቀን ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።
23 የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።

ጌታችን ኢየሱስ የተናገረው ወርቃማ ንግግር ነው። ይህ ቃል እውነተኛ አማኞችን ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን ይልቅስ የሚያበረታ ነው። እንዴት? ይህ ቃል በማቴዎስ ወንጌል በተራራ ላይ የተሰበከ ሲሆን ይሄን የሚመስል ስበከት ደግሞ ጌታችን በሜዳ ላይ ሰብኮአል ይህ ደሞ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ተጽፎአል። በጌታችን ሁለት ጊዜ የተሰበከ ስብከት እጅግ አስፈላጊ ቢሆን ነውና ሁላችን እስኪ እናጥናው።

ሁሉም ሰው ግን ሊረዳው የሚገባው ነገር
“የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።”
— ሮሜ 10፥13

ሐዋሪያው ጳውሎስ የጌታን ስም የሚጠራ አንዳንዱ ሳይሆን ሁሉ ይድናል ይላል።የጌታ ስም ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በአጭሩ ጌታዬ ጌታዬ የሚል ሁሉ ሳይሆን የሚድነው "እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የሆነውን የናዝሬቱን ኢየሱስ" የሚጠራ ነው።

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 5 እስከ 7 ድረስ በተራራ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እውነተኛ ማንነትና ያህ ማንነት ደግሞ በፍሬው እንደሚታወቅ በምሳሌ ያስተምራቸዋል።በመጀመሪያ "የበግ ለምድ የለበሱ ተኩሎች" ይላል። እነዚህ ሰዎች ሲጀመርም በግ አልነበሩም ግን በበጎች መካከል ያሉ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩሎች ናቸው ማለትም ከዳኑ በኃላ ቆይተው በድካማቸው ምክንያት የጠፉ ሳይሆኑ ቀድመውም በጎች ያልሆኑ ናቸው። ሲቀል መልካም ዛፍ ና ክፉ ዛፍ ብሎ ያስተምረናል። መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ አያፈራም ክፉም ዛፍ መልካም ፍሬ አያፈራም።ጌታ ያለው መልካም ዛፍ ወይስ ክፉ? ነው እንጂ ያለው መልካም ዛፍ ሆኖ ክፉ ፍሬ የሚያፈራ ፈጽሞ አይድንም እያለ አይደለም። የኢየሱስን ትምህርት በትክክል ከተረዳነው እያወራ ያለው ስለውስጠኛው ሰውነት ነው እንጂ ለስውጫዊ ባህሪ አይደለም። ስለዚህ ውጫዊ ስርዓትና ስነ ምግባር ላይ ትኩረት የሚያደርጉትን አይዶች(ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን) ውስጣዊ ማንነታቹ መታደስን(ዳግም ውልደትን) ማግኘት አለበት እንጂ በውጫዊ ስርዓት መፎጋገር ቀርቶአል ይላቸዋል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ውስጣዊ ማንነታቸው ሳይለወጥ(ዳግም ሳይወለዱ) ግን በእውነተኛ አማኞች(በበጎችና በመልካም ዛፎች) መካከል ስለገቡ አፋዊ አማኞች(ተኩሎችና ክፉ ዛፎች) የተናገረው ነው። እነዚህ ሰዎች በቅዱሳን መካከል የሚኖሩ ናቸው አማኝ ይመስላሉ ግን አይደሉም። እነዚህ ሰዎች ከጨለማው መንግስት ጋር በሕብረት የሚሰሩ የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለባቸውና የክርስቶስ ወገን ያልሆኑ ናቸው። ሐዋሪያው ይሐንስ ስለነዚህ ሰዎች ሲናገር እንዲህ አለ

1ኛ ዮሐንስ 2
-----------

[1] ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ።
[2] እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ።

እነዚህ አፋዊ አማኞች በመካከላችን የነበሩ ናቸው ግን ጊዜው ሲደርስ ወይም ጌታ ሲመጣ መለየት ይሆናል። ነገር ግን ከጸጋ ጎድለው አቅም አተው በኃጢያት ውስጥ የሚኖሩ አማኞች ለዘላለም ላይጠፉ በአብና በወልድ እጅ ተይዘዋል።

ኢየሱስም በጽናት የአባቴን ፈቃድ አድርጉ ብሎ ያዛቸዋል። ይህ የአባቱ ፈቃድ ምንድነው? ብለን መጠየቅና የቅዱሳት መጽሐፍትን መልስ መጠበቅ ያሻናል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የአብ ፍቃድ ብለን ራሳችን የምንሞላው ከሆነና ያልተባለውን የምንል ከሆነ እንስታለን። እግዚአብሔር አብ በአዲስ ኪዳን የሁለትዮሽ ፈቃዱን ገልጦአል

1. ልጁ ኢየሱስ ይፈጽመው ዘንድ የተሰጠው የአብ ፈቃድ

ይህ ክቡር የአብ ፈቃድ በተወደደው ልጁ ሊፈጸም የተገባና ከአንድ ልጁ በቀር ማንም ሊፈጽመው የማይችል ነው። የኢየሱስ በምድር በስጋ መገለጥም የአባቱን ፍቃድ ሊፈጽም እንደሆነ ባለማቋረጥ በኢየሱስ አንደበት ላይ ነበር። በኢየሱስ ሊፈጸም የተገባ የአብ ፈቃድ ምንድነው?
ዮሐንስ 6
-----------

[3]□ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና።
[3]□ ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው።
[4]□ ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

ዕብራውያን 10
-----------

□ ቀጥሎ፦ እነሆ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል። ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል።
[1]□ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።
...
[14] አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል።

በሁለቱም የመጽሐፍ ክፍሎች አብ ለኢየሱስ እንዲፈጽም የሰጠው ፈቃድ ወደ ኢየሱስ የሚመጡትን ሰዎች ተቀብሎ ለእነርሱ መሞትና ለዘላለም እንዳይጠፉ መጠበቅን ነው። እንዴት አይነት ውድና የተባረከ አባት ነው። በልጁ በኩል የተገለጠው ፈቃዱ ሁሉ ወደ ኢየሱስ የሚመጡ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸውና ለዘላለምም እንዳይጠፋ ነው። ይህ የአብ ፈቃድ ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ልጁ ይህን ፈቃዱን በሚገባ ፈጽሞ በአባቱ ክብር ተቀምጦአል።

"እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤"
— ዮሐንስ 17፥4

2. የሰው ልጆች ይፈጽሙት ዘንድ የተሰጠ የአብ ፈቃድ

አብ የተወደደ ፈቃዱን በልጁ በኩል ለመፈጸም ተተኪ የሌለውን ልጁን እንደላከ እንዲሁ ደግሞ ሰዎች ይፈጽሙት ዘንድ ከአብ የተሰጠ ፈቃድ አለ። ይህ ፍቃድ ምን ይሆን? ከቃሉ እንስማ

ዮሐንስ 6
-----------

2□ እንግዲህ፦ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት።
2□ ኢየሱስ መልሶ፦ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።

የሰው ልጆች ይፈጽሙት ዘንድ ከአብ ዘንድ የወጣው ፍቃድ(ስራ) ከአብ ዘንድ ወጥቶ በመጣው በናዝሬቱ ኢየሱስ እንድናምን ነው። ምክንያቱም በእምነት በኩል ሰዎች ዳግም ልደትን በመቀበል አዲስ ማንነትን ይለብሳሉ አዲስ ፍጥረትም ይባላሉ(2 ቆሮ 5፥17)። እነዚህ ሰዎች በእውነት የአብን ፈቃድ የፈጸሙ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ስለሆነ "ጌታዬ ጌታዬ" ብለው ግን በጌታ ያልታወቁ አይደሉም።በኢየሱስ ስም ተአምራት አድርገው ፣ አጋንነትን አስወጥተው ፣ ትንቢት ተናግረው ግን ያልዳኑ አሉን? ብለን ስንጠይቅ አዎ ሰዎች ሳይድኑ ያንን እንደሚያደርጉ መጽሐፍ ይነግረናል (ሐዋ 19)።ከዚህም በኃላ በምናነሳቸው ጥቅሶች እነዚህን ሰዎች ስለምናነሳቸው ወደ ቀጣዩ ጥቅስ እንለፍ።

## 2. ማቴዎስ ወንጌል 24 እና 25

በማቴዎስ ወንጌል 24 እና 25 ላይ የተቀመጡት ታሪኮችን በትኩረት ጊዜ ሰተን ስናጠናቸው ለመረዳት ቀላል የሆነ ክፍል ነው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ያስተምረን ዘንድ ጊዜ ካልሰጠነው በራሳችን መንገድ ሄደን እንስታለን። በርግጥ በማቴዎስ 24 እና 25 መሰረት እውነተኛ አማኞች ድነታቸውን ሊያጡ ይችላሉን? እውን አስርቱ ቆነጃጂቶች የክርስቲያኖች ምሳሌ ናቸውን? ዘይቱስ በአማኞች ዘንድ የሚገኘው የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነውን? የዘይቱ ማለቅ የመንፈስ ቅዱስ ማለቅ ነውን?

እነዚህ ሁለት ምዕራፎችን ጌታ ኢየሱስ ያስተማረው ከደቀ መዛሙርቱ ለተነሳበት አንድ ጥያቄ እንደመልስ አድርጎ ነው።
“እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፦ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።”
— ማቴዎስ 24፥3
ኢየሱስ በሁለቱ ምዕራፎች ይህንን ጥያቄ እየመለሰ ነው። እንግዲህ በአጭሩ ሁለቱ ምህራፎች ስለኢየሱስ መምጣትና የዓለም መጨረሻ ምልክቶች እንዴት እንደሆኑ በማስተማር ላይ ነው።በአዲሳት መጽሐፍት ላይ መሰረት አድርገን እስቲ የክርስቶስን መምጣት እናጢን። ከኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኃላ ቅዱሳት መጽሐፍትን ስናጠና ከዚህ በኃላ ክርስቶስ ሁለት መገለጦች እንዳሉት

ያስተምረናል።ቅዱሳት መጽሐፍት ክርስቶስ እንደሌባ እንደሚመጣ(1 ተሰ 5 ማቴ 24) እና አለም ሁሉ እያየው እንደሚመጣ(ማቴ 24) ያስተምራል።የትኛው ይሁን ልክ? ሁለቱም ልክ ናቸው።ከዚህ ወዲያ ክርስቶስ ሁለት መምጣት እንዳለው ያውቃሉን?

# የክርስቶስ ለቅዱሳን መምጣት(እንደሌባ መምጣት)

1 ተሰ 5፥1፥6

ጌታችን ኢየሱስ ከትንሳኤው በኃላ ለአማኞች ቤት ያዘጋጅላቸው ዘንድ ወደ ሰማይ እንደሚሄድና ገዛ ተመልሶ እንደሚወስዳቸው ቃል ገብቶላቸዋል(ዮሐ 14)። በዚህ የተስፋ ቃል ውስጥ በርሱ የማያምኑቱ ተካፋይ አይሆኑም።ክርስቶስ ለሚያምኑቱ እንዴት እንደሚገለጥ ቅዱሳት መጽሐፍት እንዲህ ያስተምራሉ

1ኛ ተሰሎንቄ 4

-----------

[1] ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤

[1] ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።

በዚህ ክፍል መሰረት ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ሲመጣ ምድር ድረስ እንደማይመጣና እስከአየር ድረስ እንደሚወርድና እኛም እርሱን በአየር ለመቀበል በደመና እንነጠቃለን እንጂ በፍጹም ምድር ደርሶ ከዚህ ይዞን እንደሚወጣ አይነግረንም።ይህ ታላቅ ክስተት የቅዱሳን ንጥቀት ይባላል።የእውነተኛ አማኞች የምድር ቆይታ በንጥቀት እንደሚጠቃለል ሐዋሪያው ጳውሎስ ያስተምረናል።ይህየመሲሁ መምጣት እንደሌባ ይመጣል ተብሎ የተነገረ ነው ምክንያቱም መሲሁ በዚህ ጊዜ ሲመጣ ቅዱሳንን ከምድር በንጥቀት ሊሰርቅና ይህም የሚሆንበት ጊዜ ስስማይታወቅ ነው። ስለዚህም ነው ሐዋሪያው ክርስቶስ በአማኞች ላይ እንደሌባ እንደማይመጣ የሚናገረው(1 ተሰ 5)።

#የክርስቶስ ለአለም ሁሉ መገለጥ

ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በንጥቀት ወደ ራሱ ከወሰዳት በኃላ በኢየሱስ የማያምነው በምድር የቀረው ሕዝብ ለ 7 አመት ያህል በእግዚአብሔር ፍርድ ይጠበሳል። ይህም ታላቁ የያዕቆብ መከራ በመባል የሚታወቀው ነው። በዚህ መከራ ውስጥ ክርስቶስ ቤተ ስርስቲያንን በምድር እንደማያሳልፋት መጽሐፍት ያስተምሩናል(ራዕ 3፥10, 2 ተሰ 2)። ያህ ታላቁ መካራ ከዛሬ 2000 አመት በፊት አይሁድን ክርስቶስ ለመቤዠት በመጣ ጊዜ አንፈልግህም ብለው ለአህዛብ አሳልፈው እንደሰጡትና እንደሰቀሉት በዚያ የሰባት አመት መከራ በሀይለኛው ሲገረፉ አይኖቻቸውን ወደ ወጉት ወደ እርሱ በማዞር እንደገና ሆሳህና(አሁን አድን) ይሉታል (ሉቃ 23)

“በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የሞገስንና የልመናን

መንፈስ አፈስሳለሁ፤ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፤ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።”
— ዘካርያስ 12፥10

በዚህ ጊዜ አይሁድን ከጠላቶቻቸው ሊያድን አለም ሁሉ እያየው በደብረ በይት ተራራ ላይ በክብር ይገለጣል(ዘካ 14፥1-10)።ይህ ነው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚባለው።በአማኞች ወደ ክርስቶስ መነጠቅና በክርስቶስ ዳግም ምጽአት መካከል የሰባት አመት ልኑነት አለ(ራዕ 14)።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24ና 25 እየተናገረ ያለው ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ከተነጠቀች በኃላ በምድር ላይ ስለሚከሰቱት ክስተቶችና ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው። ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ወቅት ከክርስቲያኖች ጋር አብሮ እንደሚመጣ መጽሐፍ ያስተምረናል(ራዕ 19)። በማቴዎስ 24ና 25 የተነገሩ ትምህርቶች ሁሉ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አብረው የማይሄዱና ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኃላ በ 7 አመቱ የፍርድ ጊዜአት የሚፈጸሙ ና በክርስቶስ ዳግሞ ምጽአት የሚጠቃለሉ ናቸው። ማቴዎስ 24ና 25 ከቤተ ክርስቲያን ጋር የማይገናኝባቸው ምክንያቶች

“ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤”
— ማቴዎስ 24፥20
ይህ ቁጥር መከራ በመጣባቹ ጊዜ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ ይላቸዋል። ይህ ማለት ክረምት የተባለበት ምክንያት እስራኤል በተለያዩ ወንዞች የተከበበች ስለሆነ በክረምት ስደት ቢነሳባቸው ወንዞቻቸው ስለሚሞሉ ማምለጥ ስለማይችሉ ነው። ይህ ለክርስቲያኖች ቢሆን ኖሮ ወንዝ የሌለባቸው አገሮችና በበረሀ የሚኖሩት ደግሞ የጸሐዩ ንዳዳ እንዳያደክማቸው በክረምት ይሻላቸዋል እና ይቃ ጥቅስ የሆነ የተወሰነ ስፍራን ብቻ ያማከለ ነው(የእስራኤልን ምድር)። እንዲሁም በሰንበት ይላቸዋል። እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያን የቀን ሰንበት የላትም ሰንበቷ ክርስቶስ ነውና(ቆላ 2፥16-17)።ምድራዊቷ እስራኤል ግን እሰከዛሬ ድረስ የቀን ሰንበት አክባሪ ነች።ቤተ ክርስቲያን ደሞ የትኛውንም ቀን ከየትኛውም ቀን እየለየች እንዳታከብር በሐዋሪያት ታዛለች(ገላ 4,ቆላ 2)።የእስራኤል ሕዝብ በሰንበት ቀን ረጅም መንገድ መጓዝና ስራ መስራት ስለማይፈቀድለት በዛች ቀን ስደቱ ከተነሳ የሙሴንን ሕግ ስለሚተላለፉ ነው።ቤተ ክርስቲያን ግን ሰንበቷ ክርስቶስ ነውን በየትኛውም ቀን ስራ የመስራትና የመንቀሳቀስ መብቱ አላት።

እያንዳንዱን ቁጥር እያነሳን ብዙ ማለት ብንችልም ግን ከጊዜ አንጻር በምዕራፍ 24 ላይ የተተረኩት ትምዕርቶች ሁሉ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ኪዳን ጋር አብረው የማይሄዱና ቤተ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ከተነጠቀች በኃላ በምድር ላይ በሚቀሩ ሰዎች የሚፈጸም ነው።ከዚህም በመነሳት

“እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።”
— ማቴዎስ 24፥13
ይሄ ጥቅስ በመከራው ዘመን በምድር ላይ ለሚቀሩ ሰዎች እስከመከራው

ፍጻሜ ካልጸኑና በጊዜው ለሚነሳው ሐሰተኛ መሲህ ከተወሰዱ እንደማይድኑ የሚናገር እንጂ ለቤተ ክርስቲያን የተጻፈ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሰዎች ድነትን የሚቀበሉት እስከመጨረሻው በመጽናት ሳይሆን በጸጋ ነው(ኤፌ 2,ቲቶ 2) ደግሞም ድነታቸውን የሚቀበሉትም አሁን ነው (1 ዮሐ 5፥12, 2 ቆሮ 6፥1-2)።

በማቴዎስ 24 ላይ የተፃፈው የሰባት አመቱ(የ 1360 ቀንና የ 42 ወራት) መከራ በተፈጸመ ጊዜ ክርስቶስ የጌቶች ጌታና የነገስታት ንጉስ ሆኖ ከቅዳሳን(ከቤተ ክርስቲያን) ጋ በክብር ይመጣል። ይህ ታሪክ በማቴዎስ 25 ላይ የተጠቀሰው ታሪክ ነው። ክርስቶስ ከሰማይ ሁለተኛ መምጣቱ ወደ አስሩ ቆነጃጅት ነው ማለትም 10 ቁጥር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሕግ(የትእዛዝ) ምሳሌ ነው። 10ቱ ትእዛዛት ደሞ ለእስራኤል እንጂ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ አይደለም። ሕግ ለእስራኤል ተሰጠ ጸጋና እውነት ለቤተክርስቲያን (ዮሐ 1፥17)።በዚህም ምክንያት አስርቱ ቆነጃጅት የቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ሳይሆኑ ቤተ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ከተነጠቀች በኃላ በምድር የሚቀሩ አይሁዶች በኢየሱስ ምክንያት በሁለት ይከፈላሉ።ግማሹ ከሚፈሰው መንፈስ በመቀበል ኢየሱስን ሲያምን ሌሎቹ ግን በመከራው ብዛት ከሰማይ የፈሰሰውን ዘይት ትተው የምድሩን(ሐሰተኛውን መሲህ) ፍለጋ ይሯሯጣሉ።

ሲቀጥል ክርስቶስ ለክርስቲያኖች ሲመጣ እስከአየር እንጂ እስካሉበት አይመጣም በዚህ ምህራፍ ግን ክርስቶስ እስካሉበት መቶአል ይህ ማለት ደሞ ቆነጃጂቶቹ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አይደሉም ማለት ነው።

በምዕራፍ 25 ፍጻሜ የመገኘውም የበጎችን ከፍየሎች የመለየት ታሪክ ፈጽሞ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የማይሄድ ነው ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ምትሄደው በን ጥቀት እንጂ ክርስቶስ ምድር መቶ በጎችን ሰፍየሎች በመለየት አይደለም የሚወስዳት። በአጭሩ በማቴዎስ ወንጌል 24ና 25 የተጻፉ ምሳሌያዊ ትምህርቶች ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ኪዳን ጋር አብረው የማይሄዱ ናቸውን አንባቢው በጸሎትና በሌሎች አጋዥ መጽሐፎች ተንተርሰው ያጥኑ።

## *3. ፍሬ የማያፈራ ሁሉ ይቆረጣል(ዮሐ 15 እና ማቴ 13)

በዮሐንስ ወንጌል 15 መሰረት ፍሬ የማያፈራ(በመልካም ሕይወት የማይመላለስ) ክርስቲያን ይቆረጣልን? ከዚህ ክፍል ተነስተው ብዙ ሰዎች እውነተኛ አማኞች ድነታቸውን በፍሬ ምክንያት ሊያጡ ይችላሉ ሲባል ይሰማል። ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? በመጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ትምህርት ሲያስተምር ማንን ማህከል አድርጎ ነው? በዚህ ጊዜ አይሁዶች ኢየሱስን "አንተ ክርስቶስ የዳዊት ልጅ የእስራኤል ተስፋ አይደለህም!" በሚሉት ጊዜ ነው ይህንን ታላቅ ትምህርት ያስተማረው። ከቅዱሳት መጽሐፍ ተነስተን ወይን የምን ምሳሌ ነው? ብለን እንጠይቅ እስቲ
“የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ወይን ቦታ እርሱ የእስራኤል ቤት ነው፥ የደስታውም አትክልት የይሁዳ ሰዎች ናቸው፤ ፍርድን ተስፋ ያደርግ ነበር፥ እነሆም ደም ማፍሰስ ሆነ፤ ጽድቅንም ይተማመን ነበር፥ እነሆም፥ ጩኸት ሆነ።”
— ኢሳይያስ 5፥7

በቅዱሳት መጽሐፍት ዘገባ መሰረት ወይን እስራኤል እንደሆነች ግልጽ ነው።እስራኤል ወይኗ ስትሆን በአባቶቻቸው ይመጣል ተብሎ የተነገራቸው ተስፋ አለ እርሱም የዳዊት ልጅና
የሚመሰርተው ዘላለማዊ መንግስቱ ነው።ኢየሱስም የዳዊት ልጅ ሆኖ ለእስራኤል መንግስትን ሊመሰርት መጣ እነርሱ ግን አንተ የምንጠብቀው መሲህ አይደለህም አሉት። ከዮሐንስ ወንጌል 5 ጀምሮ ከአይሁዶች ጋር የተደረገ ምልልስ ነው። ያህ ምልልስ ገፍቶ ምዕራፍ 15 የደረሰው። እስራኤል የእግዚአብሔር ወይን በነበረችበት ጊዜ አህዛብ የሆንን እኛ ምን ነበርን ስንል
ኤፌሶን 2

-----------

[11] ስለዚህ እናንተ አስቀድሞ በሥጋ አሕዛብ የነበራችሁ፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤
[12] በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ።

ከዚህ ክፍል በመነሳት ኢየሱስ ዮሐንስ 15 ን በሚያስተምርበት ወቅት እኛ በስጋ እስራኤል ያልነበረን ሰዎች የነበርንበትን ስፍር ሐዋሪያው ጳውሎስ በግልጽ ይነግረናል። እኛ አህዛቦች ቀድሞም በወይኗ ግንድ ላይ አልነበርንም ማለትም ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ ተብሎ እንደተጻፈ።አይሁዳውያን ግን ክርስቶስ የሚባል ተስፋ በነቢያት በኩል ተሰቶአቸዋልና እነርሱ በዛ ግንድ(ተስፋ) ላይ ነበሩ። እውነተኛው ተስፋቸው በመጣ ጊዜ ግን አንተ ክርስቶስ አይደለህም ብለው ሲገፉት ይህን ትምህርት ያስተምራል።የክፍሉ ዋና አላማ ፍሬ ማፍራት ሳይሆን በክርስቶስ መሆን ነው። ሰዎች ክርስቶስ በሆነው በኢየሱስ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ፍሬ ማፍራትን ፈለጉ።እርሱ ግን እንዲህ አላቸው
“እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።”
— ዮሐንስ 15፥5

መሲሁ አይሁድን ፍሬ ያላፈራ ይቆረጣል ሳይሆን የሚላቸው በእኔ ካልሆናችሁ ፍሬን ልታፈሩ አትችሉም ይላቸዋል። በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመነ ደሞ መጨረሻው ግልጽ ነው። ይህ በክርስቶስ የተነገረው ለእስራኤል ልጆች እንጂ ለቤተ ክርስቲያን አይደለም። ኢየሱስ በዚህ ክፍል ላይ የተናገረውን አልሰማም ብለው ስላላመኑበት እንደተቆረጡ ደግሞ ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ያስተምረናል።

ሮሜ 11

-----------

[1□] ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ፥ በቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤
[1□] ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከምሃል እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም።

[1]□ እንግዲህ፦ እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል።
[2]□ መልካም፤ እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ።
[21] እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና።

በኢየሱስ በኩል በዮሐንስ 15 ላይ የተነገረው ቃል እንደተፈጸመና አንዳንድ ቅርንጫፎች እንደተሰበሩ ጳውሎስ ይነግረናል።የተሰበሩትም ፍሬን ስላላፈሩ ሳይሆን ባለማመናቸው እንደሆነ ያረጋግጥልናል።እኛም አህዛብ የሆንን በእምነት በኩል ከክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ በኩል ወደ ወይኗ ተክል ተጨምረን ቅርንጫፍ ሆነናል።ከእንግዲህ እኛ በእውነተኛው ግንድ ላይ አለንና በእውነትም እናፈራለን። ምክንያቱም በእኔ የሚያምን ብዙ ፍሬ ያፈራል ተብሎ ተጽፎአልና(ዮሐ 15፥5)። ፍሬዎቹ በክርስቶስ ለመሆናችን ማረጋገጫ እንጂ ፈጽሞ የመዳን ምክንያትና ዋስትና አይደሉም። እኛም በግንዱ የተለጠፍነው በእምነታችን በኩል ነው። ይህን እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ። ኢየሱስ በሌላ ክፍል ስለ ፍሬ ሲያስተምር እውነተኛ አማኞች ሁሉ ፍሬን እንደሚያፈሩ በግልጽ ተናግሮአል መጠኑ ይለያያል እንጂ

“በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል።”
— ማቴዎስ 13፥23

በማቴዎስ 13 ላይ የሚገኘውን የዘሪውን ምሳሌ ወስደው ለክርስቲያኖች እንደሚሆን አድርገው የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ ግን የእውነተኛ የክርስቲያኖች ምሳሌ በመልካም መሬት ላይ የወደቀው ብቻ ነው ምክንያቱም እውነተኛ ክርስቲያኖች የተሰበከላቸውን የእውነት ቃል በመቀበላቸው ዳግም ተወልደዋልና ሌሎች ዘር የወደቀባቸው መሬቶች ሁሉ ዳግም ያልተወለዱ ናቸው። በዚህ ምክንያት እውነተኛ አማኞች በርግጥም ያፈራሉ።ቢደክሙ እንኳን ሰላሳን ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው በክርስቶስ ናቸውና።

## 5. የእግዚአብሔርን መንግስት እንደማይወርሱ አታውቁምን?

## ገላ 5፥19-24, ኤፌ 5 , 1 ቆሮ 6፥9-11

ሐዋሪያው ጳውሎስ በሦስቱ መልእክቶች ውስጥ ተመሳሳይ አይነት ሀሳብ በማስቀመጥ የተለያዩ የኃጢያት አይነቶችን በመዘርዘር ይህን የሚያደርጉ በእግዚአብሔርና በክርስቶስ መንግስት ውስጥ ስፍራ እንደሌላቸው ይናገራል።እነዚህን ጥቅሶች ይዘን እውነተኛ አማኞች በሚያደርጉት ኃጢያት ምክንያት ድነታቸውን ሊያጡ ይችላሉ ማለት እንችላለንን? ሐዋሪያውስ ክርስቲያኖችን እንደዛ ብሎአልን? ሐዋሪያው ጳውሎስ በየትኛውም መልእክቱ እውነተኛ አማኞች በእምነት የተቀበሉትን ድነት በኃጢያት ምክንያት እንደሚያጡት አይናገርም።ምክንያቱም ክርስቶስ ኢየሱስ የዕድሜ ዘመን ኃጢያታችንን በመስቀል ላይ ሞቶ አስወግዶልናልና(ሮሜ ሃ፥ሃ-5)።ክፍሎችን በቅደም ተክተል እንመልከታቸው

## ፩ኛ ቆሮንቶስ 6

----------

[9] ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ
[10] ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
[11] ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።

ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈበት ምክንያት በአማኞች መካከል ለተነሳው መከፋፈል፣ የተለያዩ ኃጢያቶች፣ የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀም ችግርና የሙታን ትንሳኤ የለም ለሚሉ ሁሉ መልስ የያዘ ደብዳቤ ነው።ሐዋሪያው በዚህ ደብዳቤ የቆሮንጦስ ክርስቲያኖችን ስጋውያን ናችሁን ይላቸዋል እንጂ ፍጥረታውያን ናችሁ አይላቸውም።ፍጥረታዊ ማለት ዳግም ያልተወለደ(ያልዳነ) ሰው ማለት ነው(1 ቆሮ 15)። ስጋዊ ማለት የዳነ ሰው ሆኖ ግን በዳነበት የሕይወት ከፍታ የማይመላለስና እንደዚህ አለም ሰው የሚኖር ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በሐዋሪያው ጳውሎስ ስጋውያን ተብለዋል።
ሐዋሪያው በዚህ ክፍል የሚያስተምረው ስጋውያን የሆናችሁ እናንተ ክርስቲያኖች ለምን እንደዚህ አለም ሰዎች ትኖራላችሁ? የዚህ አለም ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግስት እንደማይወርሱ አታውቁምን? ይላቸዋል።የቆሮንጦስ ሰዎች ከዚህ አለም ሰዎች ጋር አብረው ሲኖሩ አንድ አይነት የሆኑ መሰላቸው ይህንን ነው ጳውሎስ "እናንተ እንደነርሱ አይደላችሁም" ይላቸዋል። ሁሌም ቢሆን በቅዱሳት መጽሐፍት መሰረት "እነርሱ" እና "እኛ" የሚሉ ቃሎች ጥንቃቄ ይፈልጋሉ። ሐዋሪያው "እነርሱ" ሲል በአጭር ቋንቋ ኢ አማናውያንን እንደሆነ ግልጽ ነው። "አትወርሱም ሳይሆን አይወርሱም ነው ያላቸው። ይቀጥልና "እናንተ ግን በኢየሱስ ስምና በቅዱሱ መንፈስ በኩል ጸድቃችኃል ተቀድሳችኃል ታጥባችኃል። ክርስቲያኖቹ በስህተት ተቀላቅለው ነበርና መጨረሻቹ አንድ ስላይደሐ ከማይወርሱት ጋር አትተባበሩ ነው እንጂ የሚለው አትወርሱም አላላቸውም።

## ገላትያ 5

----------

[19] የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥
[20] ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥
[21] ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
...
[24] የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

ይሄም ክፍል በተመሳሳይ ቁ 21 ላይ አቁመን ወደ ራሳችን ፍቺ ከገባን እንስታለን። ሐዋሪያው የተለያዩ ኃጢያቶችን ከዘረዘረ በኃላ እነዚህን የሚፈጽሙ ድነት የሌላቸውና ወራሽ ያልሆኑ ሰዎች እንደሆኑ ተናግሮ በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑ(የዳኑቱ) ግን ፈጽሞ በዚህ ባህሪ እንደማይኖሩ ያረጋግጥላቸዋል።ጥያቄው አሁን ኃጢያት ሰርተህል ወይስ አልሰራህም አይደለም!!! በክርስቶስ ኢየሱስ ነህ ወይስ አይደለህም? እንጂ። በዚህ ክፍል መሰረት ሁለት
አይነት ሰዎች አሉ የሥጋ የሆኑ(ኢ አማናውያን) ቁ19 እና የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑ(አማኞች)። ጥያቄው የማን ነህ? ነው እንጂ ምን እየሰራህ ነው አይደለም። እውነተኛ አማኞች እንደዚህ አለም ሰዎች በኃጢያት ጸንተው መኖር አይችሉም(1 ዮሐ 4)።

ኤፌሶን 5
-----------

□ ይህን እወቁ፤ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኵስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።
□ ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ።
□ እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ፤

በዚህም ክፍል በተመሳሳይ "እነርሱ" ከተባሉት ጋር እንዳንተባበር ያዘናል። "እነርሱ" የሚባሉት ሰዎች ዳግም ያልተወለዱና ያልዳኑ ሲሆኑ ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥም የክርስቶስ አካል ሳይሆኑ የማህበሩ አባል ሆነው ሊኖሩ ይችላሉ። እያወራን ያለነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላላ ሰው ሳይሆን ስለእውነተኛ አማኝ ነው። እውነተኛ አማኝ በእግዚአብሔር እጅ ተይዟልና ለዘላለም አይጠፋም።

## 6. አገልግዬ ተጥዬ እንዳልቀር 1 ቆሮ 9፥24-27

ሐዋሪያው ጳውሎስ በመጀመሪያቱ የቆሮንቶስ መልእክት በዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ የጻፈው አንድ ጥሩ መልእክትን ወስደው ሰዎች የክርስቶስን ስራ ለማሳነስና በመስቀል ላይ የተከፈለውን ክቡር ደም ዋጋ ለማሳነስ ይሞክራሉ።ሐዋሪያው ግን የጻፈው ጽሑፍ በሌሎች መልእክቱ ከአስተማረው ከጤናማው ቃል ጋር አብሮ የሚሄድ እንጂ የሚጋጭ አልነበረም።እስኪ ክፍሉን እንመልከት

1ኛ ቆሮንቶስ 9
-----------

24 በእሽቅድምድም ስፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ።
2□ የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን።
2□ ስለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጎስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤

[2]□ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።

የሚገረው ነገር በዚህ ክፍል ላይ መዳን ጽድቅ የዘላለም ሕይወት የሚባሉት ነገሮች ሳይጠቀሱ ለምን ሰዎች ከነዚያ ነገሮች ጋር ለማገናኘት እንደሚሮጡ ነው? ከላይ የዘረዘርኳቸው በረከቶች ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ስራ እንዲሁ በምህረቱ የምንቀበላቸው እንጂ በሩጫ ሜዳ በእሽቅድድም የሚገኙ ነገሮች አይደሉም

“እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።”

— ሮሜ 9፥16

በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ሐዋሪያው እያወራ ያለው በእምነት የምንቀበለውን መዳን ሳይሆን በሥራ የምናገኘውን አክሊል ነው። አክሊል ማለት ሽልማት ወይም ደሞዝ ማለት ነው። ሰዎች ሩጫ ከሮጡ በኃላ ሲሲያሸንፉ በራሳቸው ላይ የሚጫንላቸው ዘውድ ነው በዛሬ ጊዜ በአንገታቸው ላይ የሚጠልቅላቸው ሜዳልያ ሲሆን በላባቸው ያመጡት ነውና ደሞዝ ወይም ሽልማት እንጂ በፍፁም ስጦታ አይደለም። ወደ ድነት ስንመጣ ግን ደሞዝ ሳይሆን ስጦታ ነው

ሮሜ 4

----------

[4] ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤

□ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።

ጽድቅ የዘላለም ሕይወት መዳን ዳግም ውልደት ሁሉ ስጦታ እንጂ የሥራችን ውጤት አይደሉም።(ኤፌ 2፥8-9,ሮሜ 6፥23, 2 ጢሞ 1፥7-9, ቲቶ 3)።ክርስቲያኖች እንዲሁ በጸጋ ከዳኑ በኃላ እግዚአብሔር ቤቱን ያገለግሉ ዘንድ ለእያንዳንዱ አማኝ በመንፈስቅዱስ በኩል የጸጋን ስጦታ ችሮናል። ይህን የሰጠን ቅዱሳንን እንድናገለግልበትና ለአለም ሁሉ ወንጌልን እንድናደርስበት ነው። ይህንን ስናደረግ ግን ለተሰጠን ዘላለማዊ ሕይወት የፍቅር ምላሽ ብቻ ሳይሆን በውጤቱም ለሽልማታችንና ከእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋናን የሚያስገኝልን እንዲሆን አድርጓል። እግዚአብሔር አባታችን ምን አይነት ድንቅ አምላክ ነህ ፤ ብቸኛ ልጅ የሆነክ አንተ ክርስቶስ ኢየሱስ ምን አይነት ድንቅ ጌታ ነህ ፤ ከአብ ጸርጸ በወልድ የተላክ አንተ መንፈስ ቅዱስ ምን አይነት ድንቅ የሀይል ምንጭ ነህ!!!!!!

ክርስቲያኖች በሥራቸው ምክንያት የሚቀበሉት እስከ አምስት የሚደርሱ ሽልማቶች(አክሊሎች) እንዳሉ ቅዱሳት መጽሐፍት ያስተምራሉ።

1.የጽድቅ አክሊል

አንድ እውነተኛ አማኝ ሰዳነ በኃላ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውን የእምነት ሩጫ ሁሉ ሲጨርስና ሀይማኖቱን ሲፈጽም ከክርስቶስ እጅ የሚቀበለው ነው።ለምሳሌ ሐዋሪያው ጳውሎስ

2ኛ ጢሞቴዎስ 4

----------

 መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤
 ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።

2.የሕይወት አክሊል
አንድ እውነተኛ አማኝ ስለክርስቶስ እና ስለወንጌል እስከሞት ድረስ የታመነ ሲሆን ከክርስቶስ እጅ የሚቀበለው ሽልማት ነው።ለምሳሌ እስጢፋኖስ ሐዋ 7

“ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።”
— ራእይ 2፥10
3.የክብር አክሊል
አንድ እውነተኛ አማኝ በክርስቶስ ክቡር ደም የተዋጀችውን ክብርት ቤተ ክርስቲያንን በእረኝነት ሲያገለግል ከክርስቶስ የሚቀበለው ሽልማት ነው።

1ኛ ጴጥሮስ 5
----------

3 ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤
4 የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።

4.የድል አስሊል
ይህ የአክሊል አይነት ደግሞ አንድ መጋቢና የወንጌል ሰባኪ የተሰጣቸውን የወንጌል አደራ በታማኝነት ሲፈጽሙ ከክርስቶስ እጅ የሚቀበሉ ነው።
“ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል፥ የድሉን አክሊል አያገኝም።”
— 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5
5. የማይጠፋ አክሊል
በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያየ የጸጋ ስጦታዎች አገልግለው የሚጨርሱ ሰዎች ከክርስቶስ እጅ የሚቀበሉት የአክሊል አይነት ነው።

“የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን።”
— 1ኛ ቆሮንቶስ 9፥25
6.የተስፋ ወይም የደስታ ወይም የትምክህት አክሊል
ይህ አክሊል ደሞ ኢየሱስን በማመን ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡትን ሰዎች በተለያዩ አገልግሎት አገልግሎ በቤቱ ለሚያጸኑ ሰዎች ከክርስቶስ እጅ የሚቀበሉት ነው።
1ኛ ተሰሎንቄ 2
----------

[1□] ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን?
[2□] እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና።

ሁላችንም ማወቅ ያለብን ነገር ሰዎች እንደሚያዩና እንደሚፈርዱ ጌታ እንዳዛ ስላልሆነ የትኛዋንም አገልግሎት ስናገለግል በሙሉ መሰት እንዲሆን መጽሐፍ ያዝናል።ሁሌም ቢሆን ክርስቶስ በማህበሩ መካከል አለና።
“እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።”
— ዕብራውያን 6፥10

በክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑ እውነተኛ አማኞች ስራቸውና አገልግሎታቸው እንደ እግዚአብሔር ቃል ባይሆንና ለታይታ እንኳን ቢሆን በመጨረሻ ሽልማታቸውን እንጂ ድነታቸውን ሊያሳጣቸው አይችልም።ምክንያቱም ድነት በስራ ሳይሆን በጸጋ ነውና።

1ኛ ቆሮንቶስ 3
----------

[11] ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
[12] ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤
[13] በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል።
[14] ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤
[1□] የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።

## 7. ከዕብራውያን መልእክት የሚነሱ ጥቅሶች

የዕብራውያን መልእክት ከሐዋሪያው ጳውሎስ መልእክታት መካከል አንዱ ነው።በዚህ መልእክቱ ተደረሲያኑን ለገቡበት የትምህርት ውድቀት ከአምስት ማስጠንቀቂያዎች ጋር ወደ ቀደመው የሐዋሪያት ትምህርት እንዲመለሱ ያስተምራቸዋል። እነዚህ ሰዎች በስጋ የዕብራዊው የአብርሃም ልጆች ሲሆኑ የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ ቃላትና በረከቶቹ ሁሉ ለእነርሱ የሆነላቸው ሕዝቦች ናቸው(ሮሜ 3፥1,9፥4-5)። ይህ ታላቅ ሕዝብ ክርስቶስ የሚባል ተስፋ የነበረው ሕዝብ ነው። የናዝሬቱ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ተብሎ ሲሰበክላቸው በእምነት ተቀብለው ወደ ቤተ ክርስቲያን የተቀላቀሉ ክርስቲያኖች ሆነዋል።እነዚህ ክርስቲያኖች ግን በውስጣቸው እውነተኛ አማኞች ያልሆኑ እንዳሉ መጽሐፉ ይነግረናል።

እነዚህ አማኞች ከበፊት ሀይማኖታቸው ከአይሁዶች ዘንድ እጅግ አስቸጋሪ

መከራ ስለደረሰባቸው ክርስትናቸውን ትተው ወደ ይሁዲነት ለመግባት ሲያፈገፍጉ ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን ይጽፍላቸዋል።የመልእክቱ ዋና ሀሳብ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ከብሉይ ኪዳናት ቃላት ሁሉ ይበልጣል የሚል ነው።የተቀበላችሁትን የአብ ሀይማኖት አጥብቃችሁ ጠብቁ የሚል ማስጠንቀቂያማ አለበት።

ይህ መልእክት የተጻፈው እያፈገፈጉ ያሉ ክርስቲያኖች በተቀበሉት እምነታቸው ጸንተው እንዲኖሩ እየመከራቸው እንጂ በሀጢያት ውስጥ የገቡትን ክርስቲያኖች ድነታቸውን እንደሚያጡ እየተናገረ አይደለም። እንባብያን ሁሉ ሊያስተውሉ የሚገባው እውነተኛ አማኞች የማይጠፉ በድካማቸውንና በሀጢያታቸው እንጂ እምነታቸውን ወደ መጣልና የክርስቶስን አዳኝነትና ጌትነት ወደ መካድ ከመጡ እነዚህ ሰዎች ቀድሞም አላመኑም ማለት ነው። እናምናለን ብለው የተቀላቀሉ ግን ቀድሞም ያልዳኑ ናቸው(1 ዮሐ 2)። ይህንን ትምህርት ከዚህ መልእክት እንመልክተ እስኪ

ዕብራውያን 6
-----------

1-2 ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት፥ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት፥ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።
3 እግዚአብሔርም ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን።
4 አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን
 መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን
 በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና።
 ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፥ ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል፥ ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና፤
 እሾህና ኵርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።
 ስለ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር፥ አብልጦ የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆንላችሁ ተረድተናል።

በዚህ ክፍል ላይ አንድ እውነት እናስተውል ከቁ 1-3 ድረስ "እኛ" ይላል ጸሀፊው ራሱን አስገብቶ ከቁ 3-8 ድረስ "እነርሱ" እያለ ይናገራል ቁ 9 ጋ ደሞ "እናንተ" የሚልን ነገር ያነሳል። በዚህ ክፍል ላይ እውነተኛ አማኞች "እኛ" ና "እናንተ" የተባሉት እንደሆኑ ግልጽ ነው። እነርሱ የተባሉት ሰዎች በአማኞች መካከል የሚኖሩ እውነተኛውን ብራሀን ኢየሱስን የሚያውቁ እንጂ በእውነት ያላመኑ ፤ በክርስቲያኖች ዘንድ የሚደረጉትን መንፈሳዊ ስጦታዎች የቀመሱ(የጌታ እራት ጥምቀት ምናምን ሊሆን ይችላል) ፤ ከአማኞች ጋር

የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣና እንደሚነግስ የሚያውቁ ግን በእውነት ያላመኑ ሲሆኑ በመጨረሻ ባለማመን ራሳቸውን የሚገልጡ አፋዊ አማኞች ናቸው።በመጨረሻ እውነተኛ አማኞች ግን ለመዳን የሚሆናቸው እምነት እነርሱ ጋር እንዳለ ጸሀፊው ያረጋግጥላቸዋል።

በጣም ብዙ ጊዜ የሚነሳው ሌላ ሀሳብ ደሞ በዕብራውያን 10 ላይ ያለው የመጽሐፍ ክፍል ነው።ይህን ክፍል በትህግስት አንብቦ መጨረስ ለብዙ ሰው ፈተና ሆኖበት ከመሀል ፈልቅቆ ያወጣና የተጣመመ መረዳት ላይ ይቆማል።እስኪ ክፍሉን እንመልከት

ዕብራውያን 10
-----------

2□ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥
2□ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።
2□ የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤
2□ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኵስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?
3□ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና፤ ደግሞም፦ ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል።
31 በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያስፈራ ነው።

ይህን የመጽሐፍ ክፍል ይዘው በድካማቸው ሀጢያት የሚሰሩ ክርስቲያኖች ሊጠፉ ይችላሉ የሚሉ ሰዎች ይበዛሉ።ግን ሐዋሪያው በርግጥ እንደዛ አለን? በአጭሩ ለእሳት ባህር የሚያደረስው ኃጢያት ነው በዚህ ክፍል የተጠቀሰው እሱም የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ማለትም ክርስቶስን ትቶ ወደ ብሉያት ነቢያት የመመለስ ፣ የኪዳኑን ደም ያክፋፋ ማለትም የክርስቶስን ደም ትቶ ወደ ብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች የሚመለስ ፤ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ የሚያስተምረውን መንፈስ ቅዱስን ገፍቶ መዳን በሕግ ስራ ነው የሚል መጨረሻውን እየተናገረ ነው። እንጂ ኃጢያት ሲል በክርስቶስ ኢየሱስ የመስቀል ስራ ሙሉ በሙሉ ያመኑ ክርስቲያኖች በድካም ምክንያት ስለሚሰሩት ኃጢያት አይደለም።በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የተቀመጡ ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ ስለማያምን ልብ የተሰጡ ናቸው። በእምነት ጉዳይ ቅዱሳት መጽሐፍ እምነታችንን አጥብቀን እንድንይዝ ይጠይቀናል።

## 8. በኤፌሶን እና በሎዶቂያ ቤተ ክርስቲያን(ራዕ 2-3)

ክርስቶስ በራዕይ መጽሐፍ ላይ ለሰባቱ ኤሲያ አብያተ ክርስቲያናት ወደ ፊት የሚመጡ የቤተ ክርስቲያንን መልክ በምሳሌነት ይገልጣል። ለአብያተ ክርስቲያናቱ መላእክት(pastors or leaders) ጌታ በተለያየ መልክ ራሱን

ገልጦላቸው በዮሐንስ በኩል መልእክትን አስተላልፎላቸዋል።ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ባስተላለፋቸው መልእክቶቹ ውስጥ አማኞች ድነታቸው ሊያጡ እንደሚችሉ የሚመስል ጥቅስ እንዳ አድርገው የሚናገሩ ሰዎች እንዳሉ ይሰማል።ነገር ግን ከቅዱሳት መጽሐፍት ዘገባ አንጻር መልእክቶቹን እንመልከታቸው እስቲ
ለሰባቱም ቤተ ክርስቲያናት "ድል ለነሳው እንዲህ ይደረጋለታል" የሚል ቃል አለ።እነዚህን ቃሎች ወስደው በመልካም ስራ የሚፈጸም ድነት አለ ይባላል። ነገር ግን ድል መንሳትን ወይም ማሸነፍን መልካም ስራ ነው ብሎ የሚተረጉም በቅዱሳት መጽሐፍ መሰረት ጥቅስ አናገኝም። በዚህም መሰረት ድል መንሳት ወይም ማሸነፍ እንዴት ይገኛል ሲባል

“ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።”
— 1ኛ ዮሐንስ 5፥4
የራዕይም መጽሐፍ ከክርስቶስ የተቀበለው ራሱ ሐዋሪያው ዮሐንስ ድን መንሳትን ወይም ማሸነፍን ሲፈታው በእምነት እንጂ በስራ ብሎ አይተረጉመውም። ማለትም ድል ለሚነሳ ማለት ከእግዚአብሔር የተወለደና በልጁ የሚያምን ማለት ነው።

“እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ።”
— ራእይ 2፥5
ይህንን ጥቅስ ይዘው የዘላለም ሕይወት ይወሰዳል ሲሉ በጣም ይገርመኛል።መቅረዝ የዘላለም ሕይወት ነው ብሎ የተረጎመ አንድ የቅዱሳት መጽሐፍት ጥቅስ እንኳን ማግኘት አንችልም።መቅረዝ ማለት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች መብራት ወይም ብርሃን የሚይዙበት እቃ ነው።ጌታ ያንን መቅረዝ እወስድብሻለው ይላታል ቤተ ክርስቲያኒቱን።
ማቴዎስ 5
----------

1 መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል።
1 መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሰጠው ፍቺ በመቅረዝ ውስጥ የሚቀመጥ ብርሃን ለሰዎች ምስክርነትን የሚሰጥ መልካም ስራ እንደሆነ አብራርቶልናል። ማለትም መቅረዝሽን እወስዳለው ማለት በአለማውያን ዘንድ የነበረሽን የብርሃን(የምስክርነት) የኑሮ ዘይቤ እወስድብሻለው እያለ ነው እንጂ ስለዘላለም ሕይወት እያወራ አይደለም። ይህም ትንቢት አሁን ተፈጽሞ በኤፌሶን ማለትም በዛሬዋ ቱርክ ሀገር ቤተ ክርስቲያን የምትባል አካል ምስክረነቷ ጠፍቶ አትታወቅም ጠፍታለችም።

ራእይ 3
----------

1▯ በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር።
1▯ እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።
…
1▯ እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።

አሜን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በሎዶቅያ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያኑ በደሙ በኩል በአብ ዘንድ ያላትን ቦታ ሳይሆን በዚህ አለም ያላቸውን ምስክርነት መሰረት አድርጎ ይገጽጻቸዋል። ሎዶቅያ የምትባለዋ ከተማ ሁለት አቅራቢያዋ ከሚገኙ ከተሞች የሞቀና የቀዘቀዘ ውሃ በመደባለቅ ለብ ያለ ውሃ የሚደርስባት ከተማ ነች። በከተማይቱ ውስጥ ቀዝቃዛና ትኩስ ውሃ የለም ያለው ለብ ያለ ውሃ ነው።ቀዝቃዛ ውሃ ቢኖር ለመጥነት ይውላል ደግሞም ትኩስ ውሃ ቢኖር ለመድኃኒትነት  ይውላል።ለብ ያለ ውሃ ግን ጥቅም አልባ ነው። ጌታ ኢየሱስ በሎዶቂያ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያኑ ትኩስ ሆነሽ ለመድኃኒነትም ሆነ በራድ ሆነሽ ለመጠጥነት እየጠቀምሽ አይደለሽምና ከአፌ ልተፋሽ ነው ይላታል። ይሄ ንግግር የሎዶቂያ ክርስቲያኖች በትክክል ይረዱታል ለብ ያለ ውሃ በአፍ ላይ የሚጎመዝዝና ጥቅም የሌለው እንደሆነ ያውቃሉ።ጌታም በቀላሉ ሊረዱ በሚችሉት ቃላት ይገጽጻቸዋል።

ይህ ክፍል የሚናገረው ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙና ለመልካም አገልግሎት ራሳቸውን እንዲያበቁ የሚናገር ክፍል ሲሆን በፍፁም የዘላለም ሕይወት ጋር የተያያዘ አይደለም። በክርስቶስ ጸጋ በኩል ክርስቲያኖች ለአካሉ ጥቅምና መገንባት መዋል ሲገባቸው አንዳንዶች ግን ለብ ያሉ በመሆናቸው ከአካሉ ግንባታ ውጪ ሆነው በክርስቶስ እየተቀጡ ነው።ጌታ ኢየሱስም የሚወዳቸው፣ ላዳናቸውና ለዘላለም በማያጠፉ እጆቹ የያዛቸው የማይጠፉ ክርስቲያኖች ከመተፋት(ማለትም ለክርስቶስ አካል አገልግሎት ጥቅም አልባ) ከመሆን ወጥተው ትኩስ ሆነው ለመድኃኒትነት ወይም በራድ ሆነው ለመጠጥነት እንዲውሉ የሁሌም ጥሪው ነው።

ይህን ክፍል ይዘው ድነት ሊጠፋ ይችላል ብለው ሊያስረዱ የሚፈልጉ ሰዎች ትኩስ መሆንን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል መቀጣጠል አድርገውና መቀዝቀዝን ደግሞ እንደዚህ አለም ሰዎች በኃጢያት ውስጥ መኖርን አድርገው ይወስዱታል።ይህ ግን ከክፍሉ አንጻር ፈጽሞ የተሳሳተ ነው ምክንያቱም አሜን በሆነው በኢየሱስ ዘንድ ትኩስ መሆንም በራድ መሆንም የተነሱት በበጎ ጎናቸው እንጂ ትኩሱ በበጎ ቀዝቃዛ ደሞ እንደ ክፉ ጎን ተደርጎ አይደለም።

“በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር።”
— ራእይ 3፥15

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ነው ብሎ የተረጎመውን በራድ መጥፋት ወይም ገሀነም ነው ብሎ መተርጎም ልክ አይደለም። ክርስቲያኖችን ሁሉ ትኩስ ሆነው እንደመድሀኒትነት የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ወይም ደግሞ በራድ ሆነው ለመጠጥነት የሚውሉ እንዲሆኑ በጌታ ፍቅር አሳስባለው።ሁላችን ለክርስቶስ  አካል ግንባታ ምንውል እንሆን ዘንድ በጸጋው ይርዳን አሜን።

# የእምነት ቃል አዋጅ

እግዚአብሔረ አምላክ የሁሉ ገዢና ፈጣሪ የሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ስራ በኩል በኃጢያት የወደቅነውን የሰው ዘር ሁሉ ከሰማይ ባፈሰሰው ጸጋ ብቻ አድኖናል። እኛም ሰዎች ከእግዚአብሔር ያለምንም ክፍያ እንዲያው በነፃ የተለቀቀውን ይህንን ታላቅ የድነት ጸጋ የምንቀበልበት መንገድ በእምነት ብቻ እንደሆነ እናምናለን። ይህን ታላቅና በነፃ የፈሰሰልን የጸጋ ስራ የተሰራው በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን እናምናለን።በጸጋ ብቻ መዳናችን ፤ መዳናችንንም የምንቀበልበት መንገድ በእምነት ብቻ መሆኑ ደግሞም የመዳናችንም ስራ የተሰራው በክርስቶስ ብቻ መሆን ውጤቱ ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ መሆኑን እናምናለን። የዚህን የመዳን እውነት ማረጋገጫው የአባቶች ወግ ሳይሆን ቅዱሳት መጽሐፍት ብቻ እንደሆነ እናምናለን።

| | |
|---|---|
| በጸጋ ብቻ | Sola gracia |
| በእምነት ብቻ | Sola fide |
| በክርስቶስ ብቻ | Solus Christus |
| ቅዱሳት መጽሐፍት ብቻ | Sola scriptura |
| ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ | Sola deo gloria |

# ዋቢ

## 39 ኙ የብሉይ ቅዱሳት መጽሐፍት

## 27 ቱ የአዲስ ቅዱሳት መጽሐፍት